

# እሳት ወይ አበባ

ከጸጋዬ ገብረ መድኅን

ሥነ ግጥም

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# እሳት

## ወይ

# አበባ

ከጸጋዬ ገብረ መድኅን

ሥነ ግጥም

ይህን መጽሐፍ በማንኛውም ኤሌክትሮኒክ መሣርያ ለማስተሳላለፍ፤ ለማስቀመጥ፤ በፎቶ ኮፒ ወይም በሌላ መንገድ ለማባዛት ለማሳተምም ሆነ ለመተርጐም፤ የባለመብቱን ፍቃድ እንዲጠየቅ ሕግ ያስገድዳል።

© 1999 የጸገመ ቤተሰብ

በመጀመርያ በ1986 ዓ.ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

ለሁለተኛ ጊዜ በ1899 ዓ.ም. በግራፊክስ ኅንተሚያ ቤት ታተመ

All rights reserved. No pert of this book may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any meens, slectronic, mechanical, photocopying or otherwise, without the prior permission of the publisher.

© 2007 TGM femily

First printed in 1973 by Berhanene Selem

Printing Press, Addis Ababa, Ethiopia

Cover Design: Assegid Gessesse

ISBN 978-0-9793201-0-1

Library of Congress Control Number 2007900859

www.tsegeye.org

info@tsegeye.org

ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን የበርካታ ተወዳጅ ሥነ-ግጥሞች ደራሲ ሆኖ ሳለ፣ “እሳት ወይ አበባ" ብሎ ከሰየመው ከዚህ መድብል ውስጥ ከማሜገኙት በቀር ሌሎች ግጥሞቹ በመፅሐፍ መልክ ለህትመት አልበቁም። “እሳት ወይ አበባ" ለመጨረሻ ጊዜ በ1966 ታትሞ ከወጣ በኋላ ባለፉት ዓመታት ጭራሹን ከገበያ ላይ በመጥፋቱ የጸጋዬን ሥራዎች ህያውነት የሚመኙ አድናቂዎች ቅሬታቸውን ገልጸዋል።

ጸጋዬ ገብረ መድኅን ባለፈባቸው የህይወት ውጣውረድ ከአዕምሮውና ከገሊናው ስርፀው፣ በርቱዕ ብዕሩ ነጥረውና ተውበው የተወለዱ በርካታ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ግጥሞችና ትያትሮች አሉ። በህይወት ሳለ የጠነሰስነውን፣ እነሂህን ሥራዎቹን አስባሰቦ የማላተሙን ተግባር፣ ለ"እሳት ወይ አበባ" ቅድሚያ በመሰጠት ጀምረናል።

ቤተሳቦቹ

ጥር 1999

ለንርዐዮ ኢሳይያስ መታሰቢያ ይሁን።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# መግቢያ

## ሀ/ ሥነ - ግጥምን እንደባለድንጋጌ ታሪክ

አንድ ምእመን የሃይማኖቱን ድንጋጌ ከማተቱ ይልቅ በቀጥታ እግዚአብሔርን በእምነት ማገልገሉ እንደሚበልጥበት ሁሉ፤ ባለቅኔም የሥነ-ግጥሞችን የአደራደር ሥርዓትና ድንጋጌ (ፎርም) ከማተቱ ይልቅ ቅኔውን ተቀኝቶ ደርሶ ፍሬ ሃሳቡን (ኮንቴንት) ማበርከቱ ይበልጥበታል ቢያሰኝም፥ የግል አሰተያየቱን ፈለግ ከጽሑፉ አነፃፅሮ በቅርብ መመልከቱ ደሞ የብዕሩን ዝንባሌ ፈር ሊያሳይ ይችላል ይባላልና፤ ሲሆን እንደሚገባው ሁሉ ሌሎች ያሳቸውን ግምት ለሌሎቹ ትቼ፤ እነሆ እኔም ራሴ ስለሥነ-ግጥም አነሳስ ያለኝን አንዳንድ ሃሳብ አስቀድሜ ባጭሩ ልንገር። "ሥነ-ግጥም ከመሠረቱ ያው የገዛ ሕይወቱ ሂስ ነው፤" ይሳልና ባለቅኔው ማቲው አርኖልድ።

በጠቅሳላው የአሰካኩ ሥርዓት እንደየምጣኔው ወይም እንደየስንኙ ቁጥር ልክ ዓይነተኛ ድንጋጌ ያደረገለትን ሃሳብ-ወለድ (ልብ-ወለድ) ሥኑጽሑፍ ብቻ ሳይሆን፤ ግጥሙ ቤት የሚመታ ወይም የማይመታን እንቆቅልሽ ሆነ ምሳሌና ተረት፤ እንዲሁም! በቃለ-ውበቱና በቃለ-ኃይሉ፤ ወይም በድቀቱ ሥምረት ለአእምሮ ለልቦናና ለስሜት የሚጥምን ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ሁሉሱ፥ ሥነ-ግጥም (ፓኤትሪ) ይሉታል።

መቸም ኪነ-ጥበብ ሁሉ ንጥር የሕይወት አካል ነውና፤ ሥርወ-መነሾው በቀጥታ ከሰው የመሠረተ-ፍጥረት ደመ-ሕይወት ጋር ተጣምሮ ስለሚጠቃቀሰ፤ የሥነ-ግጥምንም የመጀመሪያ ጥሬ መልክ፤ ያው እንደዳንስ፥ እንደሥዕልና እንደሙዚቃ ሁሉ፤ አስቀድሞ በሕፃናት ጨዋታ ሲጨፈር፣ ሲጫርረ፣ ሲተረብና ሲዘፈን እናየዋለን። ቀጥሎም፤ ኪነ-ጥበብ

ከቀዋሚ የኑሮና የመደበኛ ሥራ ክፍሎችም ጋር እያደር ተደጋግፎ ሲጠና፣ እንደየሥራው አንፃር፣ ለምሳሌ፣ በሠርግና በቀብር ሥርዓት አማካዩን የዘፈንና የሙሾ ግጥሞች፣ በግብርና የግብርና ጠቀስ ግጥምና ዜማዎችን፣ በሃይማኖትና በአምልኮ ባዕድም የኒሁኑ ጠቀስ ባሰመዝሙር፣ ባለጸሎት፣ ባለወረብ፣ ባለወሸባና ባለዝየራ ግጥሞችን ተከባክቦ ይታያል። እዚህ ላይ ዋና ዋናው ተግባር ያው ሠርጉ፣ ቀብሩ፣ ግብርናው፣ ሃይማኖቱና እምልኮ-ባዕዱ ሲሆን፤ ለየጉዳዩ የተደረደረው ግጥም ግን ለየተግባሩ ተቀጥሳነትንና ማሞካሸትን ይዞ ኖረ ማለት ነው። ይሁንና፤ የሌላ ሥራ-ክፍል ጥገኛና ተቀጥላ ከመሆን አልፎ፤ ራሱን ችሎ፤ እንደገበሬው ግብርናና እንደ ካህኑ ሃይማኖት መደበኛ የኑሮ ተግባርነት [አሉ፤ የሥነ-ግጥምም ተሰጥዎ ለሞያተኛው ዋናውና መደበኛው ተግባር ከመሆኑም ሌሳ፤ ያው እንደየቋንቋው የአደራደር ሥርዓተ-ድንይጌ የግል ዘይቤና የይዞታ ምዳቤ (ዲስፐሲን)፤ ባጣዕሙ፣ በድቀቱ፣ በቃለ-ውበቱና በቃለ-ኃይሉ ወዘተ፤ ለዕለቱ ብቻ ሳይሆን ለየጊዜው ሽግግርና ለየተከታታዩ ትውልድ ተቀባይነቱን አስፈትኖ ሲደረጅ፥ ሥነ-ግጥሙ ዘላቂ ኪነት (አርት ወይም ጥበብ) ወደመሰኘቱ ቀዋሚ ደረጃ ደረሰ ማለት ነው።

በዚሁም ይዞታና ድርድር፤ በአንድ አንፃር፤ እንደሌሎቹ ኪነ-ጥበባት ሁሉ፤ ሥነ-ግጥምም ከየትውልድ ሀገሩና ከየወራሹ ወገን የሥልጣኔ ዘመናት፤ ግሥጋሜና ውድቀት ጋር ታድሞ፤ አብሮ ገሥግሦና አብቦ አብሮ ወድቆና ተደምሰሶ፤ ወይም ደጋግሞ ታድሶ ወይም ከነአካቴው ጠፍቶ ቢቀርም እንኳ፤ አብዛኛውን ጊዜ የመሠረተ-ቋንቋውን ቅድመ-ድንጋጌና የራሱንም ስያሜ ይዞ እናገኘዋለን። ይሁንና፤ በሌላው አንፃር ደግሞ የግብርና ተግባር ሆነ የልቅሶ ሥነ-ሥርዓት፤ የእማካይ ሥነ-ግጥሞቹን የመሠረት ድርድርና ድንጋጌ ለይቶ ሳያስቀር፥ ያው እንደልጆቹ የየትውልድ ጨዋታና ተረብ፤ እንደጦርነት እስትራተጂና እንደወይዛዝርት የአለባበስ ወግ፤ እንዳንዴ ስያሜውን ከነድንጋጌው፥ አንዳንዴ ስያሜውን ይዞ

ድንጋጌውን ብቻ፥ ወይም ድንጋጌውን ይዞ ስያሜውን ብቻ እንደየዘመኑ የሥልጣኔ ዕድገትና ውድቀት፤ የምርጫ-ውርስና የገድፎ-ውርስ (ሚዩቴሽን ኤንድ ሲሌክሽን) ጣዕምና ዝንባሌ፤ ለውጧል-ይለውጣልም፣ ተለውጧል-ይለወጣልም። ምክንያቱም፤ በጠቅላሳው የኪነ ጥበብ ወይም በተለይ የሥነ-ግጥም ታሪክ፤ የየቋንቋውን የአደራደር መሠረተ-ድንጋጌ በየዘመኑ አበላልጦ ማርቀቁ ብቻ ሳይሆን፤ በየዘመኑ ከሚወራረሱት የሌሎች ቋንቋዎች ልዩ ልዩ የአደራደር መሠረተ ድንጋጌዎች ጋር፤ ከይዞታቸው ምዳቤና (ዲሲፕሲን)፤ ከየምዳቤአቸውም ቴክኒክ ጋር ያደረገው የዕድገትና የውድቀት ታሪክ ጭምር ነው መባሉ፤ "የኪነ-ጥበብ መልእክት ከሰው ተፈጥሮ ወደሰው" ሆኖ፥ ተቀባይነቱም እንደየዘመኑና እንደየትውልዱ የጣዕምና የዝንባሌ ዳኝነት የሚመጠን ስለሆነ ነው።

ለምሳሌ፤ ክክርስቶሰ ልደት በፊት በሰባተኛው ዓመተ-ዓለም ግድም በሆሜር የተቀመረው የኢልያድና የኦዲሴ 'ኤፒክ' የተሰኘው የግሪክ ሥነ-ግጥም፤ አለቀድሞ የነማንን ሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድ ተንተርሶ የተገኘ የዜማ ምዳቤ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፤ ከነማን ቋንቋ የግጥም ሥርዓት ድንጋጌ ጋር ተወራርሶና ተዳቅሎ የወጣ መሆኑንም ጭምር፤ የቅድመ እሌናውያን ባለታሪኮች ሲነግሩን፤ መጀመሪያ ወዲያው የሆሜር 'ኢልያድና ኦዲሴ' ተቀምሮ ሠላሳ ዓመት ሳይሞላው ባለቅኔዎቹ ካሊኑስና ቲቂይራታኡስ የሌኤፕኪን "ሄክሳሚተር" (የኤፒክን የስንኝ ስልት ቁጥር) ድንጋጌ ለውጠው ወይም ቀሳቅለው "ኤሌጂ" ባሰኙት የሰንኝ ለልት ቁጥር ድንጋጌ ሲቀኙ፤ ደራሲው ሴፕሲስ ደግሞ ሰማንያ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ፤ ከሥርዓተ-አምልኮ ባዕዱ የዜማ መሠረተ-ምዳቤ ውሰጥ የተካፋዮቹን እደራደር ቀይሶ ጻፈ። ዛሬማ፤ እንኳንና የነሆሜር 'ኤፒክ' የቀድሞው የኣደራደር ሥርዓተ ድንጋጌ አያሌ ጊዜ መሰዋወጥ ቀርቶ፤ 'የምዕራባውያን ሥልጣኔ ምንጭ' ተብሎ የሚታመንበት ቋንቋው ጭምር እያደር ተትቶና በትውልድ ሀገሩ እንኳ ሳይቀር እጅግ እስከሚያሳስት ድረስ ቢቀያየርም፤

የኤፒክ ሄክሳሚተር የመሠረት ስንኝ ስልት ቁጥርና ስያሜው ግን እንደነበረ ለማታውቁ ያህል ያው አሁንም ይታወቃል። በቀድሞው ደረጃ ከቶውኑ አይሁን እንጂ በጥንታዊ የግሪክ ቋንቋ ጥናት ትውስታ ጊዜም ይሠራበታል። ነገር ግን፤ ከአያሌ ቋንቋዎችና ከየሥነ-ግጥማቸው የመሠረተ ሥርዓተ ድንጋጌዎች ጋር ለአያሌ ምዕተ-ዓመታት ተወራርሷልና በቅድመ-ፍጥረት አባትነቱ ዛሬም ተከብሮ ይኖራል። በጊዜው እንደሱ ገናና ከነበሩትና፤ ለምሳሌም ክርስቶስ ራሱ መጀመሪያ ሰብኮበት ነበር ተብሎ እንደሚታመነው እንደአረማይክ ቋንቋ ግን ከነሥነ-ግጥም ድንጋጌው ጋር ጨርሶ አልጠፋም። የሁለቱ የታሪክ ልዩነት ይኸ ነው። እንደዚሁም፤ የአክሱማውያን ሥልጣኔ ተነሳቶ በደመቀበት ከክርስቶስ ልደት በፊት በሰድስተኛውና በይበልጥም እስከ አራተኛው ዓመተ-ዓለም ግድም እንደነአሰታርና አልሙጋህ ያሉትን የሳባውያን ሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድምና የኩሽንም ወገን ሥርዓተ-አምልኮ-ባፅድ ተንተርዕ፤ ከኒህና ከሌሎችም ቋንቋዎች ተወራርሶና ተዳቅሎ የተፈጠረው የግዕዝ ቋንቋ፤ በየጊዜው ቀምሮት ከነበረው ከሥነ-ግጥሞቹ የመሠረት ሥርዓተ-ድንጋጌዎች ውስጥ፥ ዛሬም በኒሁ ቋንቋዎች በተለይም በኩሽና በሳባዊው የአረብ የሰንኝ ሰልት ድንጋጌዎች ውስጥ መገቼታቸው፥ የታሪክ እንጂ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ አይደለም። ለምሳሌ፤ ከግዕዝ ቅኔ በተለይ የወል ቤት የምንለው ባለሰድስት የስንኝ ሰልት ቁጥር ድርድር፤ በአረብኛ፤ በሱዳኑም የዳንጉላዊሰና የመህሳ የጥንት ኑባውያን፣ በሶማሌ፣ በኩሽ፣ በኢትዮጵያም የኩሽና የሴም ዲቃላ ቋንቋዎች የግጥም ድንጋጌ ውሰጥ ልክ እንደግዕዙ ድርድር በጥራት ተሳክቶ እናገኘዋለን። 'አሰታር' የተሰኘችይቱም የሳባውያኑ ሴቴ ጣዖት በሥርዓተ-አምልኮ-ባዕድ ዜማና በጽሳትም ቅርፅ፤ ከጥንተ-ምሥርዋ ሴቴ-እምሳክ ከ 'አስቶር' ጋር ስለምትመሳሳል የሚቶሎጂ ምሁራን መወራረሳቸውን ይነግራሉ።

እንግዲህ በጠቅላላው፤ በአንድ ፊት፤ እንደኪነ-ጥበባት ሁሉ፤ የሥነ-ግጥምን ድንጋጌ ይኸኛው ዓይነት ብቻ መሆን አለበት፤ ወይም ደግሞ ከዚህኛው የቋንቋ መሠረተ ድንጋጌ በተወረሰው ዓይነት ብቻ መመራት አለብን ብሎ መወሳን፤ ያው ከተወሳነ እእምሮ የሚወጣ ድፍረት ነው ብንልም፤ በሌላው መልክ ደግሞ፤ ቁጥሩን (ሚተሩን ወይም 'ምቱንነ የተመደበ የሰንኝ ሰልትና ቤት ባልደነገገው የቃላት መረን አሂዶ እነሆ ሥኑግጥም ማለቱም የባሰ ጸያፍ ማሰኘቱ ሳይሳነን፤ ከላይ እንደጠቀሰኩት እንደምእመኑ ሃይማኖት ዓይነት፤ ባለቅኔም የሥነ-ግጥሞችን የአደራደር ድንጋጌ ከማተቱቴ ይልቅ ቅኔውን (ተቀኝቶ) ደርሶ ማባርከቱ ይበልጥበት ይመሰለኛል። ሰለሆነም ለምሳሌ፤ አብዛኛዎቹ የኔ ግጥሞች ካሁን ቀደም ብዙዎች ጠይቀውኝ እንደመለስኩት ሁሉ፥ እሰካሁን ከተለመዱት ከዋነኞቹ ከግዕዝ እስከ አማርኛ ውርሰ የሥነ-ግጥም ድንጋጌዎች ውሰጥ፤ ማለት፤ የወል ቤት እንዳልነው ባለሰድስት (ሁለት ባለሦስት ሐረግ) ፤ እንደ ቡሄ በሉ ቤት ባለ ሁለት ወይም እንደ በገና እንጉርጉሮ ቤት ባለ ሰድስት (ሦስት ባለ ሁለት ሐረግ) እንደሆያሆዬና እንደ ሰንጎ መገን ቤት ባለ አምስት ወይም ከኒህ ከዋነኞቹ ተቀላቅለው በመዋለድ እንደተባዙት፤ ለምሳሌ እንደመዲና (ከነሰሙ 'መዲናገ፤ ከሰንጎ መገንና ከቡሄ በሉ ቤት አፈራርቆ እንደሚደረደረውና እንደሚደረደሩት ብዙዎች የኩሽና የሳባውያን አረብ ዲቃላ ቋንቋዎች የዘልማድ ሕግጋት ሳይሆን፤ የቁጥሩን መለያ መሠረት አንድ ራሱን በስምንት የሰንኝ ሰልት ድንጋጌ ላይ ሰለምደረድረው ብቻ ነው። ይኸም በአደራደርና በሠረዝ ነጥብ ተከፍሎ ይታያል። አንዳንድ መምህራን የዚህን ድንጋጌ ዘይቤ (ሰታይል) ሰም ስላላገኙለትና እኔም ስላልሰየምኩት “የጸጋዬ ቤት" ይሉታል። ሰምንቱን ስንኝ አብዛኛውን ጊዜ ቀዋሚ አድርጌ የምከፍለው በአራት-በአራት ሐረግ ነው። አልፎ እልፎ ግን፤ በሦስት-በሁለትና-በሦስት፤ በሁለት-በሦስትና-በሦስት፤ በሦስት-በሦስትና-በሁለት በማፈራረቅ እየከፈልኩ መደርደሩም

የለውጥንና ያለማሰልቸትን ጠባይ ማስገኘቱን ስለገመትኩ ነው። በተጨማሪም፤ በተለመደው የወል ግጥም ድርድር የጻፍኳቸው ጥቂት ግጥሞች አሉ። ከዚህ ሌላ፤ ስለቦረንና ስለ ክፋ በጻፍኳቸውና በተረጐምኳቸው ሦስት ግጥሞች ብቻ፤ ያንኑ የኦሮሞን ኩሽሽ "ማከማከሳና ሙርቲ" የተሰኘ፤ በሁለት-በአራትና-በአራት፤ በሁለትና-በአምስት፤ በሁለት-በሦስትና-በሁለት ሐረግ የሚፈራረቅ የስንኝ ሰልት ድንጋጌ ተከትዬ፤ ለምሳሌ ያህል ያሰፈርኳቸው አሉ። እንግዲህ ቀድሞ እንደተባለውም፤ ባለቅኔም የዚያው የባህሉን ቅርስ አቆይቶና መግቦ ላወረሰው የገዛ ሕዝቡ የስሜት ጫፍ ተቀጥላ እንደመሆኑ፤ ከጆሮና ከአንደበቱ ድምፅ የቀመረውን ሰልት በራሱ ዘይቤ እያስተጋባ ቅርሱን በልዩ የምስክርነት መለዮ ሲያድሰና ሲገልጽ ቆይቶ-ኖሮ ማለፉ የተለመደ ሲሆን፤ ሁለት ባልቴቶችም ሦስተኛይቱ ቤት በቀመሱት የቡና ጣዕምና ቃና ባይሰማሙ፤ የሕይወት አካል ኪነ-ጥበብም እንደ ሕይወት ቅመም ቃናው ለልዩ ቀማሾች የተለያየ ሆኖ መታየቱን እንጂ ባሕርዩ ከቶም ያልተለመደ ጉዳይ መሆኑን አይነግረንም። ይሁንና ባለ ቅኔው አልፍሬድ ሀውሰማን "መድኃኒት ቀማሚዎች ጨው የሚለውን ቃል እንደሚያሰቡት፤ እኛም ሥነ-ግጥም" የሚለውን ቃል እንዳናስበው አደራ እንጠብቅ፤" ሲል በሌላ መልክ የዚሁኑ የነበረ የልዩነት ነፃነት መንገሩ ይመስለኛል። በዚህ መጽሐፍ የተጠረዙት ግጥሞች ጠቅላላ የግጥም ሥራዎቼ ሳይሆኑ፤ ከድምሩ ውሰጥ ከየዓይነቱ መርጬ ያቀረብኳቸውን ብቻ ነው። ከዚህም ሌላ ለአንባብያን ላስታውስ የምወደው፤ ለምሳሌ "እናት" ማለት ሣዝዳ" ለሚለው የኦሮምኛ የኩሽ ቃል፤ "ዳ" ለተሰኘው ትክክለኛ የልሣን ምልክት፥ በቀደምቱ በኢሮግሊፊክ ፊደል እንጂ በኋለኞቹ ወራሾች በሴማውያን፤ ወይም በግሪክና በላቲን ፊደሎች ውስጥ ሰላልተመደበለት፥ እነሆ ለጊዜው "ደ" በተሰኘው የሳባውያን ወይም የግዕዝ ፊደል አናት ላይ "" ይኸን ቁም-ሠረዝ በማከል ጫ" እያሰኘሁ መጠቀሜን ነው። 3

## ለ/ ሥነ-ግጥምን እንደ ቃለ-ሕጅወት ፈለግ ፍሬ-ሃሳብ

የኪነ-ጥበብ ፈለግ በሚውተበተብበት ዋዜማ ጠንቋይ ጠቢብ ነውና፤ በአፈ-ሊቃውንቱ ወረርሺኝ ብዛት እንደኮካ-ኮላ የማስታወቂያ ግጥም ዓይነቱ ጭምር የነገውን ትውልድ የሥነ-ባህል ሥፍራ ተከቶ፤ የሕፃናቱም አንደበት በእንቆቅልሹ 'እ-ቡ-ጊ-ዳ' ሲታጠንና ሲታነፅ እያየነው፤ የባለቅኔው ብዕር መልእክቱን ሁልጊዜም ወደተረሳው ወደኣበው ጥንተ-ድንጋጌ እንጂ ወደ አዲሱ ዓለም ሕይወት አይሳክ ብንል፤ ሌሳው ቀርቶ እነድራይደን እንኳ፤ "የሞራል እውነታም የባለ ቅኔው ፍቅረኛ እኮ ናት፤" ይሉናል። ይህም ማለት፤ የዘልማድ ንፍገት ያጥሳሳውን አውነታ ደሞ አባብሰን በይበልጥ ለማጐልደፍ ሳይሆን፤ ይልቅስ፤ ውስጣዊና ሕያዊ ባሕርዩን መርጦ አንቅቶ፥ ውበት አክሎ፥ በአሰተዋይ ኀሊናችን ውስጥ ቁሰሉን የመፈወሱም ጥረት፤ ለሥነ-ግጥም ያው የኖረ ጠባይዋና ደመ-ሕይወቷ ነው። መቸም ቢሆን የእውነት ፍቅር ያነጠራትን ዘለዓለማዊት ኪነ-ጥበብ አእምሮ የገራው ሰሜት ይፋ ያወጣታል ይሳልና ኮለሪጅ።

ግሪኮች ባለቅኔዎቻቸውን ለሁለት ከፍለው፤ የአንደኛውን ወገን ድንጋጌን ተከባክበው - እሚቀርፁ፤ ሲሏቸው፤ የሁለተኛውን ደግሞ ቃለ-ሕይወትን አንቅተው-እሚፀንሱ እንደሚሏቸው ይገልጽና ደራሲው ጊልበርት፤ "ሁለቱም ወገን እኩዮች ናቸው። ያም ሆኖ ያንዱ እኩያነት ከሌላው ያይላል" ይላል። የሥነ-ግጥም ኀሊና በየትውልዱ የሕይወት ተአምር የመደነቅ ሕዋስዋን፥ እያደር ቆዳውን በሚቀይርባት ንፍገት ስትገደብ፥ ሁሉን-አወቅ የምጸተኝነት ባሕርይዋ ይተናነቃትና ለጋ ሃሳብ የምትፀንሰሰበት ልቦናዋም እየጠበበ ትነጥፋለች። "ሁሉን-አወቅነት፥ የእኔነትን (ጎን) ሕልውና፥ ሁሉን-ጠየቅነት ደሞ የመፍጠርን የልብ ወለድን) ፅንሰ-ሕልውና ያስከትሳል፤" እንዲል ባለቅኔው ብሪኒን። ዘለቄታ የሚኖረው ሥነ-ግጥም የሰውን ልጅ ዘለዓለማዊ የሐቅ እውነታ ሊያቅፍና

ሊያበሥር ይሻዋልና። ዎርድስዎርዝ ለጆን ዊልሰን በጻፈለት ደብዳቤው ይኸን ጉዳይ ተመራምሮ ሊመልስ፥ የግጥም ኪነት ሰብአዊነታችንን የሚያስደሰት ትርኢት ነው ሰንል ሰብአዊ ፍጥረታችንንም የማይሸነግል መሆኑ ይታወቀናል፤ ካለ በኋላ፥ ይህንኑ እንዴት ከመንፈሳችን እንደምናገናዝበው ሲያስረዳ "...እርቃነ ልቦናችንን ወደ አልባሌው ሰው የየዕለት ሕይወት ገልጠን ተፈጥሮአችንን በተፈጥሮው ገጽ ከማስተዋል..." የምንቀምረው ሲሆን ነው ይሳል። ሸክላ ሠሪ ጡቧን፤ ተፈጥሮ እኛን ከልዩ ትቢያ እንደምትቀርጽ ሁሉሌ፥ ባለቅኔም ኪነትን ከምርጥ ቃለ-ሕይወት ዳግመኛ ፈጠረ ሲባል፤ ተፈጥሮ የለገሠችው ዕድሜውንም በሕይወት ዋጋ ላይ እንደ ማዕድን ፈትኖና አንጥሮ ፍሬዋን ብቻ የማብሠር ግለኛ ጥረቱን፥ "ያ ለማንም ሰው ከሚሰማው ይፋ ሰሜት፤ ለሕፃኑ እንኳ ከሚሰማው ይፋ ሰሜት፤ ሌላው በተደሰተ ከሚያሰደስተን፤ ሌላው ባዘነ ከሚያሳዝነን፥ ነፍሱን ከነፍሳችን ከሚያጣምረን 'የፈለቀ'፤ ያ ነው የኪነ-ጥበብ ደመ-ሕይወት፤'" ይለዋል ቶልስቶይ። በኪነ-ጥበብ የተስጥዎ ግዳጁ ተዳክሞ ተጭለምልሞ ነፍሱን ሲያሳድፍና የሰሙን ዕጩኸት በምጥ በማስተጋባቱ ብቻ ዕለታዊ ተደማጭነትን እንደጥቅም ሲቃርምና ሲዘርፍ ግን፤ '...ያማ የኪነቱን የእውነታ አቅጣጫ ስቶ ብፅሩንም አሳተ፣ ማለት ነው ይሳል ብሮኖውሰኪኪ።፡

ያም ሆኖ፤ በሌሳ መልኳ፤ ሥነ-ግጥም ሕይወትን ተቻችሎም ሆነ አተኩሮ ለመዝለቅ ሲባል ኀሊናን በኅሊና የመፈተን ውጤት ስትሆን፤ አንዳንዴም ከብቸኝነት ሕልውናችን ውስጥ ብቻ የምትደመጥ ሙዚቃዊ ፊደል ናትና፣፤ የኑሮን ውትብትብ ጠልቀን፣ ሠርሥረን ገብተን አገኘን የምንለውን ፍሬ-ሃሳብ መንጥቀን አውጥተን በአደባባይ ስንገልጥ፤ 'ቃልን' በውበት በድቀትና በአክብሮት እንዲንጸባረቅ ካደረግነው፤ የየፈንታችንን ፀንስን አሳልፈነዋልና፤ 'ቃልን' ገደፍክ አንባልም። ቃል ኃይል ነውና። ቃል ውበት ነውና። ቃል እውነት ነውና። ቃል ሕይወት ነውና። "አስቀድሞ

ቃል ነበረ፤ ቃልም በአግዜብሔር ዘንድ ነበረ፤ ያም ቃል እግዚአብሔር ነበረ፤" እንዲል።

ጸ. ገ. መ.

## ማውጫ

መግቢያ ....... 6
ይድረስ ለወንድሜ ለማላውቅህ ....... 18
አይ መርካቶ ....... 24
ቃል ቃተተ ....... 28
የብዕር አሟሟት ሌላ ....... 31
ክልስ - አባ - ልበ - እግረኛ ....... 33
መውደድ አባ ጸጸት ....... 38
መተማን በሕልም ....... 41
በቃኝ ....... 43
ቦረን (የሃዩ አላኬ ሊበን ቀረርቶ) ....... 45
ዋ! .... ያቺ ዓድዋ ....... 48
ሕይወት ቢራቢሮ ....... 52
መሸ ደሞ አምባ ልውጣ! ....... 59
ማነው .... 'ምንትስ'ገ ....... 60
'እከካም ተማሪ' ....... 73
ረሃብ ስንት ቀን ይፈጃል? ....... 82
ምነው አምቦ? ....... 86
"አቴቴ ዱብራ አሮሞ" ....... 87
ምንም አልል ....... 90
አዋሽ ....... 92
እግር እንይ! ....... 100
አንኮበር ....... 103

ደኅና ዋይ እማማ.....108
ሊማ-ሊሞ ..... 112
ኅል!.....114
አዴ አዳዬ..... 117
የት አባቱ ሞትም ይሙት! .....125
ሰቆቃው ጴጥሮስ .....128
እንቅልፍ ነው እሚያስወስድህ.....134
እሳት ወይ አበባ.....137
አስቀመጡህ አሉ! .....154
አባይ.....159
መሄዴ ነው .....165
ዶጋሊ .....166
ቦረን (የሙርቲ-ጸሎት-ጥሪ).....167
ውሸታም .....169
ከፋ ..... 171
"እሳት ዐመድ ወለደ" .....172
ሕረር .....175
እውነት አሁን አንቺ እሷ ነሽ!.....177
በራ፣ የመስቀል ደመራ .....180
ጌራ .....182
ማይጨው .....192
ድሬ-ዳዋ.....194
ተወኝ.....196

ድንቅም አደል? ........................................ 198
ኣብረን ዝም እንበል ........................................ 200
አሥመራ ........................................ 203
ወንድ ብቻውን ነው እሚያለቅስ ........................................ 204
ትዝታ ........................................ 208
አዘቦን ዳግም አየኋት ........................................ 209
እንዳይነግርህ አንዳች እውነት! ........................................ 211
የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ ........................................ 213
ስለደራሲው በጥቂቱ ........................................ 219

# ይድረስ ለወንድሜ ለማላውቅህ

ይድረስ ላንተ ለማላውቅህ
ለወንድሜ ሩቅ ለማልፍህ
ለምታውቀኝ-ለማላውቅህ፥ ለምታየኝ-ለማላይህ....

ማነህ ባክህ?

ሳትወደኝም ሳታምነኝም፥ አጢነህ ለምትፈራኝ
ስናገርህ አጠንቅረህ፥ አተኩረህ ለምትሰማኝ, ...
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፥ ለአረህ ዚሪው ለገታሩ
ለሩቅ ገጠሬ ነባሩ
ለማላውቅህ ለዳርዳሩ...

ማነህ

ከሩቅ የምታሰተውለኝ
የማልለይህ-የምትለየኝ

ተግተህ የምትገምተኝ፥ ያላየኸኝ አስመሰለህ
አቀርቅረህ ተግ ብለህ
ባንደበትህ የእርግማን መርዝ፥ በልብህ ትእዝብት ቋጥረህ...

የፀጥታው የዋሻው ሱቅ
ማነህ አንተ የቅርቤ-ሩቅ

ከረን ነህ መለሎ ብሌን
ከአሰብ ወደብ እስከ ሰሜን

ሰትሳብ ሰትሰበሰብ
ሽንጠ ሰንበሌጠ-መርገብ
ከኡመራ ነህ ከመረብ
አኑአከ ነህ ወይስ ገለብ

ከዘር ተገፍተህ ተሰደህ
በሐሩር ሰደድ ተጥለህ
በንዳድ መቀመቅ ታጥረህ
በእልቂት አፋፍ ፈፋ ያለህ

ማነህ

'አጋው' ነህ ወይስ ሺናሻ
ቅማንቴ ነህ ወይ ፈላሻ
ሰምህ የሆነብን ግርሻ፥

ግራ ጐንደር ነህ መተከል
ባላዋቂ የምላስ ቅርስ፤ የዘር ንፍገት ሰትቀበል
ያለዕዳህ ሰምህ ሲበከል
እምትችል እምትቀበል፥ እማትሞት እማትነቀል

ማነህ

ቆለኛ ሸክላ ሠሪ ነህ
ያገር ዕድል ያገለለህ።

ለጥበብህ እንደመካሰ
በደባትር ትንታግ ምላሰ
ዘለዓለም ልብህ የሚላስ

ማነህ

ገባር ነህ የሙከት ሳቢ
እረኛ ነህ የከብት አርቢ
አራሽ ነህ ያገር ቀላቢ
አማል ነህ የግመል ባቢ ...

ባክህ ማነህ ወንድምዬ፥ አንድም ቀን የማንወያይ
በውል፥ በጣይ፥ ባደባባይ

በፎቶ ግራፍ ዓይን እንጂ፥ ዓይን ለዓይን የማንተያይ
እኔ ለወሬ አንተን መሳይ፥ አንተ ለጭንቅ እኔን መሳይ።

ማነህ እኮ የማላውቅህ
ማዶ ለማዶ ሩቅ ለሩቅ፥ በመኪና ዓይን የማይህ
የማትቀርበኝ የማልቀርብህ
ጠረንክን የምጠየፍህ
በጋዜጣ በመጽሔት፥ ወሬህን የምተርክህ
ሥዕልክን ፎቶግራፍክን፥ ላገር ጐብኚ የምሸጥህ፥

ማነህ አንተ ወንድምዬ፥ የማላውቅህ የምታውቀኝ
ሶዶሬ ማዶ እምታልፈኝ
በዝምታህ የምትከሰኝ
ባይንህ ጦር የምትገሥፀኝ
የሆድክን የማልጠይቅህ፥ የሆድክን የማትነግረኝ፥

ማነህ

ቦረን ነህ አባ ጋናሌ
የኛጻ ጠር አባ ጣሌ
ወይ 'ላፋር'' ንጥረ ሶማሌ፥
ከረን ነህ ወይስ ዳንካሌ

አፋር ነህ አባ ቱማታ
ማታሐራ ወይ ከምባታ
ወይስ ኩናማ አባ ዱታ፥

ማነህ ጐበዝ ማነህ እያ
ኢማኑ ነህ አባ ራያ

ወይስ ኢቱ አባ ሎቲ
የአዳል ሞእ የአዳል ሞቲ፥

እኮ ማነህ ሩቅ ያለኸው
ማንነትክን የማላውቀው
እማልሰማ እማልጠይቅህ
እማትነግረኝ እማላውቅህ፥

ማነህ ጐበዝ ሳስተውልህ፥ አተኩረህ ጭጭ እምትል
እማትታጠፍ ቅምጥል
መሃል አገር ያልሸተተህ
ባሻገር ዙር ድንበር ያለህ
የእህል ደላላ እሚበላህ
ባለሚዛን እሚያዋካህ፥

ማነህ

የዝምታ መደብር ነህ?...
እኮ ማነህ ስምህ ማነው
የዘር ግንድህ የሰየመው
ተበጥሶ ያልተቀጠሰው
ሥርህ ማነው?....

በልቦናህ የምታማኝ
ታዝበህ የምትስማኝ
ባትወደኝም ባታምነኝም፤ አጢነህ የምትፈራኝ
ማክበር እንጂ እማታስጠጋኝ፥

ማንነትክን ምንነትክን፥ ሳልሰማህ የምጠይቅህ
ለጉልበት ለላብህ በቀር፥ ላንተነትህ የማልቀርብህ
ከዓይነ-ጥላዬ እምትሸሸኝ፤ ከዓይነ-ጥላህ እማልርቅህ
ላፌ እንጂ ለልቦናዬ፥ የማትመስለኝ የማልመስልህ
ከመንፈሴ እምገልልህ
ከሕሊናዬ እማሸሽህ

ቦታህን የማትረሳ፥ ቦታህን የማስታውስህ....

ማነህ

ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፥ ሕመምክን ለማታዋየኝ
በጸጥታህ ለምትወቅሰኝ

ጐፈሬህን እንደአባትህ፥ እንደሞያህ አጐፍረህ
በወለባ አንቆጥቁጠህ
ሎቲ አጥልቀህ ጦር አንግበህ
በመኪና እግር እማልፍህ
የማትጠራኝ የማላውቅህ፥

ማነህ

በየቱሪስቱ ካርድ ላይ
ከቦህ ሰማያዊ ሰማይ
አተኩረህ የምትታይ
ውሽትክን ፈጠህ ሳቅሁ ባይ፥

እንደቴክኖክራሲ አግቦ
ዙሪያህ በሀስት ጌጥ ታጅቦ

እፎይታ ያቀፈህ መስለህ
ትእዝብት በዓይንህ ጦር አዝለህ
ርቀህ ተቀብረህ ሰንብተህ
የቱሪስት ካርድ የሳበህ

አንተ ማነህ?

እኮ ማነህ ወንድምዬ፥ ደራሲ የሚቀኝብህ
ሠዓሲ የሚነድፍብህ
ቀሲስ የሚቀስስብህ
የቱሪስት የጋዜጠኛ፥ ካሜራ እሚጋባዝብህ

የሚተች የሚተረጒም፤ የሚነድፍህ የማንም እጅ
የማነህ ደም የማነህ ቅጅ?...
ኣንተ የማማ ኢትዮጵያ ልጅ
እኔማ ሆኜብህ ፈረንጅ

አሳብ ለአሳብ ለተጣጣን
ምን አጣላን ማን አጣላን
ማን እንዳንወያይ ገራን
እንደባቢሎን ኬላ ግንብ፥ ለመተላለፍ የቀባን
አንተን የዘልማድ ዘላን፥እኔን የመኪና ዘላን
እንድንሆን የገፋፋን?
ማነው ምንድነው ወንድሜ፥ ሆድ ለሆድ የሚያናክሰን
ሳንርቅ የሚያራርቀን፥ ሳናኮርፍ የሚያኳርፈን!...
ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፥ ለምትሳብ ናዳ ጥጉን
ፈፋ ዙሪያ ሸንተረሩን
ሸለቆውን ፈረፈሩን
ዳር ድንበሩን ሩቁን-ሩቁን፥

ከዘር ተገፍተህ ተሰደህ
በሐሩር ሰደድ ተጥለህ
በንዳድ መቀመቅ ታጥረህ
በእልቂት አፋፍ ፈፋ ላለህ...

እኛ መሀል ለሌለኸው
ታሪክህ ለተሸፈነው
ሁሉን ከሩቅ አብሰልስለህ አጠንቅረህ ለምታየው...

ይድረስ ለክቡር ወንድሜ፥ ለምታየኝ ለማላይህ
ለምታውቀኝ ለማላውቅህ
ማነህ ባክህ...

ማነህ

ለበጌምድር ወይጦ ባላገር - (፲፱፻፷፫ - ደባርቅ)

# አይ መርካቶ

አገር ከየጕራው ወጥቶ
አንቺን ብሎ ነቅሎ መጥቶ
ግሣንጉሡን ጓዙን ሞልቶ
ጎልቄ መሣፍርትሽ ፈልቶ
ባንቺ ባዝኖ ተንከራትቶ
እንደባዘቶ ተባዝቶ
ተንጠራውዞ ዋትቶ ዋትቶ
አይ መርካቶ፥

የምድር ዓፅም የእንጀራ እናት
ላንዱ ርካሽ ለሌላ እሳት
ላንዱ ፍትሃት ላንዱ ምትሃት
ላንዱ ሲሳይ ላንዱ ፍርሃት
ላንዱ ተስፋ ላንዱ ሥጋት
የግርግር የሆይታ ቋት

አይ መርካቶ፥
ያንዱን ወስዶ ላንድ ስጥቶ
ያንዱን ገፍፎ ላንዱ አብልቶ
አንዱን ነስቶ ላንዱ አድልቶ
ስንቱን ፈርቶ ሰንቱን ሸሽቶ
ባፈ-ጮሌ ተሸልቶ

አይ መርካቶ፥

ቢያዋጣ ወይ ባያዋጣ
ከስንቱ ተንጣጥቶ ጣጣ

ተነታርኮ ተገዛግዞ
ተብለጥልጦ ተበዛብዞ

መርካቶ ያገር ድግሱ
የገጠር ስንቅ አግበስብሱ
ለከተሜው ለአባ ከርሱ
በትሬንታው በአውቶቡሱ
በቁሳቁስ ግሣንጉሱ
ለቱጃር የጥጋብ ቅርሱ
ለኔ ብጤም የቀን ጉርሱ
አባ መስጠት እጦት ቢሱ

አይ መርካቶ፥
ተሻምቶ ተገበያይቶ
ወይ ተፈራርሶ ተጣልቶ
በእንካ ስላንቲያ ተማትቶ
አንዳንዴም ተፈነካክቶ
ወይ ተመራርቆ ተስማምቶ
አይ መርካቶ፥

የኤስፔራንቶ የቋንቋ አዝር
ያ ሲነገር ያ ሲሰበር
የስንቱ ልሣን ሲቀመር

ያንዱን ሲያከር ያንዱን ሲያቀር
ያንዱን ሲያውስ ያንዱን ሲያስቀር
ያ ሲደቀል ያ ሲፈጠር

የልሣን ሸማች ለብቻ
ከዕቃው ጭምር በስልቻ
ሲመዠርጥ እንደግቻ
ቶሎ በል ቶሎ በል ብቻ፥

ዝግ በሉ እማይባልበት
መርካቶ የአንደበት ፍላት
ግርግር እሚባልባት
ክርክር እሚሞቅባት
ወዝ እሚንጠፈጠፍባት
ሸቀጥ እሚታመቅባት
ደላላ የሚያውጅባት
ቸርቻሪ እሚተምምባት
ሌባ ላብክን የሚያልብባት

አይ መርካቶ፥

መርካቶ የገበያ ጎራ
ላንዱ ምድር ላንዱ ጣራ
ያ ሲዘረፍ ያ ሲደራ
ያ ሲወስን ያ ሲፈራ
ያ ሲሸሽግ ያ ሲያወራ
የንግድን ጠፍ ወይ የአዝመራ
የነጋዴን ምጥ መከራ፥

የከበረ እንደመረዋ፥ ረብጣ አፍኖት ሲያስገመግም
የከሰረ እንደ ፈሳስፉ፥ በቁም ቅዥት ሲያልጐመጉም
የኔ ብጤም ጠብሻን መቶት፥ በየጥሻው ሲያስሰስመልም
| ቸርቻሪ ዝርዝሩን ቋጥሮ፥ ቅንጣቢውን ሲቃርም
የወር ሸማች ስንቁን ጭኖ፥ ሲመርቅና ሲረግም
ማጅራት መቺ ከጀርባው፥ ጥሻውን ዘሎ ሲያዘግም

ከዚህ በርሮ እዚያ ስብሮ፥* ያዝ ሲባል ሲሸሽ ሲጣጣር
ካማኑኤል እራጉኤል፥ ሾልኮ ዶሮ ማነቂያ ዳር
ከመስጊድ እስከበረንዳ፥ ከአራተኛ እስከነፍስ ይማር

የኡኡታው የጡሩምባው፥ የጩኸቱ የፊሽካው ሣግ
የሰው የመኪና የከብት፥ የፍግ የቁሳቁስ ትንፋግ
ሲገፋተር ሲመዣረጥ፥ ሳቦት ለላቦት ሲላላግ
ትንፋሽ ስትንፋሽ ሲማማግ

አባ ሽብሩ መርካቶ፥ ያለውን በገፍ አጣጥቶ
የሌለውን ከሌሰበት፥ አስጐልጉሎ አስወጥቶ
ስንቱን ከዳር ዳር አዛምቶ
በግድም በውድ አስማምቶ
አገርን ካገር አካትቶ
ሁሉን አቀፍ ባይ መርካቶ
ያቻችለዋል አሻምቶ፥
አይ መርካቶ ጻ

፲፱፻፷፫ - መርካቶ

# ቃል ቃተተ

ቃል አይሞትም ይሏል እንጂ፥ እስትንፋስ ይሞታል ቅሉ
ቃሌ በፅንሱ በነነ፥ እፍ አልሺውና በሽሉ።

ለካስ በቁጠማ ነዶ፥ ዕርግብ ፍላፃ ደብቃ
በንሥር ልቦና መጥቃ
አለሳልሳ አማቅቃ

አምኗት ሲታበይ ነበረ
ያየር ያድማሳት ገሞራው፥ ያ እንደጋሬጣ የሾረ
ርቱእ ጥፍሩ የነፈረ።

ፍጡርሽን መለኮት ብዬ፥ በሥጋ ለበስ ዝንጋኤ
እንደ ብሩክታዊት እንባ፥ ተማጽኜሽ በሱባዔ
"ዝውእቱ ዳግማዊት ሞት0 ወእስመ አልቦ ትንሣኤ።፡...

ምጤን ጭንቁን እንደአንከርት በልቦናሽ አጠንጥኜ
ከባዕድም ከወዳጅም፥ ዓይንና ጆሮ ሸፍኜ
እንደጉድ ፍቅሬን ቀብሬ፥፤ በእምነትሽ ጥላ ከድኜ
የአንጀት ፍሜን ነበልባሌን፥ አዳፍኜ ተዳፍኜ፥

አዬ ሥጋ ለበስ ተስፋ
እንዲህ ላም ኣለኝ በስማይ፥ የምኞት ዘር አሳቅፋ
ያም በምድረ-በዳ ፈፋ
ካልሳምናት የዕፀ-በለስ ዛፍ፥ ከማንደርለባት ተቀርፋ
በሕልም አንኳ ግጠን ሳንወጣት፤ በቁም ቅት ስታስለፋ...
ምነው ረቂቅ ሽል መቅጠፉ? የውን ውላችንስ ይጥፋ
ቃላችንን ካስጐሰበትን፥0 እንደ ሥራ-ቤት ልፈፋ

እንደቀፈፋ አቆማዳ* ምሥጢር ካፎቱ ከሰፋ
እንደባለጌ መቀነት፥ዐ ውሉ በልፊያ እየገፋ
እንደአቃቢት ግብር ውሀ፥ ገበና የትም ሲደፋ፣!...
ብቻ ጡሩ የግፍ ግፉ
ከበባደልም በደል ዕድፉ
ከቶም ረቂቅ ሽል መቅጠፉ።

ገና በቆባው በእምቡጡ
ቡቃያው ከማቆጥቆጡ

ገና በሽል ገና ባፍላ
ዓይኔ ከዓይንሽ ብሌን ጥላ
የቋጠረው ወዝ ሳይሞላ

ሕልሜ ብልጭታው ሳይጠራ
ጭላንጭል መቅረዝ ሳይበራ

ሲቃዬ እስትንፋሱን ሳይረጭ
ደሜ፥ የልቤ ፅንስ አንጭጭ
ምነው ሳይፈጠር ይቀጭ?

በመዳፍሽ የጠለለው፥ የዕንባ ወዜስ ይምከን፥ ይምጠጥ
የብሌንሽ ወላፍን እጭ፥ እርግብግቢቱ እንዴት ይፍረጥ?...

ለካስ በቄጠማ ነዶ* ዕርግብ ፍሳፃ ደብቃ
በንሥር ልቦና መጥቃ
ሕዋሱን ደባብሳ አድቅቃ
አለሳልሳ አማቅቃ

አምናት ሲታበይ ነበረ

ያ በሞገድ ድባብ መጥቆ፥ ሁሉን ቁልቁል ያተኮረ
አናምርትን ነጌያትን፥ እንስሳትን ያሸበረ
አእዋፍን በደመና፥ አውሬን በደን ያስገበረ
በነበልባል አክናፋት ጦር፥ ያየርን ሰርጥ የሰበረ
የየብስ የአድማሳት ገሞራው፥ ያ እንደ ጋሬጣ የሾረ

ፍላፃ ዓይኖቹን ታውሮ
ርቱእ የጦር-ጥፍሩን ነፍሮ
አውራ-ገነን ከብሩን ከስሮ
ቅስሙን ውጦ፥ ባክኖ አፍሮ
ኩፍ እንዳለች ዶሮ፥ ጓሮ
ሊለቅም ግብሰብስ ጭሮ

የጀግና ሐሞቱ ታልቦ
ገሞራነቱ ተሰልቦ...

አምኖሽ ሲታበይ ነበረ
የየብስ ያድማሳት እሳቱ፥ ያ እንደ ጋሬጣ የሾረ
ፍላፃ ዓይኑ የታወረ
ርቱእ ጥፍሩ የነፈረን
ዓሞራነቱ የከሰረ?

ለአበራ በነበር - (፲፱፻፶፮ - ጉለሌ)

# የብዕር አሟሟት ሌላ

የቃለ-ልሣን ቅመሙ

የባለቅኔ ቀለሙ

ነጠበ እንጂ ፈሰሰ አንበል*፥ ቢዘነበል እንኳ ደሙ

ሰከነ እንጂ ከሰለ አንበል፥ ቢከሰከስ'እንኳን እፅሙ

የቃለ እሳት ነበልባሉ

አልባከነምና ውሉ

የዘር-ንድፉ የፊደሉ

ቢሞት እንኳን ሞተ ኣአትበሉ።

እስካልተዳፈነ ፍሙ

እስካልተሰበረ ቅስሙ

እስካልተቀበረ ሰሙ

የደራሲ ዐፅመ-ወዙ

የብዕር ቀስተ-መቅረዙ

ሕዋሳቱ እስካልቀዘዙ

አልፏልና ከሥጋ-ሞት

በቃሉ ሚጠት ሰልባቦት

በፊደሉ እድማስሰ-ፍኖት

በኅብረ ቀለሙ ማኅቶት

በሥነ-ግጥሙ ምትሃት

በግሦ ንጥረ-ልሳናት

በነባቢቱ ነፍስ እሳት

ይነዝራልና ደም-ሥሩ፥ አይሞትምና ፀዳሉ

ቢሞት እንኳ ሞተ አትበሉ ....

የብዕር እሟሟት ሌላ፥

ሲፈስ የብሌኑ ኬላ

የፊደል መቅረዝ አሟሟት

ከውስጥ ነው እንደጋን መብራት

በቁም ነው እንደቁም ፍትሐት

የሚያጨልም የነፍስ እሳት፥

እንጂ ብዕር ሞተ አትበሱ፥ እሳቱን ሳያስለመልም

ነበልባሉን ሳያከስም

ውጋጋኑን ሳያጨልም፤

ቃለ-ምንጩን ካልመሰነ፥ ሥለቱን ካልጐለደፈ

መቅረዙን ካልተዳፈነ፥ ከፊደሉ ካልነጠፈ

ዐፅመ-ወዙን ካልደረቀ፥ ጧፉን ቀልጦ ካልሰፈፈ

ጡጦ እንደጠፋበት አራስ፥ ቁም ተዝካሩን ካልለፈፈ

ብዕሩ ቀርቶ ምላሱ፥ በሃሜት ካልተንጠፈጠፈ፤

የቃስ-እሳት ነበልባሉ

የድምፀ ብርሃን ፀዳሉ

የኀብረ ቀሰማት ኃይሉ

አልባከነምና ውሉ
የዘር-ንድፉ የፈደሉ
ቢሞት እንኳን ሞተ አትበሉ።

ለካሣ ተሰማ - (፲፱፻፶፱ - ቆቃ)

# ክልስ - አባ - ልበ - እግረኛ

ከብቸኞችም ብቸኛ
ያንድ ሃሳብ-ግዞት-ቁራኛ
ከግለኞችም ግለኛ
ክልስ አባ-ነፋሱ-አትተኛ
የመንፈሰ-ራብ ግዞተኛ

ባክኖ በእምነት ፈለግ-እርከን
የወዳጅ ተፋፊው ዘላን፤

ክልስ የእምነት-ምስኪን ድንዝዝ
ግንጥል የቂም-ቁስል ምርቅዝ
ግንዝ፥ ክልስ ፍቅረ ግንዝ፤
የበቀል ነፍሰ-ጡር ትኩዝ
ግልል ያገር ሕመም ግዑዝ

ብቸኝነት ያስጨከነው
ያም ያን ሲለው ያም ያን ሲለው
ከብቸኛ ልቡ ሌላ፥ ወዳጅ ያለው የማይመስለው፤

ከቆዳው ወይ ከምላሱ
የማይረሳለት ድጉሱ
ከሁለት ዘር መታመሱ
ከሁለት ደም መደገሱ፤

ያየኝ አስታወሰኝ ብሎ፥ የነፍሱን ቁስል ደብቆ
በሥጋና በወዝ ቀርቦ፥ በውሰጠኝነቱ ርቆ
በግለኝነቱ ማቅቆ
ከሁለት እንደወደቀ፥ ነፍሱን ከነፍሱ አስተራርቆ

አንዳንዴም ልቡን አግዞ
አንዳንዴም ቂሙን አርግዞ

ያቺን የሰው እምነት ራቡን
የብቸኝነት እርቃኑን
በአድማ የተጥሳላች ነፍሱን

ተገንጥላ እንደዋተተች፥ በእምነት ረሃብ ስትገረጣ
ብድሩን ሊከፈልላት፤ እንደተቀጣች ሊቀጣ
በብሩ ወይ በሥልጣኑ፤ የማታ ማታ ሊወጣ

እምነቱ እንደተባዘተ፤፥ ድንጉጥ ባንዳ ሲያነበንብ
እንደቤት-ውልድ የበቀል ልብ፥
ያን የመንፈሱን ቀፎነት፤ በገንዘብ ጠግኖ ሊከብ
እንደጠበቃ በድብቅ፥ እንደሞጃ በከንብንብ፤

አንዳንዴም ባለቤት ሆኖ
በተቆርቋሪነት ገንኖ
ሕዝባዊነቱን አጋኖ
በአደባባይ አስተማምኖ
ሊፈወሰ ሲል ከቂም ድኖ

ባሉ-ቧልታ ምጸተኞች
በወግ ታዛቢ አፈ-ጊንጦች
ተጠልፎ በወጥመዳቸው፥ በሰው ሊቃ ቀለብተኞች

አፍ ላፍ ሲመሰጣጠሩ፥ በፈገግታ በዓይን-ጥቅሻ
በውስጡ ከንፈር ንክሻ
በሱነቱ እንዳይታመን፥ የልብ እርካታ እንዳይሻ

በግንባር እሱን ጠቁመው
ተጠቃቅሰው እሱን ጠቅሰው
በምጸት ልቡን ፈርፍረው
የምሳቸውን አቁሰለው
እንዳላየም ሆኖ እንዲያየው
እንዲያውቀው እንዲያስታውሰው
መለየቱን እንዲለየው፤

ዳግም ለሱው ቁጭተኞች፥ መስለው ቀርበው እንዲያድጉበት
ጸአእምሮው ወይ በገንዘቡ፥ ወይ በሥልጣኑ ሊያውቁበት
ጠላታቸውን ጠላቱ* አርገው ጠሳት ሊገዙለት
ወዳጃቸውን ወዳጁ፥ አርገው ወዳጅ ሊሸጡለት
እምነቱን ሊታመኑበት
ፅድገቱን ሊታደጉበት

ውስጡን ሆድ ለሆድ ሊሰቁ
ለሆዳቸው ሰሳወቁ
እሱ ውሱን መጠበቁ
ለነሱ ልቡን ማውለቁ
የግፍ ድርብ አሳልቋቸው፥ በሱው ስለሚደነቁ፥

ዘንግተውት ወይ አውቀውት
ጎሊናቸውን ሰልበውት

የእምነት ከልሶች እነሱ
በመሆን እንደሚብሱ
ተሸነጋግለው ሊረሱ፥

ያንዱ ርቆት ያንዱ ንቆት፥ ከሁለት ወገን መውደቁ
የዘር ሕመም መነጠቁ "
ስለማይመስላቸው ብቁ
የግል ሕመሙን ሳያውቁ
ጥቃቱንም ላይጠቁ
ስጥቅማቸው አንጂ ለሱ፥0 አንዳችም ሳይጨነቁ

የምጸቱ ሞያተኞች
የኅሲና ጃንደረቦች

መሆናቸውን ሲረሱ
አሱ ላይቀር ማስታወሱ
ጠርጣሪ ሆናበት ነፍሱ፤

አንዱ ስሙን ሲያልከሰከስ
አንዱ ደሙን ሲያቀናንስ
ሌላው ቅስሙን ሲያከሳክስ፣

ከልሱን እንደዘር-ቅዳጅ
የቤት ውልዱን' ፍናጅ-ቅናጅ

ከማለት ሳላይታገዱ፣ ላይቀር ያፈ ልማዱ ጠንቅ
ያም የቆሸቱን ቁስል ሳይድን፤ ከቂም ፅንሱ ላይላቀቅ

አድርገውት ፍቅረ-በድን
ከመንፈሱም ሕመም ላይድን

መለዮው ከቶ ተቃርኖ፥ እውነታው ከቶ ተማጥቆ
ባቀፈው ቂሙን አምቆ

በጣሉት ልቡን-አሙቆ
ሲያርቁትም ባፍ-አጥላልቶ፥ ሲያቀርቡትም ውስጡን ንቆ

ከዓለም ተጣራሪ ጠባይ፥ ያለውዱ የፈለቀ
ከሁለት ዛፍ የወደቀ
አንድ የጣለው ካንድ የራቀ፣

ከልስ አባ-ልበቡ-እግረኛ
ያንድ ሃሳብ-ግዞት-ቁራኛ
ከግለኞችም ግለኛ

የወዳጅ ቀፋፊው ዘላን
ባክኖ በእምነት ፈለግ-እርካን

ያም ያን ሲለው ያም ያን ሲለው
ብቸኝነት ያሰጨከነው....
ያለግዞትኛ ልቡ፥ ወዳጅ አለኝ የማይለው፤

ክልስ ግዑዝ
ክልስ ትኩዝ
ግንጥል የቂም ቁስል ምርቅዝ
ግልል ከልለ ፍቅረ-ግንዝ

የመንፈስ-ራብ ግዞተኛ
ከግለኞችም ግለኛ
ከብቸኞችም ብቸኛ...
ከልስ-አባ-ልበ-እግረኛ።

ለማዳም ሄለን ደጉ ወልደ ጊዮርጊስ - (፲፱፻፷)

# መውደድ አባ ጸጸት

ዋሽቼ እንደነበር፥ ምነው ባወቅሽብኝ
ጉዴን ባየሽብኝ።

“በቃኝ” ስልሽ ጮኬ፥ መርሬ አማርሬ
አርሬ አሳርሬ
"አክ እትፍ!' ስልሽ፥ ስተፋሽ አንቅሬ፥

ምነው ባወቅሽብኝ
ጉዴን ባየሽብኝ።

“ዱታው ዘራፍ" ስልሽ...
ግነን በኝ" ሰልሽ፥
ወይ አለማየትሽ

ወይ አለማየቴ
ባላንጣ እንደሆነኝ፥ የገዛ አንደበቴ፥

በገዛ ልሳኔ፥ ያንጀቴን ማነቂ
ወይ አለማወቅሽ፥ ወይ አስማወቂ...

ለካስ አፍ ባዳ ነው፥ የልብ እውነት ደፍኖ
የላንቃን አጋኖ
ያንጀትን አባክኖ...

በቃ እንግዲህ በቃን፥0 አንቺም ሽር እኔም ሽር
አንቺም ብር እኔም ብር፥

አንቺ ቢል!
እኔ ቢል!

አንቺ እርር!

እኔ እርር!
ዕድሜ ድንብር ግትር
“ሳይቸግር ጤፍ ብድር" ።
እውነት ያፍ አፍ ሆኗል፥ የልባችን ይቅር።

“ብጥስ ቅንጥስ ነው! ታድያስ! እረ ንሳ!
“ወጉስ-ማዕረጉሳ!”....

ሆኖስ ምን ተረፈን?
ሆያ ሆዬው ብቻ፥ ፋንፋሩ ጨረሰን፤...

ተስፋ መፍለቅለቋ፥ ከነምንጩጪ ሲበልዝ
ነፍስ እርግብግቢቷ፥ ከደም ሥሯ ሲቀዝ

ሕልማችን ከዋዣ፥ በሕሊናችን ከስ
ዓይን ያይን ዓዋጅ ነው፥ አንጀታችን ያልቅሰ።
የገደል ማሚቶው፥ አፍ በተነፈስ
“ክብሬን ነክቶ!" ብለን፥ ልጅነት ፈረሰ።
እውነት ደፈረሰ
“ዳቦ ተቆረሰ"
እውነት ያንጀት እውነት፥ እንቆቅልሽ ሆነ
እንደ ዓመድ በነነ፥
ያለእምነታችን ባሕል፥ ጊዜ ያስአሳዳጊ
የሰማሽውን ነው፥* 'ሆዴ ምን ታረጊ፡'...
ወሬ ካሸነፈን
ጉራ ግርግሩ፥ 'ኤክሰፓው' ይማርከን?
ጠፋን ላሉ ቧልታ
ለይሰሙላ እምቢልታ?...
ተሸጠ እንደ ተረብ
በቧልት ሊነበብ

የነፍሴ የነፍስሽ፥ ገበና ታተተ
በመበለትና፥ ባዋጅ ተተረተ
አንቺም የኔ እፍታ፥ ወዝሽ ተጨለፈ
አበባሽ ረገፈ
ልጅነት አለፈ
መውደድ አባ ጳጳት*0 በዕድሜ ተቆለፈ
ጠኖ፥ ጐስደፈ
ጫጨ፥፤ ገረጀፈ።
መውተርተር ተረፈን+ ቢያስጠቃም ቢያስከፋም
እንግዲህ ልጅነት፥ ተመልሶ አይመጣም።....
"አልወድሽም ያልኩሽ፥ ውሸቴ ውሸቴ"
ላይሽ ብንን፥ ብንን ይላል አከሳቴ"
ሳጣሽ እርር ኩርምት፥ ይላል ሆዴ እንጀቴ፥...
ወይ አጉል እርግማን፥ ወይ ከንቱ መገደር
ያንጀቴን ቀብሬ፥ ያፌን ብቻ ነበር፥...
ወይ በነቃሁብሽ ፥ ወይ በነቃሽብኝ
ዋሽቼ እንደነበር፥ ምነው ባወቅሽብኝ
የሆድሽን ባየሁት፥ ሆዴን ባየሽብኝ።

፲፱፻፶፪ - ሁሉቃ

# መተማን በሕልም

መተማ የጎንደር ዘማች

ተቸግሮ በሕልም አፋች

ትርጉሙ ተወሳሰቦበት

የሄሮድስ ልጅ ሰሎሜ፥ ተገልጣ ገለጠችለት።

እንዲህ ስትል:

“ሟች የገዛ ሕልሙን ሥዕል

ቀን እያስታወሰ ሲስል

ትርጉሙን መፋጠጥ ባስቶ፥ ያልመሰሰው እንዲመስል

ሐቁን በተሰፋ ሲያጣጥል

ቆሜ እሻል ሞቼ እሻል እንዲል፥

እንደሞት ሁሉ ላንድ ሞት፥0 መተማ ሁለት ፊት ትግል

ያንዱን ዕድል ለሌላው ድል

ለታሪክ ኅሊና ቁስል

በዕድሜ ምዕራፍ ሰታዋውል፥

ሐለስተ-ዓዶት መተማ

ጊዜ ባንቺ ቀን ታድማ

ነጋ-ጠባ ስታቅማማ

ደማች የፋሲል ከተማ።"....

ከራስ ዳሽን አድማስ ግርጌ፥ ከዞበል መቃብር ማዶ

መተግ የተኛ ዘንዶ

ተምዘግዝጎ ጠረፍ ንዶ

እንደሰሎሜ ምሳሌ፥ እንደሄሮድስ ሴት ልጅ ሽንጥ

በኖባ ተራራ ጥምጥም፥ ሠራ-አካሱን ቢያንቀጠቅጥ

አርበድብዶ ቢያቅበጠብጥ ሌ

ጎንደር ይዚት የብቻ ምጥ፥

አዋላጂቱ ሰሎሜም፥ ሰቧት የግዝፈቱ ግርማ

የመጥምቅ ደም ብትጠማ

የጂሃድ ሰይፍ ኣቅዘምዝማ

ዮሐንስን በመተማ

ባረከች ፋሲል ከተማ።

ኀለተ-ዝሙት ሰሎሜ

አድራ ከደርቡሽ ቅማሜ

ከቅንዝር በቀል ሰያሜ

ምሰለ በለሰ የእንሰት አሣች

ሕልሙን ለጎንደር ሰው ዘማች

መቅደሳ ላይ ፊት ያማታች

በመተማ ቆርጣ ፈታች።

፲፱፻፷፪ - እንዳሥላሴ

# በቃኝ

በቃኝ የኑሮ አጉራህ ጠናኝ፥
እፎይ የዕድሜ-አዚሜ ጠራኝ።
አስለመለመ ሙብራቱ
በሕይወት የመዋተቱ
ከነጉነግ መንከራተቱ
መንከሳወሱ ልፋቱ....
መከሬ ሻማዋ ጠፋ
መሸ ቀኔ ሳንቀላፋ።
የዕድሜ-ጀምበሬ ጠለቀች
ቅድመ-ፍጥረቴ አሸለመች
ልደቴ ተረመረመች
ተጭለመለመሙች በበርኖሰ
እንደጭጋግ ዶፍ ጥቀርሻ፥ ተዳፍና የዕድሜዬ ፋኖሰ
ጠራኝ፥ የዕድሜ አዚሜ ጠራኝ
እኔም በቃኝ እፎይ በቃኝ፥
መሸች ጠለቀች ፀሐዬ
የሕይወት ከረምቴ ወጣች፥ ጉም ተሳበሰች ጥላዬ
እረፍቷን ተከናነበች፥ ተሰለመለመች ዕጣዬ፥
በቃኝ ትግሌን ተገሳገልኩ

ውጣ ውረዴን አከተምኩ
እፎይ ደከምኩ አሰለመሰምኪ...
ተሸነፍኩ ኣዎን ተሸነፍኩ፥
የከበደኝ ጣር ቀለለኝ
ያታከተኝ ያደከመኝ
ያሰለቸኝ ዕድሜ ተወኝ
እፎይ ቀለለኝ ቀለለኝ...
ባለወር ተራ ተተካ
ተቀበለኝ ትግሌን እንካ፥
ማነህ አንተ ባለሳምንት
ያስጠምድህ ባስራ ለድስት
በዕድሜህ ያሰጠምድህ...ወይኔ
በልደትህ ያስፈርድህ....መጥኔ
ለኔስ መሽቶልኛል ቀኔ።
በቃኝ የኑሮ አጉራህ ጠናኝ
እፎይ የዕድሜ-አዚሜ ጠራኝ።

ለኢታፋ ዋላጋ - (፲፱፻፶፰)

# ቦረን (የሃዩ አላኬ ሊበን ቀረርቶ)

ዳምባል! ጋላልቻ ሬሮ!

ኢማጂ ዲና! አባ ጋናሌ!

*ዳምባል"' አለ

(የህሪያውን' - የዕድሜ እኩያ ጓዱን ስያሜ ነው)

ዳምባል! እንዲያው በስመ ዳምባል

የከረምቱን ጐርፍ አይደል...

የዘንካቶቹን እንጂ

የአሬሮን ምንጭ ቅጂ

የነጋላልቻን ቅጂ!

የዲናው መቅሠፍት እሳት

ዱታው የነጉዮ አባት

ዳምበል! ድምፀ አባ ሮሮ

እንደምንሸር አምሮ

ሸንቃጣው ግዳይ-ጣሌ

ሮሮዬም እንደቃሌ

ዳምባል! አባ ጋናሌ!

መልሼ መላልሼ

ደጋግሜ አሠልሼ

ደጋግሞ ገዳይ ሾጤ

መላልሶ ጣይ ሰተቴ

ብላ ወልዳኝ እናቴ

ዳምባል ገደል-ከሣቴ!

እንደአይጥ ፈፋ ምሶ

እንዳይሞት ትቢያ ልሶ

ሲቀር በጉዲፈቻ

ነበር ያረኩት አቻ።

ዳምባል! የሚያውቅ ይወቀኝ

ወትሮም የቦረን እሳት፥ እምሰኘው እኔ ነኝ

የሚያውቀኝ ወትሮም ያውቃል፥ ዱታው የነዲና ጣር!

የማያውቀኝ ያው ይማር

ያውሬን ጭለማ ጠለል

የደኑን ዋሻ ገደል

መንጥሮ-ገባን ዳምባል!

ባንዲት መካን ሲት ኩራት

አልሰማ ብዬ ጥቃት

የቆንጨሮ ፍም እላት

ሌሊት ጀምበር ሳትወጣ

ገባሁት በጨበጣ!

ጨረር ሳትቀላ በደን
በዋርሲቱ ልጆች ቀን
የሰባት ጓድ ሁለት ረድፍ
ጭሰማ ለብሶ ሲከንፍ
እኔ የመቅሰፍት እጁ
ከነጐልማሳ ልጁ
ተግ ሲል እንዳየሁት
በገዛ ደሙ አጠብኩት!
ስመለሰ ቀን ሳይነጋ
ብቻውን ካውሬ መንጋ
ጥንድ አውራሪሰ አድፍጦ
ቢጋፈጠኝ አፍጥጦ
በከረዮ ሴት ኩራት
አልኖር ብዩ በጥቃት
ቤቴን በረቴን ትቼ
ሎጋ ጦሬን አንግቼ
በዳምባል ሰም እንደማልኩ
ኮርማ አውራሪስ ተንተራሰኩ።
ሸንቃጣው ግዳይ-ጣሌ
ዳምባል አባ ጋናሌ!

ዳምባል! ሮሮምሳ ዲራ!

ዳምባል! ጋላልቻ ሬሮ!

ኢማጂ ዲና! አባ ጋናሌ!

ለአሥመሮም ለገሰ - (፲፱፻፷፪ - ሊበን)

# ዋ! .... ያቺ ዓድዋ

ዋ

ዓድዋ ሩቅዋ

የዓለት ምሰሶ አድማስ ጥግዋ

ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ

ዓድዋ ....

ባንቺ ብቻ ሕልውና

በትዝታሽ ብፅዕና

በመስዋዕት ክንድሽ ዜና

አበው ታደሙ እንደገና...

ዋ!

ዓድዋ የዘር ዐፅመ ርስትዋ

የደም ትቢያ መቀነትዋ

በሞት ከባርነት ሥርየት

በደም ስነፃነት ስለት
አበው የተሰውብሽ ለት፤
ዓድዋ
የኩሩ ትውልድ ቅርስዋ
የኢትዮጵያነት ምስክርዋ
ዓድዋ
የኩሩ ደም ባንቺ ጽዋ
ታድማ በባመዘንበልዋ
ዐፅምሽ በትንሣኤ ነፋስ
ደምሽ በነፃነት ሕዋስ
ሲቀሰቀስ ትንሣኤዋ
ተግ ሲል ሲንር ትቢያዋ
ብር ትር ሲል ጥሪዋ
ድው-እልም ሲል ጋሻዋ
ሲያስተጋባ ከበሮዋ
ሲያስገመግም ዳኘው መድፍዋ
ያባ መቻል ያባ ዳኘው
ያባ ነፍሶ ያባ ቃኘው
ያባ በለው በለው ሲለው
በለው-በለው-በለው-በለው!

ዋ! .... ዓድዋ ....

ያንቺን ጽዋ ያንቺን አይጣል

ማስቻል ያለው ኣባ መቻል

በዳኘው ልብ በአባ መላው

በዝበየሁ በአባ ጐራው

በአባ ነፍሶ በአባ ቃኘው

በለው ብሎ፥ በስው-በለው!

ዋ! ... ዓድዎ ....

ዓድዋ የትላንትናዋ

ይኸው ባንቺ ሕልውና

በትዝታሽ ብፅዕና

በመስዋዕት ክንድሽ ዝና

በነፃነት ቅርስሽ ዜና

አበው ተነሡ እንደገና።

.... ዋ!? ....'ያቺ ዓድዋ

ዓድዋ ሩቅዋ

የአለት ምሰሶ አድማስ ጥግዋ

ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ

ዓዋ ...

የካቲት - (፲፱፻፷፬ - ዓድዋ)

# ሕይወት ቢራቢሮ

ቢራ ቢሮ ከአበባው ላይ፥ ምን አይተሽ ነው ከቅጠሉ
ከቂጠማው፥ ከለምለሙ፥ ሰምረሽ፥ አቅፈሽ መመሰሉ
ስለምንድነው ቢራ ቢሮ
አባባሽ ከአበባው ሥምሮ፥
በፀደይ ከዐደይ ጋር ፈክቶ
በርቶ* ተጥለቅልቆ ደርቶ
እንደ ጮራ ተንዥርግጐ፥ በመንጸባርቅ ተንጣሎ
ዘደይ አክሎ ፀደይ መስሎ
ውሎ፥ .... ኋላ ቀኑ ሲመሽ
ፀሐይ ግንባሯን ቀልሳ፤፥ ከጭለማ ክንፍ ስትሸሽ
ብርሃኗ በሌት ተዳፍኖ፤ ዓይኗም ፈገግታዋም ሲሰንፍ
አዝርእቱ እርጭ ብሎ፥ ጸጋውን ከመልኩ ሲገፍ
ምን አይተሻል ከቂጠማ፥ ምን አይተሻል ከለምለሙ
አስተምሪኝ ቢራ ቢሮ፤ ሰው ለመባል አሰኝታዬ
ቀድሞ የት ነው መነሻዬ
ሲመሽ የት ነው መድረሻዬ? ....
ሲተረትማ ሲወጋ፥ ከየብልጭታው ውጋጋን
አበባው ምድሩን ሲንተራስ፥ ያፈር ጽዋ ዕረፍቱን ሲገድፍ

ቢራ ቢሮ ያንቺስ ሞገስ፥ ለምንድነው አብሮ እሚረግፍ? ...

ቀን አብረሽ አብበሽ ውለሽ፥ ሲመሽ አብረሽ መሰለምለሙ? ...

የሰው የአራዊት የአእዋፍ፥ ውሰብሰብ ነገደ ጉንዳን

ሲነሣ ሲሮጥ ሲደፋ፥ ሲያጋድል ሲያዛባ ሚዛን

በማይመጠን ታላቅ ኃይል፥ በተፈጥሮ ግዙፍ ሥልጣን

ሊፍተለተል ይወለዳል፥ ሳይነቃ ይወድማል ይባላል

ልደቱ ዕድሜና ሞቱ፥ አለማቋረጥ ይጓዛል፥

ይኸ ይሆን አልፋ-ኦሜጋ? ይኸ ይሆን አስቀድሞ ቃል? ...

ያንቺሳ ምሥጢር ምንድነው፥ ቢራ ቢሮ አንወያይ

አንቺ የዕፀዋት አዋዋይ

ከፀደይ ጋር ፀደይ መሳይ

ከአበባም አበባ መሳይ....

ምን አለበት ላንዲት ሰሞን

ቢራቢሮ እኔ አንቺን ብሆን

በፍስሃሽ ብጥለቀለቅ፥ ብነግሥባት ባንቺ ጽዮን?

ጸጋ ሞገሰሽን ለብሼ፥ እኔ ባንቺ ሰም አልፌ

እኔ ባየርሽ ሰፍፌ

እኔ በአክናፍሽ ከንፌ

ምን አለበት ቢራ ቢሮ፥ .... አንቺ ቀለም ለበስ ቅጠል

የብርሃን ጮራ ጠለል

ተወርዋሪ ሚሳይ መሰል፥

ምነ አለበት ቢራ ቢሮ፥ ዕድልሽን አኔ ብታደልገ ...

ትንኞች፥ ዝንቦች ያሙሻል

ወረተኛ ነሽ ይሉሻል፤

ከአበባ አበባ መክነፍሽ

ከፀደይ በጋ መዝለቅሽ፥

ከሾህ፥ ከጉድፍ ሰትስቂ

ከየሰንጥሩ ሰትወድቂ

ስትሳዳሪ፥፤ ወግ ስትነጥቂ

እያወቅሽ እንዳላዋቂ

የወረት ነው ብለውሻል፥ ቢራ ቢሮ ተጠንቀቂ።

ያበጋው እንኳ ግድየለም፥ የህጋይ አሰድ እሳቱ

ቢያነድሽ፥ ቢያከነፈንፍሽ፥ ቢያጤንብሽ ትኩሳቱ

ተፈታትኖሽ ነው ፍትወቱ

አለውልሽ መዋተቱ

ከጉድፍ ጋር መጋጨቱ።

ምነው ታድያን ቢራ ቢሮ፥ በዝንቦች ወራት በበልጉ

አበቦች ሲጠወልጉ

መሰኩ ቦዘን ሲከናነብ፥ በትንኝ ጪስ ሲታፈን

አረንጓዴው ሲገረጣ፤ ያሸበረቀው ሲሸፈን

ፀሐይ የኀዘን ማቅ አጥልቃ፥ በጉም በርኖስ ስትዳፈን
አንደ ደሰታዋ ጊዜ*፥ መከራዋን ሳትካፈይ
ጭንቋን አብረሽ ሳትቀበይ
ከትንኝ ጋር ስትጋፊ*፥ አልቀመጥ ብለሽ አርፈሽ
ይኸው አጉል ስም ተረፈሽ።
ቢራ ቢሮ ተናገሪ፥ ሞያው እንዲህ ነው ባንቺ ዓለም
ከፀደይ የፀደይ ቀለም፥ ከበልግም የበልግ ቀለም
ከአበባውም፥ ከጉድፉም፥ ከትንኙም መስሎ መግጠም?
ለካ እንዲህ ነው ያማርሽባት፥ የሕይወትን አገም ጠቀም
ቢራ ቢሮ ሆኖ አማይበር፥ ፀደይ ሆኖ የሚዘልቅ የለምየገ!
ላንቺ ይብላኝልኝ እንጂ፤ ለኔስ ክረምት ደረሰ
በሰማያት ዕንባ ምድርን፥ዐ ሊጠርግ እያኀበሰበሰ፥
አበባውን እንደጉድፍ፥ ጉድፉን ከዝንብ መር ሲያስስ
ሁሉን እኩል ሲያግበሰብስ
አጥርና ጐጆ ሲድስ
ሜዳውን በደለል ሲምስ
ግንዱን በዶፍ ሲገረስስ
ክረምት አያ እናት እይምሬ፥ ማመዛዘኛም የለህ ወይ?
ጉድፍ፥ ጽጌ-ረዳ፥ ዐደይ
ማንንም ከማንም አትለይ?

አየን የሁሉ እኩል ቤት ወግ
መደምሰሰ፥ መገርሰስ፥ መጥረግ!
ቢራ ቢሮ እንዴት ነበር፥ ያንቺስ የክረምቱ ውሎ?
መቸስ ለይቶ ፈጥሮሻል፥ ከሁሉ አድረሽ ኑሪ ብሎ
የመመሰል ሞያ ከኖ፥ የመጠጋት አቅል አድሎ ....
ከረምሽ አሉ እንደ ሴት ወፍ
ተለትመሽ ከቤት ከፈፍ፥
እንደ ግንደ-በል ምሰጦች፥ ከምሰሶ ተገን መግባት
በየጣራ እንደ ሸሸረሪት* በምድጃ እንደ እሳት እራት
ዕድልሽ የዋዛም አደል
ከፉ ፈተና ነው መምሰል ....

በርቺ እንግዲህ ቢራ ቢሮ፥ ክረምት ሳንች ብቻ አለፈ
መስሎ አሳድር ያለውማ፤ በጐርፍ ዘቅጦ ጐረፈ
ለካ ምሥጢርሽ ይኸው ነው። በቃኝ እኔም አልሳሳት
ሲነገር እንደሰማነው፥ ከየብልጭታው ውጋጋን
የስው* የአራዊት* የአእዋፍ፥ ውስብሰብ ነገደ ጉንዳን
በማይመጠን ታላቅ ኃይል፥ በተፈጥሮ ግዙፍ ሥልጣን
ሊፍተለተል ይወለዳል፥ ሳይነቃ ያልፋል ይባላል
ልደቱ ዕድሜና ሞቱ፥ አለማቋረጥ ይጓዛል

ይኸው ነው አልፋ-ኦሜጋ? ይኸው ነው አስቀድሞ ቃል?

በኅሊና መሳከሩ፥ ሳይሆን የቆሸት ሕመም ማብቀል

በአለብላቢት መለብለቡ፥ ልቦናን በሣግ መቀቀል

ይሁን ያለን ዲበቡኩሉ፥ የኑሮ ግማደ መስቀል

ለካ እንዲያው ነው መርበትበቱ፥ ሥራ ቃሉ ላይነቀልገ

....

በይ ብር በይ ቢራ ቢሮ፥ ክረምት ላንቺ ብቻ አለፈ

ሌላው በጐርፍ ጐረፈ

ሞተ፥ በተኛበት ረጋ ....

ፀደይ ላንቺ ብቻ ነጋ

ሸር ብለሽ መንቆጥቆጥ ነው፥ ከዚያም* ከዚያም፥ ከዚያም ሠምሮ

አወቅሁብሽ* ነቃሁብሽ ፥ አንቺ ሕይወት ቢራ ቢሮ ...

ቀናሁ መሰል አንች ወላዋይ?

ነይ ብር በይ እንወያይ

ኣንቺ የዕፅዋት አዋዋይ -

ከፀደይ ጋር ፀደይ መሳይ ፡

ከአበባም ኣበባ መባይ ...

ምን አሰበት ሳንዲት ሰሞን

ቢራ ቢሮ እኔ አንቺን ብሆን?

፲፱፻፷፩ - ስድስት ኪሎ

# መሸ ደሞ አምባ ልውጣ!

አምባ ወጥቼ እኩለ-ሌት፥ ስለት ገብቼ በስሟ
ከርሞ ስይጣን በሷ አስቶኝ፥ ልገላገል ከሕመሟ
ጠበሏ አፉፍ በጨረቃ፥ ደጋግሜ፥ ማሕሌት ቆሜ
ሆዴ ቃትቶ ባር ባር ብሎ፥ እርቃኔን ከሷ ታድሜ
ደጃ ሰላሟን በአራት እግር፥ ተንበርክኬ ተሳልሜ
በሥጋዬ እሚነደውን፥ በጸሎት ላቤ አጣጥሜ
እፎይ ብዬ አመስግኜ፥ ውዳሴዋን ደጋግሜ ....
ገና ከደጇዋ እልፍ ሳልል፥ ደሞ ይምጣ የቁም ሕልሜ?
ሌት በጥምቀቷ የነጣው፥ ነጋ፥ ደፈረስ ደሜ።
ለሷ እንጂ ለኔ አልያዘልኝ፥ አዬ የስለት አታምጣ!
በውጣ ውረድ በጠበል፥ ባሣር ወዜ ቢገረጣ
ልክፍቷ እንደሁ አልለቀቀኝ፥ መሸ ደሞ አምባ ልውጣ!

፲፱፻፵፯ - ቢሾፍቱ

# ማነው .... 'ምንትስ'ገ

ያው መቸም እኔም እንደሰው

አንዳንዴ፥ አንዳንዴ ብቻ፥ ሕሲናዬን እውነት ሲያምረው

ሰብሰብ ብዬ እማሰበው

“ቀድሞስ ቢሆን ለኔ ብጤ፡-፥ ለኔ ብጢ የሔዋን ዘር

አዳሜ በኔ ላይ በቀር፥ ለኔ መሰክሮ አይናገር"

ብዬ ከልቤ ስማከር

እኔው ከኔው ስከራከር

ተጨብጬ እማብላላው

ያው መቸም እኔም እንደሰው

የሐቅ ራብ ነፍሴን ሲያከው

ልቤ ልቤን ሲሞግተው ....

“እውነትስ ምንትሰ ማነው?"

እያለ ነው። ....

ያም ሆኖ ነገሬ ከልብ

ያልወጣ ነውና ለሕዝብ

ለማንም ያልተገለጠ፥ የራሴ ድብቅ ሱባዔ

ልቤ ከልቤ ጋር ብቻ፥ ያረገው የዝግ ጉባዔ

ከቶ የናንተን ዳኝነት፥ አልጠይቅምና ስሙኝ

ፋይል ከፊቾ እንዳትሉኝ። ....

ያው ብቻ በዘልማድ ሕግ፤ በእንቶ-ፈንቶአችሁ ልረታ ....

እውነቱ ከእውነት ተፋጭቶ፥ ሐቅ ሆኗልና ሽውታ

ስለዚህ አንዳንዴ ብቻ፥ አልፎ ኣልፎ ብቻ ላንዳፍታ

አሳቤም ሥጋዬም አብሮ፥ ትንፋሼም ሲያገኝ እፎይታ

ምንትሶች ለምትሉን፥ የለንምና ጸጥታ

ከዚያ ከሌት ውጣ ውረድ፥ ከቀን መኻታው ድውታ

ላመል ታህል ብቻ ድንገት፥ ለሃሳብ ንቃት ለትዝታ

ገለል ቀለል ሲለኝ፤ ከስንቱ ሆይታና ዋይታ

"ከዳር ዋጋው ካንድ ጊዜው" ከሂሳብ ዛቻው ቆይታ

ከግራ-ማ-ፎን ቀረርቶው ከድም-ድሙ ካካታ

ከሙዚቃው ሆያ ሆዬ፥ ከናላ-ወቀጣው ፋታ

ከዳንኪራው ውትር ግትር

ከመጠጡ ብዥ ድንብር

ትንሽ የሕሊና ሰላም፥ አገኘሁ ስል .... የሚለኝ ቅር

እንደገና ለብቻዬ፥ የልቤን ቁስል የሚያጭር

አለብኝ የሐቅ ብትር

ነፍሴን ከስሶ እሚያከራክር

እንደዛር እሚጐነትል፥ ሐቅ እንድጠይቅ የሚያስጥር፥

ያራቡኝን+ ያጠሙኝን፥ የነሱኝን የሐቅ ዕድር

እንድጠይቅ፥ እንድጠይቅ፥ የሚያረገኝ እርር ክርር
ነፍሴን ከልቤ እሚያሚግት፥ በሐቅ ራብ እስካጣጥር
መንፈሴ ውስጥ የሚያቃጭል
'እውነትስ ማነው ምንትስ?'፥ እስቲ እንጠያየቅ የሚል ....
ሕመም አለኝ፥ ... ይኸም ሆኖ፥ እግዜር ያሳያችሁ ላልል
ለይታችሁ አጥራችሁኝ፤ ከዳኝነታችሁ ባሕል
ከፍርድ አደባባይ ክልል፥
ለኔ ከቶ ላታውቁልኝ ።
ነውር በቀር ላታዩብኝ
ጠር በቀር ላታሰቡብኝ
የሕሊናችሁን በደል፤ በኔ ለምትወጡብኝ
ምንትስ ከማለት በቀር፥ ሌላ ምን ላታስገኙልኝ
መቸም ቢሆን እኔ እናንተን፥ እግዜር ያሳያችሁ ላልል
እዘልቃት እንደሁ ነው እንጂ፥ ከልቤ ጋር ሳብስለስል
ምንም! ቃል ለምድር ለሰማይ
ያሳያችሁስ ብላችሁ፤ አየን ላትሉ አለብካይ ....
መሃላ አለኝ፥ ትናንት እንኳ የእህቴ ልጅ እንኳ ትላንት፥
የሥጋ የዘመድ ያጥንት፥ የደም መተሣሠር ገፍቷት
አገር አቋርጣ ልታየኝ
ልታጫውት ልትጠይቀኝ

ልታዋየኝ ልታቀርበኝ

ችግርሽ ገባኝ ልትለኝ

ከዘመድ ልትደባልቀኝ

የወግ መሰላል ልትሆነኝ

ካገር ልታመሳሰለኝ

አዲስ ዘዴ ልታሳየኝ

እንደመጻሕፍቷ ብርሃን፥ አርቃ ልታሳስበኝ

በመንፈስ ውድቀት እንዳልርቅ፥ በርቺ ልትል ልታቀርበኝ

መጣች ብዬ ሳሳስቃት

ሳጐርሳት ስገባብዛት

ልቤ ፈክቶ ሳዳምጣት፥

የእህቴ ልጅ እንኳ ትላንት

ለካ እሷስ 'ቦይ-ፍሬን' ብጤ፥ 'ዳር-ልግ' እምትሉት ሽቷት

ምሥጢር የሚያመሣጥራት

አሳስቧት አሰኝቷት

የሚያሳውቅ፥ የሚያስተምር፥ ልቦና የሚከፍትላት

ለጊዜው፥ ለጊዜው ብቻ፥ በኔው ቴፕ እያራመዳት

በኔው መጠጥ እያጣጣት

በኔው ሶፋ እያስጠናት
ችግሯን ከተረዳላት
ኋላ .... ደብተር መግዣ እሚላት
አስኘቷት፥ አሳስቧት
ነበር ለካ የደከመችው
ያገርን የወግ ድልድል፥ ድንበሩን የዘለለችው
የባሕሉን የሥርዓቱን፥ ክልል የተሻገረችው
የሥልጣኔ መጽሐፏን፥ ድርሳኗን የዘረጋችው ...
እና አንዳንዴ፥ አንዳንዴ ብቻ፥ እኔው ከኔው ስመካከር
ከልቤ ጋር ስከራከር
ያው መቸም እኔም እንደሰው
የሐቅ ራብ ነፍሴን ሲያመው
እኔንሰ ያሉትን አሉኝ፥ “ግን የእውነት ምንትስ ማነው?"
እያልኩ ነው።
ይህ ነው አንዳንዴ እሚያጽናናኝ
ከሃሰት ሃፍረት የሚያዋጣኝ
ከንፈሩን ለሚመጥልኝ፥ ለሚያዝንልኝ እንዳዝንለት
ከንፈሩን ለሚነክስብኝ፥ በሚያዝንብኝ እንዳዝንበት
ለወረት ይፍታሽ ለሚለኝ፥ ወረት ይፍታህ እንድልበት
በሚያሾፍ እንዳሾፍበት

በሚሰቅ እንድስቅበት

በቀን ለሚንበላጠጡ

በሌት ለሚብለጠለጡ ....

እንደቀንድ አውጣ ሰንኮፈን፥ እንጭጭ ሕሊና ያወጡ ...

የሴቶች አብሮ አደጐቼም፥ ባሎች እየፈረጠጡ

በጭለማ እየወጡ፥ እያዋጡ እየዋጡ

ሁሉም በተራ ከመጡ

በወሬም በማሸቃበጡ

በኔው ሥራ እኔን ሲበልጡ

ሴቶቻቸው ፈንታቸውን፥ ከኛው ጋር ሊበላለጡ

ለይሰሙላ ለወግ ብቻ፥ እኛኑ እያሸሚጠጡ

ስልካቸውን መዋዋያ፥ እያረጉ ቢያሸቃብጡ

ቢሮአቸውን ሱቅ አድርገው፥ እየዋሉ ቢጋለጡ

ያው አልፈው በወረታችን፥ በእንጀራችን ላይ በመጡ

በገንዘቡም በሌላውም፥ ስጦታ እየተሰጣጡ

በምሥጢር ሲቀማመጡ

ባልና ሚስቱ በገሃድ፥ በንግዳችን በገቡብን

ገቢያችንን ወስደውብን

ስሙን ብቻ በተውልን ...

በዚህ ላይ ጩኸታችንን፥ ጭምር ነጥቀው ሲጮኹብን

መልሰው ደሞ ሲያዝኑልን

ለወግ ሲመጻደቁብን ....

ሕሊናቸውን ባይሹት፥ ኀዘን የሚሹት እነሱ

ለሰባት እምነት ሲምሉ፥ በሰባት ምላስ ሲያወሱ

ባንደኛው ሲነካከሱ

በሌላው ሲሞጋገሱ

በሦስተኛው ሲካሰሱ

ሌት ዓይኑን ላፈር ያሉትን፥ ሳይነጋ የሚያወድሱ

እነሱን አርጐብን ጨዋ፥ የሽንጐ የባሕል አዋይ

የሥነ-ሥርዓት ደላዳይ

መራጭ ቆራጭ ቀናን ከአባይ

ጨዋ መሳይ፥ ንጹሕ መሳይ

ከኔ ምንም ሳይሻሉ፥ ደሞ እኔን ምንትስ ባይ!

"ከሌባ ሌባ ቢሰርቀው

ምን ይደንቀው" እንደሚባለው

እኔንም የሚያሰደንቁኝ

ከኔ አንሰው እኔን ሲያወግዙኝ፤

በገዛ ስማቸው እኔን፥ ባፍ ሙሉ ምንትስ ሲሉኝ፤

ይደነቅላቸው እንጂ፥ ያም ቢሆን በቃን ላይሉ

ወኔአችንን ካልበከሉ

በሥጋችን እንደጣሉን፥ መንፈሳችንን ካልጣሉ
ቅስማችንን ልባችንን፥ ሌት-ተቀን ካላቃለሉ
ዓሜን ብለን እስክናምን፥ ምንትስ ነን በሉ እያሉ
ሲያሽቃብጡ ሲያዳልሉ...
ስንቱን በኛ ላይ ማጋፈር፥ ለይስሙላ መካካሻ
ወይ ለንዴት መቀነሻ
ወይ ለበቀል ማስታገሻ
ወይ ለመሃላ ማፍረሻ ....
ኸረ ስንቱ፤ ሞልቶ ስንቱ፥ ብኩን የመንፈስ ምንትስ
ለሥጋውም አብሮን ወድቆ፥ ዳግም በአእምሮው ሲረክስ
በልቦናውም ሲሴስን፥ በሕሊናው ሕግ ሲድስ
'ፍራደሜ' ነው እያለ፥ የኔኑ ደም ሲያልከሰክስ
በቃሉና በመንፈሱ፥ ወድቆ ደቅቆ ሲበሰብስ
ቴህ ወዲያ ማነው ምንትስ!
ከሥጋው ኣልፎ በአእምሮ
ዘሙቶ ወድቆ ተሰብሮ
ከኔ እኩል ለገንዘብ ሰክሮ
በቃልና ባንደበቱ፤ ከኔ ይበልጥ አመንዝሮ
ገበናው እንዳዋጅ ቅዳጅ፥ ከቤት ሾልኮ የትም ሲታይ
ልቅሶ ሳይ ሆነ አደባባይ

ጐረቤት ሆነ ገበያ፥ ቤተ-ታቦት ቤተ-ጠንቋይ

በመኪና ወይ በጫካ፥ በጭለማ ወይ ጣይ ለጣይ ....

ዝም ብንል ብናደባ፥ ዘመን ስንቱን አሸከሞን

የጅልነት እኮ አደለም፥ እንድንቻቻል ነው ገብቶን

ገልጦ ታይቶን ሁሉ ታውቆን

እንጂ፥ አደለም ተሰኖን

ጨዋ እሚባል ማን አለና፥ ደሞ ማን ምንትስ ሊሲሆን፥ ...

አማማና አባባ አንኳ፥ የልቤን የምነግራቸው

ምንም የማልደብቃቸው

አንዳንዴም ሲቸግራቸው ....

ገንዘብ ቋጥሬ ይፔሳቸው

መጦሪያ የሚሆናቸው

ድካምና ሽምግልና፥ ጐረቤት ፊት ባይጥላቸው

ጐጆ ልቀልስላቸው

የግብር ልከፍልላቸው

ሄጄ፥ ዘመድ አዝማድ መሃል፥ ተፈራርቀው ሲመርቁኝ

ጉልበታቸውን እንደሳምኩ፥ ቡራኬአቸውን ሳይሰጡኝ፥

... አባባና እማማ እንኳን፤ ካንድ ልቤ .... እኩል የሚያውቁኝ

ዝቅ እንዳልኩ ሳልነሳ፥ ተንበርክኬ ሲመርቁኝ

እዚያው ተጠቃቅሰው አሙኝ፥

በዓይንና በግንባር ጥቅሻ፥ ከዘመድ አዝማድ ጋር በሱኝ፥

ጉድ ብለው እያስታወሱ

በገጻቸው እያወሱ

ከንፈር እየተናከሱ

በዓይን እየተጠቃቀሱ

የልጅነቴን ሳይረሱ

ከጐረቤቱ መሃከል፥ እነማን እንደለመኑኝ

እምቢ ስልም የሰደቡኝ

እሺ ስል ጉድ-ፈላ ያሉኝ

ወይም ከኔው አድረው ውለው፥ ኋላ ያቹ ምንትስ ያሉኝ

እነማን እንደነበሩ፤ ሁሉንም አስታውሰው አሙኝ፥

በጐረቤቱ መሃከል፥ አንዳችም ወሬ ሳይረሱ

በዓይን እየተጠቃቀሱ

ከግራቸው ሥር ሳልነሳ፥ ቡራኬውን ሳይጨርሱ ....

አሙኝ

ሥጋዬን ከተፉኝ

ከዘመድ አዝማድ ጋር በሉኝ።....

ታዲያን እኔንም እንደሰው

አንዳንዴ፤ አንዳንዴ ብቻ፥ ሕሊናዬን ሀቅ ሲያምረው

ዳኝነት የእግዜር ነውና፥ ልቤን ፍረደኝ የምለው

“እውነትስ ምንትስ ማነው?”

እያልኩ ነው። ....

ግን አንዳንዴ እምዘነጋው፥ ሳሰታምም የሰሜን ቁሰል

አለነሱም የለኝም ብል

ቢያሙኝ ነውና የባህል ....

ምነው በተለይ በነሱ፥ ብቻ ለምን ይቅርባቸው

እያልኩም ነው።

...: ደሞ ያባባም የእማማም፥ አልፎ ቀርቶ ደሞ ዛሬ

እንዲህ የስም ማቅ ለብሼ፤ ነፍሴን ጭምር ተዘክሬ

ተገንጥዬ ተነውሬ

ኣይሰበሩት ሰብራት፥ የሰም ቅጭት ተሰብሬ

ክብሬን አንገቴን ቀብሬ

አንድ ልጄን አስተምሬ

አሰጨርሼ ተቸግሬ

አልፎ፥ 'ግራ-ዱኤት' ሲሆን፥ ደሞ አዲስ ችግር ያሳየኝ!

የሥርጉ ዕስት ከእጮኛው ጋር፥ ጠርቶ እንዳያስተዋውቀኝ

...... ማን ይበለኝ፥ ምን ይበለኝ

ስም አጠረው፥ ሰም አጠረኝ።

እኔን፥ ልጄን፤ ግራ ይግባኝ!

እኔን እናትክን ስም ይጥፋኝ፥

አትጥራኝ አልኩት፥ አትጥራኝ

አታስታውሰኝ አልኩት እርሳኝ ....

ይህም ሆኖ እኔ ልጄን፥ እግዚአብሔር ያሳይህ አልል

ቢከብደው ይሆናልና፥ ማለፍ ከትምህርቱ ከልል

ከሥልጣኔውን ኬላ ደፍ፥ እሱም ከሱ ዘመን ባህል፥

እግዜር ያሳይህም ብለው፥ ቢጥርም ሊያሳየኝ ላይችል

በእውቀቱ ብስለት ተቆርጦ ተበጣጥሶበት የኔ ውል

እንደገና የሱም ዘመን፥ አዲስ ባወጣው ድልድል ....

ታጥሮ የኔ ዕድል ከሱ ዕድል፥

እና ምንም ቢሆን ልጄን

ፍቅሬን የመጨረሻዬን

ስም ያጣልኝን አንድዬን

ባላዋሰኝ ውል እንዳልውል

ያውጣህ እንጂ ከዚህ እክል

ይኸው ቃል ለምድር ለሰማይ፥ እግዜር ያመልከትህ ላልል!

ብቻ እንዳንዴ እየረሳሁት

አንዳንዴ እኔም እንደሰው፥ ልቤን እያስዘነጋሁት

ለትንፋሽ ያህል ለእፎይታ፥ ፋታ ብጤ እየሰጠሁት

ከዳንሱ ዳንኪራ ርግደት

ከሙዚቃው ዋይታ ግዝፈት

ከፍካሬ ኢየሱስ ጥሪ፥ ከፋንፋር ነጋሪት ግለት
ከሃሳዊ መሲሃን ጩኸት
ከነጉግ ማንጉግ መለከት
እኔም እንደሰው አንዳንዴ፥ ልቤን እያስዘነጋሁት
ሕሊናዬ እያመለጠኝ፥ ያ በመጠጥ የሸፈንኩት
በውስኪ እንፋሎት ያፈንኩት
በዕድሜ ቁሰል የጠቀምኩት
ተግ ይልና፥ ብቅ ይልና፥* በገሃድ እያስተዋልኩት
የሐቅ ራብ እንደፈራሁት
ግትር ብሎ ግንባሬ ላይ፥ በቁም እየተፋጠጥኩት
ልቤ ልቤን ሲያማክረው
"በቁም መረሳት፥ መጥፎ ነው!"
እንኳ ቢለው
ዳኝነት የእግዜር ነውና፥ እኔም ፍረደኝ የምለው
"እውነትስ ምንትስ ማነው?"
እያልኩ ነው።

፲፱፻፷፫ - አዲሳባ

# 'እከካም ተማሪ'

አንባቢው ጀመረ፥ ደብተሩን ጨበጠ፥

ገጽ አገላበጠ፥

በቃላቱ ምትሀት፥ ሃሳቡ ተዋጠ፤

አንባቢው ጀመረ፥

እኔም ቢራዬን ያዝኩ+፥ አበባ አየሁ አለ፥

እያሰላሰሰ፥ ይተች ጀመረ፥

ያነብ ጀመረ፥

እኔም ቢራዬን ያዝኩ፥ እየተመቻቸሁ፥

ሃሳቤን ጠቅልዬ፥ እየተጐነጨሁ፥

ትዝታው ፈለቀ፥ እያሰላሰለ፥

አበባ አየሁ አለ።

ታምሜ ተኘቼ-ሆስፒታል ገብቼ

አበባ አየሁ አለ፥

አንዲት ውብ አበባ፥ ሰም ያወጣሁላት፥

ውብነሽ አሰኘቼ፥ ብቻዬን ተኘቼ

አበባየሁ አለ!

አንደእንቁጣጣሽ ቀን፥ እንደመስቀል መዓልት

ስም ያወጣሁላት፥ እንደ አበባ ወራት፥

አበባየሁ አለ። ብቻዬን ተኘቼ፥

ሆስፒታል ገብቼ።

እኔም ቢራዬን ያዝኩ፥ በሃሳቡ እየተያዝኩ

እንደሱ እያስታወስኩ፥ እንደሱ እያስተዋልኩ፥

እንደሱ ትዝ አሰኘ፥ እንኳን እማውቃቸው፤

እማላውቃቸውን፥ ጭምር አስታውሰኘ፥

አበባ አየሁ ሲለኘ፥ ግጥሙን ሲደረድር፥

ቅኔ ሲደረድር፥

እማላውቃቸውን፣ ጭምር ኣስታወሰኘ፥

ቢራዬን እንደያዝኩ፥

እንደሱ እያስተዋልኩ።

እኔንም ትዝ አሉኘ፥ በድምፁ ተሰሙኘ፥

በከንፈሩ ሳሙኘ፥ በዓይኖቹ አልፈው አዩኘ፥

ጕንጬት፥ ጕንጬት እያልኩ፥ እንደሱ እያስተዋልኩ።

እኔንም ትዝ አለኘ፥

እንኳንና እማውቀው፥ እማላውቀው ታየኘ፥

በከንፈሩ ሳሙኘ፥

በዓይኖቹ አልፈው አዩኘ፥

በድምፁ ተሰሙኘ'

ዳባ የሰበሱ፥ አቆማዳ የያዙ፥

በትረ-አሮን፥ መቋሚያ፥ የተመረኮዙ፥

ከከ የወረሳቸው፥ ከቶ እማላውቃቸው፥

በድምፁ ተሰሙኝ፤ በዓይኖቹ እልፈው ታዩኝ፡፡

ደሙ የቆረቆዘ፥ ወዙ የቆረቆዘ፥

በትረ-አሮን፥ መቋሚያ፥ የተመረኮዘ

ዳባ የለበሰ፥ አቆማዳ የያዘ፥

ልብሱ የታረዘ። ዳባ ያጠለቀ፥

በርኖስ ያጠለቀ፥ እከካም ተማሪ፥

አንጀቱ የራቀው፥ በራብ የደቀቀ፥

ታየኝ በአንባቢው ዓይን፥ ግጥሙን ሲደረደር፥

በድምፁ ተሰማኝ፥ ሳመኝ በሱ ከንፈር።

ያ ለማኝ ተማሪ፥ እከካም ተማሪ፥

በሱ ተመስሎ፥ ባንተ ተመስሎ፤

እሱ ኖሯል ኗሪ፥

እሱ ኖሯል ቀሪ።

በኛ ተመስሎ፥ ባንተ ተመሰሎ፥

ዳግመኛ ተፈጥሮ፥ ሁለተኛ በቅሎ፤

እበባው ሲዘራ፥

የግጥም አዝመራ፥

የቅኔ አደባባይ፥ ገበያው ሲደራ።

አንባቢው ቀጠለ፥

እያስላሰለ፥

አበባየሁ አለ!

"ኢዮሃ አባባዬ፥ መስከረም ጠባዩ!"

ዳባ የለበሰ፥ ማጎደር ያነገተ፥

በጭቶ የነከተ፥ በእከክ የነከተ፥

'እኮ ዘተምህረ፥ ይከውን መምህረ'

አንባቢው ቀጠለ፥

አበባየሁ አለ!|

ፊት-ለፊቴም ያለው፥ ጭጭ ብሎ አዳመጠው፥

ዘጉ ቅንድቦቹ

ለዘብ አሉ ዓይኖቹ።

ለሸ እሉ፥ ፀጥ አሉ፥ እርጭ አሉ፥ ተኙ፥

በባሕረ-ሃሳብ ሰጥመው፥ ጠልቀው፥ ቀዝፈው ዋኙ፥

በቁም ሕልሙ ምሥጢር፤ ተአምር ሲናኙ።

ወይስ ለሱም ታዩት?

ዳባ የለበሱት።

ጢማሙ ከጐኑ፥ ዓይኖቹን ቀልሶ፥

በከናፍሩ ጫፍ፥ ትምባሆውን ነክሶ

ተከዝም እያለ፥ ፈካ እያለም ጥርሱ

ያንባቢውን ግጥም፥ ላሚው ከነጢሱ፥

አለ ግን አምሳያ፥ በአንባቢና በሱ፥

ግጥሙን ሲደረድር፤ ሲያነብ አንበልብሎ፥

ባሕር ቅርድዶች፥ የፍቅር ቃጠሎ"

ሲያነብ አንበልብሎ፥ ሲተች ዝግ ብሎ።

ቢራዬን እንደያዝኩ፥ እንደሱ እያሰተዋልኩ፥

ያ ባለአቆማዳው፥ እከካም ተማሪ፤

በዚህ ተመሰሎ፥

በዚያም ተመሰሎ፥

ያ ለማኝ ተማሪ፥ ቅማላም ተማሪ፥

በኔም ተመስሎ፥ እሱ ኖሯል ኗሪ፥

እሱ ኖሯል ቀሪ።

ያ ዳባ ለባሹ*፥ እከካም ተማሪ፥

አለ መሃላችን፥ ከኛ ተመስሎ

ምንተ-ማርያም ባዩ፥ የሌለው ማደሪያ፥

አለ መሃላችን፥ በዛሬው ገበያ

በግጥም ድርድረር፥ በቅኔ ገባያ፥

በአእምሮ መሰተዋት፥ ራሰን በመለያ

ራስን በማወቂያ፥ ራስን በመለኪያ፥

በቅኔ አደባባይ፥ በቅኔ ገበያ

በየአንዳንዱ መንፈስ፥ በየአንዳንዱ ማሳ፥*
ምሥጢር ሲያቆጠቁጥ፥ ተአምር ሲዘራ፥
አደባባይ ቆሞ፥ ገበያው ሲደራ፥
በየአንዳንዱ መንፈስ፥ በየአንዳንዱ ማሳ፥
አለ ያ ተማሪ፥ አለ ያ 'ኮሳሳ'።
ባንተም በኔም በሱም፥ እየተመሰለ፥
አንባቢው ጐን ባለው፥ እየተመሰለ
ሕልም አየሁ በሚለው፥ እየተመሰለ
አንባቢው ጐን ሆኖ፥ እያለሳሰለ፥
ሕልም እየሁ እያለ፥ ትዝ አለኝ እያለ
የልጅነት ገጹን* የልጅነት ወጉን፥
ያን የድሮ ሕልሙን፥
እያለሳሰለ፤
በቅኔው መስተዋት፥ ዛሬ እያስተዋለ
ትዝ አለኝ እያለ*፥ ሕልም እየሁ እያለ።
ከሕልሜ ነቅቼ፥ ያለምኩትን ልነድፍ፥
ልቃኘው ቅዝቴን፥ ላስቀምጠው በረድፍ፥
ከሕልሜ ባንኜ፥ ከእንቅልፌ ነቅቼ፥
እርሳሴን መዝዤ፥ ደብተሬን ዘርግቼ፥
የግጥም ድርድር፥ ገበያው ሲደራ፥

ሲደራ - ሲደራ - ሲደራ-
አሁን ያለምኩትን ከሃሳቤ ላውጣጣ፥
ልነድፈው-ልነድፈው-ልነድፈው ሰቃጣ
ያን የቅዥት ፍሬ፥ ደብተር ላይ ልዘራ፥
ገበያው ሲደራ፥ ጉባዔው ሲደራ
ብዥ ይልብኝ ጀመር፥ ሐቅ አለኝ - አነቀኝ!
አልፈጠር አለኝ፥ አልወለድ አለኝ።
ባምጠው ባምጠው፥ አልወለድ አለኝ!
አንባቢው ጕን ሆኖ፥ እያለላሰለ፥
እያቅበጠበጠው - እያቁነጠነጠው-
እያበሻቀጠው - ሳቡ ችፍ እያለ*፥
እንደዚያ ሲያወጋ፣ ሐልም አየሁ እያለ
የልጅነት ገጹን* የልጅነት ወጉን፥
በቅኔ መሰተዋት፥ ሲያሰተውል ራሱን፥
ያ ባለ አቆማዳው፥ እከካም ተማሪ፥
"እኮ ዘተምህረ ይከውን መምህረ፥
ብዕሲት እእመረት፥ ተማሪ አእመረ፥"
በሱ ተመሰሎ፥ በዚያ ተመሰሎ፥
ዳግመኛ ተፈጥሮ፥ ሁለተኛ በቅሎ፥
ያ ለማኝ ተማሪ፥ ቅማላም ተማሪ፥

በኛ ተመስሎ፥ እሱ ኖሯል ኗሪ፥
እሱ ኖሯል ቋሚ፥ እሱ ኖሯል ቀሪ
ደሞም ጐኔ ያለው፥ ዓይኖቹን አጉልቶ፥
ድምፁን አጕርንቶ፥
ከባለቅኔዎች፥ ራሱን አሰተያይቶ፥
በሕይወት ካሉትም፥ ካሱትም በመንፈሰ፥
“ቻሌንጅ” ነው አለ፥ እንዴት? ከማ ልነሰ?
ራሱን እነጻጽሮ፥ ከነሱ ተዋህዶ፥
ቻሊንጅ ነው አለ፥ ማ ለማን ተዋርዶ?!
ውድድር ነው አለ*፥ መዝኖ፥ አሰተውሎ፥
እኛን ተወክሎ፥ ራሱን ተወክሎ፥
ተማሪውን መሰሎ፥ ተሜም እሱን መስሎ፥
ያ እከካም ተማሪ፥ ያ ዘኬ ለቃሚ፥
ያ ዐርብ ሮብ ጧሚ
ያ በተከሲያን ሳሚ፥
እኛን ተመሰሎ፥ እሱ ኖሯል ቋሚ፥
በአንባቢው ዓይን ያየኝ፥
በግጥም ድርድር፥ በቅኔ ገበያ፥*
በየአንዳንዱ መንፈስ፥ ተአምር ሲዘራ፥
ምሥጢር ሲያቆጠቁጥ፥ ገበያው ሲደራ፥

ምንተ-ማርያም ባዩ* የሌለው ማደሪያ፥
እለ መሃላችን፥ በዛሬው ገበያ፤
በያንዳንዱ ቅኝት በቅኔ ገበያ
በአእምሮ መስተዋት፥ ራሉን በመለያ
ራስን በማወቂያ፥ ራሰን በመለኪያ፥
በየአንዳንዱ ምሥጢር፥ በየአንዳንዱ ማሳ፥
እለ ያ ቅማላም፥ አለ ያ 'ኮሳሳ'፥
በአንባቢዩ ቅኔ፥ በአንባቢዩ አሰማት፥ በሃሳቡ እንደተያዝኩ፥
ቢራዩን እንደያዝኩ፥ እንጸሱ እያሰተዋልኩ፥
ያ ከካም ተማሪ፥ አቆማዳ የያዘ፥
በትረ-አሮን፥ መቋሚያ፥ የተመረኮዘ፥
ያ ዘኬ ለቃሚ
እሱ ኖሯል ቋሚ፥
ዳግመኛ ተፈጥሮ፥ ሁለተኛ በቅሎ፥
እሱ ኖሯል ቀሪ፥ እኛን ተመስሎ፣
ያ እከካም ተማሪ።
እኛን ሆኖ ኗሪ።

ለአንዲት የቅኔ ምሽት - (፲፱፻፶፫)

# ረሃብ ስንት ቀን ይፈጃል?

ረሃብ ቀጠሮ ይሰጣል?

ወይስ ቀን ቆጥሮ ይፈጃል?

“የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል”

ይባላል፥ ድሮም ይባላል፥

ይዘለዝላል ይከትፋል

ብቻ እስከሚጨርስ ድረስ፥ ሆድ ለሆድ ጊዜ ይሰጣል?

ወተት አንጀት ነጥፎ ሲላብ

ሆድ ዕቃ ደርቆ ሆድ ሲራብ

ተሟጦ አንጀት በአንጀት ሲሳብ ...

የጣር ቀጠሮው ስንት ነው

ለሰው ልጅ ሰው ለምንለው

ላይችል ሰጥቶት ለሚያስችለው

ስንት ቀን ነው? ስንት ሌት ነው ....

የማዕዱ ወዝ ሳታጥጥ

አድባሩ አብዳ ሳትፈረጥ

ጥንብ ሳይተርፋት ሜዳ-አይጥ

የቤት ድመት ሳታማምጥ

በእመቤቷ አስከሬን ብካይ

እሷም ዋይ አንጀቷም ዋይ-ዋይ

ውሻም በጌታው ሥጋ ላይ

ቸነፈር በጣሰው ሲሳይ

አይ! ....

ስንት ቀን ትሆን የራብ አዋይ? ....

እስቲ እናንተ ተናገሩ፥ ተርባችሁ የምታውቁ

ከቸነፈር አምልጣችሁ፥ ተርፋችሁ እንደሁ ሳታልቁ

ትንፋሽ ቀርቷችሁ እንደሆን፥ ያስችሳችሁ እንደሁ ጥቂት

ቀጠሮ ይሰጣል እልቂት?

ስንት መዓልት? ሰንት ሌሊት?

ጥንብ አንሳው ሳይወርድ በፊት* ሳይሞዥርጣችሁ ጥፍሩ

በጣረራሞት አከናፉቱ፥ አንዣቦ በመቅሰፍት እግሩ፥

አንደበት ተርፏችሁ እንደሁ፥ ሳትነግሩን ከምትቀሩ

ካሰቻላችሁ ተናገሩ።

ቆሸሸት-ሲቃው ሳያጣጥር፥ ሰቀቀኑን ሳያጋግል

እሰትንፋሰ ስልምልም ሳትል

ቀጠሮ ይሰጣል ረሃብ? ስስንት ቀን ለስንት ያህል?

ሰንት ሰዓት ነው የራቡ እቅሙ?

ለኔ ብጤማ ትርጉሙ

የሁለት ፊደል ድምፅ ነው፥ 'ራብ' የሚሱት ከነሰሙ

እንጂ የኔ ብጤውማ

የት አውቆት ጠባዩንማ፤

ብቻ ሲነገር ይሰማል

ይህንን ሁለት ፊደል ቃል፥ ....

ቃሉማ ያው በዘልማድ፥*፥ ይነገራል ይሰፈፋል

ይተረካል ይዘከራል

ይደጋገማል ይተቻል

እንጂ እንኳን ጠባዩንና፥ የራብ ዕድሜውን የት ያውቃልን ....

እና እምታውቁት ንገሩን፥ እውነት ራብ ሰንት ቀን ይፈጃል? ...

በጣር አፋፍ ላይ ያለህ ሰው፥ ራብ እንዴት ነው የሚያዛልቅ

ለሰሰንት ቀን ቀን ይሰጣል፤ አንደበትክን ሳይሸመቅቅ

ሽረሪት በልሣንህ ላይ*፥ የድር ትብትቡን ሳይሠራ

ቁራና ቀበሮ በቀን፥ ከቀየህ ድባብ ሳይደራ

ጥንብ አንሳ ሊጭር ሳይመጣ፥ ቅምቡርሰ ከጐጆህ ጣራ

እንደፍካሬ ኢየሱሰ ቃል፥ በጣር ምፅአትን ሳትጠራ

እንደበት ሳለህ ተናገር

የምታውቅ የራብን ነገር

አስከሬንህ ከየጥሻው፥ ተርፎ እንደሁ ሳይቀረቀር

ሰንት ደቂቅ ሰንት ፋታ* ቀጠሮው ሰንት ትንፋሽ ነበር

ቆሸት አርሮ ሳይፈረፈር

ትናጋህ በድርቀት ንዳድ፥ ጉሮሮህ ሳይሰነጠር? ...

የሆድ ነገር ስንት ያቆያል? ቀጠሮ ይሰጣል እልቂት?

ስንት መዓልት? ስንት ሌሊት?

ስንት ሰዓት ነው ሰቆቃው፥ ስንት ደቂቃ ነው ጭንቁ

እስቲ እናንተ ተናገሩ፥ ተርባችሁ የምታውቁ

ስንት ያቆያል? ስንት ያዘልቃልገ ....

እውነት ራብ ስንት ቀን ይፈጃል?

ጥር - ፲፱፻፷፫ - ዋልዲያ

# ምነው አምቦ?

ምነው አምቦ ....

የደማም አምባዎች ቁንጮ፥ እንዳልነበርሽ የደም ገንቦ

እንዳልነበርሽ ንጥረ-ዘቦ

ዙሪያሽ በምንጭሽ ታጅቦ

በተራሮችሽ ተከብቦ

ከጠበልሽ ሚሳይ ታልቦ

ከአዝርእትሽ ፍሬ ዘንቦ

ከዓመት ዓመት ጤና አብቦ

ሕይወት ደርቶ ሰላም ቀርቦ ...

የአየር ትፍሥሕት እንዳልነበረሽ፥ የዘር ሆነ የእሸት የአትክልት

ከመጫ እስከ አዋሽ እምብርት

ምንጭሽ ሲያጥጥ ሲፍለቀላቅ፥ ከዳንዲ እስከ ዋንጪ እትብት ...

እንዳልነበርሽ የምድር አድባር፥ የዘር ድባብ ያገር ችቦ

ዛሬ እንደዚህ ምነው አምቦ

የቀትር ጥላሽ ተስቦ

የጡቶችሽ ወዝ ተሰልቦ

ውስጥ አንጀትሽ ተሰብሰቦ

የመዓዛሽ መፍለቅላቂያ፥ መንጸባርቅሽ ተሸብቦ

ተረምርሞ ተተብትቦ ....

ምነው? .... ምነው አምቦ?

፲፱፻፷ - አምቦ |

# “አቴቴ ዱብራ አሮሞ”

ለካ እንደትዝታ አስታምሞ

እንደዘነጉት የእናት ጡት፥ ከዘመን ጋር አገግሞ

ምንም ቢርቅ ምንም ቢሸሽ* ሕልሜ ከሕልምሽ ተዛሞ

በዓይንሽና በዓይኔ መሃል፥ የሃሰት ሥልጣኔ ቆሞ

ባንተያይ ባንወያይ፥ አቴቴ ዱብራ አሮሞ

እንደልጅነት ሰመመን፥ ለካስ ዕድሜዬም ያማል ከርሞ።

ተግ ሲል ያንቺ ሽውታ

ብዥ ሲል እንደአድባር ጥሪ፤ እንደተረብ ቅርስ ሽታ

እንደእሳት ዳር ተረት ግርሻ፥ እንደእንቆቅልሽ ትውስታ

የጥቅምት እሸት አወደ፥ ነቃ ደሞ ያንቺ ትዝታ ...

አውድማው ተንደረከከ

ሰንበሌጥ ተንተረከከ

ነይ አከርማ እንነቃቀል፥

ከወንዛችን ሾላ ጠለል

ነይ ጢሎሽ እንንጠላጠል፥

መስኮቻችን ስብሎቻችን፥ ግጦሾቻችን አባቱ

የአቴቴሽ ላሞች አጋቱ

በሮቻችንም አጓሩ፥ ኮርማዎቻችንም ነቁ

ጊደሮቻችን ለጥቃት፥ ለይዘታ ለከብደት በቁ

የሁዳድ ድርቆሽ ሠፈር፥ ጥገቶቻችን ቦረቁ፤

አቴቴ ዱብራ አሮሞ፥ እጄን በትዝታሽ ያገርኝ

በሕልም ጣቶችሽ ሳቢኝ

መቸም .... በውን አልሆንሽም እንዲያው በሰመመን ዳሺኝ።

የኔ እጅ እኮ አርፍ አይጨብጥም

የኔ ክንድ ተልም አይተልምም

የኔ ጣት አረም አይነቅልም

በፊደል መፈደል በቀር፥ ጉልጓሎ እኮ አይጐለጉልም

ለስልሻለሁ፥ ሠልጥኛለሁ፥ ሰይጥኛለሁ አልሆንሽም፥

አቴቴ ዱብራ ቦረና

መቸም ሁሉን ቻይ ነሽና

አጥንቴ ከአጥንትሽ ማዕድን፥ ቢመነጭም ተቀምሞ

ከ"ሀና" ከ'አሐዱ" በፊት፥ ከቃል በፊት አስቀድሞ

ዛሬ በዓይንሽ በዓይኔ መሀል፥ አጉል ሥልጣኔ ቆሞ

ሰየጠንኩና አልሆንሽ አልኩ፥ አቴቴ ዱብራ አሮሞ፥...

አዎን መቻል ባንቺ ያምራል፥ ያን የትዝታ ሰቀቀን

ያን የልጅነት ሰመመን

ምንም በውል ባንደርስበት፥ ጭላንጭሉ እየታወሰን

ውል ሲል እንዳልጠፋ ቀን

ከዓመት ዓመት ተሸጋግረን፥ አዳዲስ ዘመን ሲስለፍ

ስንበሌጡ ሲንተረከክ፥ የአዝመራ እሸት ሲትረፈረፍ

የማር እሸት እንቁረጥ ተይ፥ የጥቅምት አበባ እንቅጠፍ

ነይ ሸጎዬ አብረን እንግዘፍ

ጣት ለጣት እንቆላለፍ

በዓይን ጥቅሻ አንገራረፍ

ከአውድማችን አፋፍ ላአፋፍ፥ በዳሰሳ እንጠላለፍ

ተይ ፍቅር እንዘራረፍ

በሕልም እንኳ እንተቃቀፍ፥ ....

አቴቴ ዱብራ ቦረና፥ አቴቴ ዱብራ ኦሮሞ

የቀን የጊዜ እንቆቅልሽ፥ በሕልም መርፌ ተጠቅሞ

በየመከሩ ተተልሞ

ከትዝታ ጋር አሰታምሞ

እንደዘነጉት የእናት ጡት፥ ከዘመን ጋር አገግሞ

ምንም ቢርቅ ምንም ቢሸሽ፥ ሕልሜ ከሕልምሽ ተዛሞ

በዓይንሽና በዓይኔ መሃል፥ አጉል ሥልጣኔ ቆሞ

ባንተያይ ባንወያይ፥ እንደጥንቱ እንደቀድሞ
እንደልጅነት ስመመን፥ ዕድሜም እኮ ያማል ደሞ...
አዎን ዕድሜም ያማል ከርሞ ....
“አቴቴ ዱብራ አሮሞ።”"

ለአቴቴ ዱብራ አሮሞ - (፲፱፻፷፪ - ባሌ-ጎባ)

# ምንም አልል

እሺ እንግዲህ በዝምታ
የልቤን ደም ሥር ትርታ
የደቂቅ ዕድሜን ትዝታ
ትር ስትል አፍታ ለአፍታ
እያዳመጥኩ እያሰታመምኩ፤ ጊዜዬን እያሰላሰልኩ
ሳልናገር ሳልጋገር፥ እየደገምኩ እያሰለሰኩ
ሳልሰለች እየመላለሰኩ ....
እሺ እንግዲህ በጸጥታ
የልቤን ደም ሥር ትርታ
የእስትንፋሴን ቃል ጉምጉምታ
ትር ስልት አፍታ ለአፍታ

ሳልሰለች እየደጋገምኩ

በእግረ ሕሊና እያደቀቅኩ

እየቋጠርኩ እየቆጠርኩ ....

እሺ እንግዲህ አልናገርም

በአንደበቴ አልተነፍስም

በልሳኔ አልመሰክርም

አልልም። ምንም አልልም

እንዲያው ዝም እንጂ ዝም ዝም ....

የልቤ ደም ሥር ሲያቃጭል

ልሳኔን ሲያስነሳ ሲያሰጥል

ቃላቴን ሲቃኝ ሲያጋግል

ትንፋሼን ሲያንር ሲያዳውል

ክል ሲል ትር ድም ሲል

ማዳመጥ ማሰታመም እንጂ፤፥ ሌላ ምንም ምንም አልል።

ጥቅምት - ፲፱፻፷፫ - 'ፒያሳ'

# አዋሽ

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ....

አዋሽ፥ የመጫ ሥር ፍሳሽ

የለም አፈርሽ ደም ቅናሽ

የሸዋ የእምብርትሽ ላቦት፥ የምንጮችሽ የምጥ አማጭ

የአለትሽ የተራሮችሽ፥ የጉልጥምጥሚትሽ ፍላጭ፤

አዋሽ ሕመምህ ምንድነው? ሕመምክስ አንተስ ምንድነህ?

ከውሀ ወዝ የተለየ፥ መቾስ ልዩ ንግርት የለህ

እንደ-ሴቴ ሽረሪት ፅንስ፥ ራስክን በራስህ ዋጥ ያለህ፤...

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ሲያሳድድ ሲያቅበዘብዝህ

ላትዘልቀው ሳያዛልቅህ፥

አሸዋ ለአሸዋ ድኸህ

ውስጥ ለውሰጥ ምሰህ ጠልቀህ

የምድርን ማኅፀን ቦርቡረህ

ዋልታዋን ቁልቁል ሰንጥረህ

እናትህ ውቂያኖስ ማኅፀን፥ ላትገባ ትባክናለህ፤....

እስከመቼ ይሆን አዋሽ?... አዋሽ ቡርቃው፥ መጫ ምንጩ

ዳዳ ፅንሱ ሸዋ ፍንጩ

ውጠህ፥ ተውጠህ እርጩ

የንዳዱ የበረሀ ዕጨ

ንግርትህ ምድነው አዋሽ፥ አባ ብቻ አባ እቅጩ?

ዘለዓለምክን ፈስሰህ ባታልቅ

ምነው ተስፋ መቁረጥ አታውቅ?

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? .... አዋሽ በቃኝ አትል ቆራጥ

ማን ያስተማረህ ፈሊጥ ነው፥ አረህ ለማለምለም መዋጥ

አሻቅበህ ወደ ምሥራቅ፥ ወደ ጀምበር መውጫ መናጥ

ሰምጠህ ልትቀር በሀሩር ማጥ?

አዋሽ፥ ቡቡ ሮሮ ብርቁ

የዘለዓለም ንዳድ ስንቁ፥

አዋሽ አባ ብቻ ጉዞ

ዘለዓለም ብሶት አርግዞ፥

እነዋቤ ሸበሌማ፥ ሰብረው ውቅያኖስ ሲዘልቁ

እነግዮን ወርደው አልፈው፥ ሱዳንን ምሥርን ሲያጠምቁ

ምነው ያንተ ጉዞ ብቻ፥ በረሃ ላይ መታነቁ?

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? .... ወዝክን አሸዋ ሲውጥህ

ደምክን በረሃ ሲመጥህ

ዘለዓለም ሲመዘምዝህ

መቼ ይሆን በቃኝ እምትል፥ መቼ ይሆን በቃኝ እሚልሀ?

እስከመቼ ይሆን አዋሽ?...

አዋሽ የመጫ ሥር ፍሳሽ
የጸዳ የቱለማ ደም
በረህ እምትደመደም?
የሰባት ቤት ጉራጌ አድባር
የከረዩ ቅቤና ማር
ፈስሰህ ለአሸዋ እምትዳር?
አሰቲ አንዴ እንኳ አንደነዋቤ፥ ባክህ ሂድ ውቅያኖሰ ግባ
ዘለዓለምክን በአሸዋ ሆድ፥ ተውጠህ ከምታነባ፥
ቆራጡ እንኳ አንተ ነበርክ፥ የጀግኖች መፍለቂያ ኩሬ
የሡንጋ ፈረሰኞቹ፥ የነኦርዶፋ ጨንገሬ
የሰንቱ መጠጊያ ዋሻ፥ አዋሽ ደኔ አዋሽ ዱሬ
የጥንተ ፍጡራን መደብ፥ የቅድመ ማልካ ካንቱሬ፥
አዋሽ በቃኝን አታውቅም?
በምድር ማኅፀን ከአድማሰ አድማሰ፥ ዘለዓለምክን ሰታዘግም
ወርደህ፥ ሟጠህ፥ ተንጠፍጥፈህ፥ አሜን፥ ታከተኝ አትልም?

መጫ ቋጥሮ ሸዋ ፀንሶ፥ ሰባት ቤት ጉራጌ አርግዞ
ከዳዳ ምንጭ አሩሲ እምብርት፥ ከነቅሪቱ ተጉዞ
ከአላባ ጣፋ ሼህ ሁሴን፥ አዳል ሞቲ ሸሉን ይዞ
ከከረዩ ማታሐራ፥ ከኢቱ እሰከአፋር አምጦ

አሸዋ ነክሶ ቀረ አዋሽ፥ ሳይገላገል ሽምጥጦ
እንደወላድ ሳይታረዝ፥ ከነፅንሱ አረህ ሰምጦ
በምድረ በዳ ጉረሮ፥ በረሃ ሳንቃ ተውጦ።
እሰከመቼ ይሆን አዋሽ? .... አዋሽ አባ ሮሮ ቅርሱ
የዘለዓለም ንዳድ ጉርሱ፥
አዋሽ ቡቡ በረኸኛ
የአረህ ሽለቆ በረኛ
የአሸዋ ዋሻ መተኛ
የበረሀ ዋነተኛ
የምድረ በዳ ብቸኛ
የዘለዓለም መንገደኛ፥....
የአበቅቴ መወራረሻ፤ የዕፀዋት ዕድሜ መቁጠሪያ
በፀደይ የአልባሳት ማዕጠንት፥ የዘመን ሳቦት ወዝ ማጥሪያ
የእንቁጣጣሽ ማዳበሪያ
የአዝርእት ሰብል ማጥለያ፥
በክረምት የዶፍ ረከቦት፥ የሰማይ ምጥ መቀባያ
የደመና አምባ ማጠቢያ፤ የማዕበል ሰደድ ማከያ
የተራሮችን ለቅሶ ቻይ
የጅረት የምንጮች አዋይ፤....
ጭምት መሳይ፥ ያለዐመሉ

ዘራፍ ባይ በመስከ ሙሉ፥

አባ ጭራቅ-አከናፍ ቀንዶ

አዋሽ ዘጠኝ ራሰ ዘንዶ

ቁልቁል እንደምሽት ጥሳ፤ ከሰማየ ሰማይ ወርዶ

ሞልቶ ተንደላቆ ኮርቶ፥ የሰንት ዓለም ምድር ጐርዶ

ቀይ ደመና ተከናንቦ፥ ጋራ እንደአሻንጉሊት አዝሎ

ሰንቱን በረት እንደጉድፍ አውተፍትፎ አንጠልጥሎ

አውድማውን አንገዋልሎ

ወርካውን ግቻ አሳክሎ

አመንምኖ አስልሎ

እንደዘጠኝ በገና አውታር፥ በየረድፉ ተሰድሮ

በአገር ምድር ዙሪያ ጥምጥም፥ እንደመቀነት ተቋጥሮ፥

አዋሽ ቁጣ አባ ዱታ

የሰማይ ጥጉ ቱማታ፤

አዋሽ አባ ሻኛው ጋራ

ኩሩ እንደነማታ ሐራ፥

የግርማ ሞገስ መርገፉ

አስከነምድረ-አቀፍ ዘርፉ

አባ ገርስስ ሞልቶ ደራሽ፥ አባ አደፍርስ አባ ኩርፉድ

ከተፍ እንደመብረቅ ግማድ

በምድር ቁና ድንገት ሲጣድ፥
አዋሽ ንፉግ አባ መዓት
የገጠሬ አታምጣ ምጣት፥
አዋሽ ደርሶ-ቀማው-መብረቅ
አባ መዝረፍ-መውሰድ-መንጠቅ
ግሣንግሱን አግበስብሶ፥ በምድረ በዳ ለማጨቅ
ሀሩር ጉረሮ ለማመቅ
የአሸዋ ሆድ ለመጠቅጠቅ
ሀራም ብሎ አብሮ ለመጥለቅ
እምድረ ከርስ መቀመቅ....
እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ... አዋሽ ብኩን ምሥጢረኛ
የጠፍ-ፋኖ አባ ብቸኛ
የበረሃ መንገደኛ
የጨረቃ ግዞተኛ፤
ካገር ሞት ወዲያ ላትሞት፥ ካገር ምጥ ወዲያ ላታምጥ
እሰከመቼ ይሆን አዋሽ፥ ራስክን በራስህ እምትውጥ?
አዋሽ አባ ሮሮ አገሩ
ያሸዋ ማኅፀን ድንበሩ
የምድረ ዓለም ኬላ በሩ
ኩሩ፥ ብሶት እንደልቡ

ቅምጥል የሸዋ ቡቡ

የሰማይ አድማስ ግድቡ

ንዳድ ስንቁ አረህ ግቡ፤

እስከ መቼ ይሆን አዋሽ? ... አዋሽ ቡቡ አባ ብሶት

የሰው ችግር ሳይደርስብህ፥ ሳይቸግርህ የእውነት እጦት

ላትዘልቀው ላያዛልቅህ፥ ለማንም የትም እምትሞት?

ታድያ እስከመቼ ነው አዋሽ?

አዋሽ፥ የመጫ ሥር ፍሳሽ፥

የሸዋ የእምብርትሽ ላቦት፥ የምንጮችሽ የምጥ አማጭ

የአለትሽ የተራሮችሽ፥ የጉልጥምጥሚትሽሽ ፍላጭ፥

እስከመቼ ይሆን አዋሽ፥ ወዝክን አሸዋ እሚውጥህ?

ደምክን በረሃ እሚመጥህ

አጥንትህን ምድረ በዳ፥ ሀሩር እሚመዘምዝሀ?

መጫ ቋጥሮ ሸዋ ፀንሶ፥ ሰባት ቤት ጉራጌ አርግዞ

ከዳዳ ምንጭ አሩሲ እምብርት፤ ከነቅሪቱ ተጉዞ

ከአላባ ጣፋ ሼህ ሁሴን፥ አዳል ሞቲ ሽሉን ይዞ

ከከረዩ ማታ ሐራ፥ ከኢቱ እስከ አፋር አምጦ

እንደወላድ ሳይታረዝ፥ ከነፅንሱ አረህ ሰምጦ፥...

በምድረ በዳ ጉረሮ፥ በረህ ላንቃ ተውጦ....

አሸዋ ነክሶ ቀረ አዋሽ፥ ላይገላገል ሸምጥጦ።

እስከመቼ ይሆን አዋሽ፥ ተሰፋ መቁረጥን እማታውቅ?

ፈስሰህ ተሟጠህ እማታልቅ?

ጉዞህ በረሃ ሲታነቅ

ሀሩር ጉረሮ ሲታጨቅ

አጥንትህ ጉልጥምጥሚትህ፥ እምድረ-በዳ ሲታመቅ

እስከመቼ ይሆን አዋሽ፥* ቆርጠህ ቀይ ባህር እማትዘልቅ?

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? .... መቸም ሌላ ንግርት የለህ

እንደ ሴቴ ሽረሪት ፅንስ፥ ራሰክን በራስህ ዋጥ ያስህ፥

እስከመቼ ይሆን አዋሽ? ....

ለጋማቹ ቃማሊቲ - (፲፱፻፺፬ - አዋሽ)

# እግር እንይ!

አርቀን ማስተዋል ማስት፤ የኛን ሥልጣኔ ድልድይ
እግር ማየት ነው ብለዋል፥ እስቲ እንግዲህ እግር እንይ!
ያባቶችህ ያይን ድንበር፥ ከተረከዘ ሎሚ ሳያልፍ
አንተ ግን ጀቢራው-ዘራፍ
ጠረፍ አይወስንህ ጉብል
ጥሎህ በዘመንህ ዕድል
ዓይንህ ባት አልፎ እንዲዋልል፤
ቱህ ወዲያ ጀግንነት የለ* ተዚህ የከረረ ግዳጅ
ባደባባይ የዱር ገደል፥ ስትናደፍ የእግር አዋጅ
ሌሊቱን በየሌት- 'ግለብ'* ቀኑን ጭምር በጠራራ
ሲነጋ እንደጧት ጀቢራ
በከተማህ ስታቅራራ
በዕድሜህ መንከራተት ሥራ፥
ካንዱ ቢሮ ሌላው ቢሮ፥ አቦል በረካውን ብለህ
ያገሩን ወሬ ተንትነህ
ተጨቃጭቀህ ተለፋልፈህ
አመሳጥረህ አቆላልፈህ፤፥ የዚያን ጉዳይ ከዚህ ጉዳይ
ዘጋግነህ በቡና ምገህ፥ አምተህ ደክመህ ስተለያይ፤

በዚህ ብቻ ሳታስቀረው፥ ደሞ አዲሱን የአገር ጠባይ

ከልማድ የቡና ሱስ ጋር፥ የዘመኑን ሳትለያይ

እስቲ ደሞ አራዳ ወጥተህ፥ በከተማው አደባባይ

ያንዱን ካንዱ ዳሌና ባት፥ እግሯን ከአግር ጋር አስተያይ!

ደርቶልህ ያገር ልጅ ቅልጥም

ዳሌው ባቷ እስኪፈረጥም

እየናረ እስኪያስገመግም

አንተ አድፍጠህ ከኋላዋ፥ በዓይንህ ሣግ ስታነፈንፍ

ያቺን ልክፍ ያቺን ንድፍ

እያረክ ስታሾልቅ፤ አንዷ ፈርታ አንዷ ስታፈጥ

ተጠግታህ ባቷ ሲያገምጥ

"ዘራፍ" ቀርቶ ቀልብህም "ውይ"

እያለ ወኔህ አግር ይይ!

"በሠየጠኑትማ ዘንድ

አንዱም የባላንጣ ዘዴ፥ የባዕዳን ሥውር መንገድ

ዘመናይ ጦር መሣሪያ ነው፥ ታዳጊ አገር ለማንጋደድ

እምነቱን ለማወናበድ

ያንድን ትውልድ የሕልም አቅጣጫ

ወደፊት ሳይሆን ወደታች፥ አመንምኖ ማቀጨጫ"

ቢልህ ፈጥጦ በግልምጫ

ለኅሲናህ ማጋለጫ

ናቀው እርግፍ አርገህ ተወው፥ ቴህ ብጤው ጋር አትንጫጫ።

ሦልጥነን ንቀን አልፈነው፥ የይሉኝታን መቀጣጫ

የኛ ዓይን የእግር ነው አንጂ፥ በቅቶት ኅሊና መግለጫ።

አርቀን ማስተዋል ማለት፥ የኛን ሥልጣኔ ድልድይ

እግር ማየት ነው ብለናል፥-አሜን በቃን እግር አንይ!

ለአግረተኞች' - (፲፱፻፷፫ - 'ፒያሳ')

# አንኮበር

አንኮበር የአምሃየስ በር
አድማስ-ፈጠር ኬላ-ሰበር፥
አንኮበር የአምባ ላይ አገር፥
የኮረብታ ዲብ ያድባር ዛፍ
አንኮበር የአለት ላይ አጥናፍ
ስውር ምድር የአድማሳት ጫፍ፥
ባሥራ ሁለት እግር ሺዋ፥ እንዳሞራ ከግንድ አፋፍ
የተንሠራፈትሽ እመቤት፥ እንደታቦት በእምነት ድጋፍ
እንደራዕይ በክንፍ እርካብ
አንደጽላት በአየር ድባብ፤
አቀበት የደመና አዘል
መቀመቅ ዝንጀሮ ገደል
የመዲኖች ጭፍግ ጠለል።
መንዝህ ይጫ ጌራ ምድር
ሮይ-አንጀትላ ላሎ ቁጥር፥
ከወልቃ በር እስከጠራ
ከደንገዜ እስከአፍቀራ
ባለመጣቀሻ ነፍጥሽ፥ ከካራ-መገን አይራራ፤

ግድም ኤፍራታ አእጸኪያ

የጎበዛዝሽ መፍለቂያ፥

ከተጉለት ዳር እስከ እንሣሮ፥ ከነይገባዋል መግቢያ

ከጉራች በመለስ ማዶ፥ ከሙቀጪት ጅረት ወዲያ

ከጀራ እስከስላላ፥ እስከጥዱ ሞረት አገር

አንኮበር የአስት ድንበርሽ፥ የምድረ ገጽሽ ፈረፈር

ከመልከአ-መሬት ደርዝ ጋር፥ አምባዷሮ እንዳለሽ ነገር

እንደአዞ መጋዝ መንጋጋ

ከኤፍራታ እስካርጐባ፥ ከቆላ እስከወይናደጋ

ከቤቶ እስከሸበቶ፥ ከጥቁር አባዬ ቡልጋ፥

ከወላስማ እስከንሣሮ

በፈፋሽ አነባበሮ

ዙሪያ ጥግሽ ተተርትሮ

ሽቅብ ቁልቁል ተከርክሮ

ተረተርሽ ተቦርቡሮ

መቀመቅሽ ተሠርስሮ፥

አንኮበር የአምባ ላይ አገር “

አድማስ-ፈጠር ኬላ-ሰበር፥ -

ጠራ-ሲቄ የሥረቄ፣ ጠራ አምሃራ የአምሃየስ

የኩሩ አገር ጋሜ መለስ

የገር አገር ዳባ ሰበስ

የነቸር አምሃ ፈስስ፤

አንኮበር 'ያታከልት' አገር፥ የነእምዬ ምኒሲክ ፍንጭ

የመርድ ዘሜ ቅኔ ምንጭ፥

ስወረ-ሴክ መገናኝ፥ ለነጣይቱ ስያሜ

በመላክ-ሣንቃ ጎዳናሽ፥ ለጎንእደሬ ለጎጀአሜ

ለትግራይ አባት ለአጋሜ፥

በሞፈር ውሀ ክናድሽ

በቀጭኔ ጅረት ሽንጥሽ

ከመገዘዝ ይፋት ግርጌ

የነወልዱን መርሐቤቴ፥ ከአርግቢያት አስከገደልጌ፤

ሰነፍ የዶባ ሰው ሲሉ፥ ላም የጋላሞታ ሲሱ

ከአባ ዳኘው ከሥዕሉ

እንደአባ-ጉራች ጉዲሳ፥ ሺዋን ሲፈጥራት በምስሉ

ኃይለ-መለኮት ፀበሉ

ዕድልሽ ሆኖ ነው ውሉ

"አንኮበር ዕደግ" መባሌ?....

አንኮበር የኬላ ሰበር

ከዓይኔ ከተማ ዳር-አገር

ዘመን ወደ አንቺ ሲሻገር

የነበርሺው ደን ውድማ፥
እትብትሽ እንዲህ ሲለማ
ማማ ምድርሽ መንዝህ ማማ
ጌራ ምድርሽ መንዝህ ይጫ፥ ሳሎ ምድርሽ መንዝህ ጭማ
ከማፉድ እስከሮቢት ዳር፥ እስከ ዶቃቂት ከተማ፥
ከሾላ ሜዳ እስከዓዋዲ፥ ከጣርማ-በር አስከአራድማ
ከገፈገፍ እሳካንጋቻ፥ ከይፋት አስከወላስማ
ከአውሳ አብዬስ ግሼን ማዶ
በደጋሽ አናት ላይ በርዶ
ጉንሽ ቡልጋ ተገድግዶ
ፍርኩታ ንዳድ ተወርዶ
በከስም በረሃሽ ነዶ፥
ከሸንኮራ እስከምንጃር
አንኮበር "የመሄዴ'" አገር-
ከመረሬ አፋፍ መልሶ፥ እለከጨበሬ ምሑይ ዳር
ከወግዳ ከነባሮ አገር፥ ከታላቅ አምባ ነጭ ሣር፤
አንኮበር የአለት ላይ አጥናፍ
ስውር ምድር የአድማሳት ጫፍ
የኮረብታ ዲብ ያድባር ዛፍ፥
እንደራዕይ በክንፍ እርካብ

እንደጽላት በአየር ድባብ፥
አቀበት የደመና አዘል
መቀመቅ ዝንጅሮ ገደል
የመዲኖች ጭፍግ ጠለል፤
አንኮበር የአምባ ላይ አገር
አድማስ-ፈጠር ኬላ-ሰበር |
አንኮበር የአምሃየስ በር።

ለተፈራ ደገፌ - (፲፱፻፷፫ - ደብረ ብርሃን)

# ደኅና ዋይ እማማ

አዬ፥ አማምዬ፥ ደኅና ዋይ

ያሳወረሽ አሳወረኝ፥ ቀን የተጣባብን ሥራይ፤

ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ ...

ያለ ጠር መጣረር ዕዳ፥ ወይ ያለባላንጣ ግዳይ

አቆላልፎን፥ አቆራርጦን፥ በዕንባ በትካዜ ብካይ

ዘመን የተፋው ሾተላይ፥

አዬ፥ በቃሽኝ፥ በቃሁሽ፥ ዓይኔስ ዓይንሽንም አያይ...

በቃ እማማ እናት ዓለም፥ እማትነፍጊ እማታቅማሚ

እማታሳጪ እማታሚ

እኔን በራበኝ፥ በጠማኝ፥ እንዲያ አብረሺኝ ስትጠሚ

ምነው ወተቴን ከጡትሽ፥ በጊዜ-ገፊ ታስቀሚ?

አንጀቴ ያንጀትሽ ቁራጭ፥

አጥንቴ ያጥንትሽ ፍላጭ

ሕይወትሽ የሕይወቴ ምንጭ፥ ወዜ የፍቅርሽ ወዝ ምጣጭ

ማኅፀንሽ የፍጥረቴ አማጭ...

ከእንግዲህ በቃሁሽ፥ በቃኝ፥ እማማ የነፍሴ ቁራጭ

ይበጠስ ውልሽ ከውሌ፥ ቃሌ ከቃልሽ ይፈለጥ

ዓይንሽ ባይኔ ትል ዘነበ፥ በቃኝ፥ የኔው ብሌን ይፍረጥ
ብቻ በምን አንጀቴ ነው፥ አንጀቴን ባንጀቴ እምቆርጥ?

ይቆረጥ እንበል፥ ይገርለስ?
ይረሳ፥ ይሙት፥ ይደምሰስ?
እርም አፈር እንበል ይበጠስ?
ማኅፀንሽ ጽዋው መረዘኝ፥ ዘጠኝ ወር ያጠባኝ ገንቦ
ጡትሽ የደም ወተት ዘንቦ
ሆድሽ የቁሰል ምጥ ታልቦ
ባዳ ቅሪት ተመትሮብሽ፥ የእንብርቴ እልባት ተሰብሮ
ደሜ በፋፋበት እትብት፥ ገፌ ዲቃላ ተቋጥሮ፤

በቃ እማማ፥ እማማዬ
መቀነቴ፥ ገበናዬ
በቃሁሽ አድባሬ፤ መቅኔ
ከእንግዲህሰ ላንቺ መጥኔ
አዬ ላንቺ አዬ ለኔ ....
ጫቅላዬን ባዘለ እቅፍሽ
ገፌ ጉግ ማንጉግ መፅነሰሽ
ጉምቱ ሾተላይ ማብቀልሽ...
አይሆንም አንጂ ከሆነሽ፥ ካለልሽ ካዘለቀልሽ

እግዚአብሔር ያሳድግልሽሽ፤

አዎን፥ ቃል ለምድር ለሰማይ

ደኅና ዋይ በቃ፥ ደኅና ዋይ

ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ፤

ከፉም በጐም አናሰማ

እንዲያው ደኅና ዋይ እማማ

እናት ዓለም የስሜ አርማ

የሕይወቴ ወዝ የዓይኔ ማማ

እማትነፍጊ እማታቅማሚ

እማታሳጪ እማታሚ

እኔን በራበኝ በጠማኝ፥ አብረሽኝ እምትጠሚ

ጥቃቴን እምትጠቂ፥ ቁስሌን እምትታመሚ

ፍሥሃዬን፥ ፈገግታዬን፥ ሳቄን ብቻ እምታልሚ

አንቺ እማማ

አንቺ የነፍሴ ልብ ዓልማ

የዓይኔ ማማ...

ምነው ጡትሽ ተጣረረኝ?

በጊዜ-ገፊ ለወጠኝ?

እንዴት ይንጠቀኝ ሾተላይ?

ቀን የተጣባብን ሥራይ

ያለኝታ ኀብስተ-መና፥ የወገን የአጥንቴን ሢሳይ

የደሜን ምንጭ የሕይወቴን ማይ

የማኅፀን የእትብቴን አዋይ?...

አዎን፥ ይብቃን እናት ዓለም፥ አንጀቴ ባንጀቴ ይቆረጥ

አጥንቴም በአጥንቴ ይድፈጥፈጥ

ቃሌም ከቃልሽ ይፈለጥ

የዓይኔም ውሃ በዓይንሽ ይፍረጥ

ይረሳ፥ ይጥፋ፥ ይደምሰሰ

እርም አፈር እንበል ይበጠስ...

በቃ እማማዬ ደኅና ዋይ

የደሜ ምንጭ የሕይወቴ ማይ

የማኅፀን የእትብቴ አዋይ

አሜን፥ ቃል ለምድር ሰሰማይ

ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ።

፲፱፻፵፫ ሎንዶን

# ሊማ-ሊሞ

የስማይ የምድሩ ኬላ፥ የየብስ የጠፈሩ ዋልታ
አይበገር የአለት ጣራ፥ አይመከተው መከታ
ሊማ-ሊሞ አድማሰ ሰበሩ፥ በጐማ ፈለግ ይፈታ?
በትሬንታ እግር ይረታ...

ሊማ-ሊሞ የቁም እርሙ፥ ሰማይ-አዘል ሊማ-ሊሞ
ከንፉ ከነካሰማው ዘሞ
ከጠፈር ውሃ ገድቦ፥ ለየብሰ እንደማገር ቆሞ
ተጠማዝዞ ተጠምጥሞ
ከጽንፍ ጽንፍ እረምሞ

ከደባርቅ እሰከ አዲ አርቃይ
አለት ከደመና በላይ
አዘንብሎ እንደ ሰማይ
እንደጠፈር ሽቅብ ሲታይ፤

ጉም አጥልቆ እንደቀሚሱ
ፀሐዩን እንዳንገት ልብሱ

ተከናንቦ ተሸላልሞ
ተንደላቆ ሊማ-ሊሞ፤

ጨረር ባደመቀው ጭጋግ
ዙሪያ ዘርፉን እንደጎዳግ

በንዳድ ሀሩር ምድኛ
ፍም አንጥፎ እንደ ሥጋጃ፤

ሰማዩን ቁልቁል ዘንጥፎ
በብብቱ ጉም ታቅፎ
የእድማሳቱን ፍንጣቂ፥ ለእግሩ መርገጫ አርከፍክፎ፥

እንደፍካሬ ኢየሱስ ቃል፥ እንደሙታን የግዞት ሕግ
ተውተብትቦ ተጥለፍልፎ፥ ተቆላልፎ እንደዛር ድግ
በምድር በስማይ ዳር ድንበር፥ በሕዋው ዓለም ክልል ጥግ

በሲዖል ጠፍር መሰሳል፥ የብለ ከጠፈር ታድሞ
ጥጉን እንደራእዩ እውታር፥ ከነአከናፉ ቁልቁል ዘሞ
እንደእንጦርጦሰ በር አጥር፥ በአለት ናዳ ተረምርሞ
የጉም ክናዱን እንደጣር፥ ወደ ምድር ማኅፀን ቆልምሞ
እንደባቢሎን ግንብ አጥር፥ ቋንቋ ለቋንቋ እሳድሞ
አልበገር እልደፈር፥ አልሰበር ያለን ከርሞ
ሊማ-ሊሞ የቁም-እርሙ፥ ጠፈር-አዘል ሊማ-ሊሞ
ዛሬ እንደስለት ሃጅ ፈለግ፥ በግብረ ጉንዳን ተተልሞ
ሰማይ ከምድር ተደላድሎ፥ ተኮትኩቶ ተከርክሞ
በዲማሚት ተፈልፍሎ፥ ድልድይ ይሁን ሊማ-ሊሞ?

ለፈረደ ዘሪሁን - ፲፱፻፷፫ - ተክዜ

# ጎል!

ያንዱ ደስታ ላንዱ ዋይታ...

እሰየው ጎል! .... እረገኝ ጎል!

ያንዱ ገነት ላንዱ ሲያዖል።

እንዲያ ነው ጎል አባ ቁርጡ

ያንን ሁዳድ ሙሉ ጀግና፥ ሲገላግለው ከምጡ። ....

አጫዋቹ ያፉን ፊሻካ፥ ሲነፋ ሲል ገና ሲያሾል

ሠራዊቱ ተሸቀዳድሞ፥ ከቅምጡ ሲኮለኮል

ዓይንና እጁ ከነነፍሱ፥ ብን ብሎ ሲንጠለጠል

ከአራጋቢው ጨርቅ ጋራ፥ ብትን ሲል ሲንጀለሰጀል

ልቡ ከኳስ ቀድሞ በሮ፥ ሽቅብ ሲጐን ሲሽቆለቆል

በገና እግር የተለጋ፥ የፈኛ ሩር ሲድቦለቦል

በሁለት ማዕዘን መካከል፥ ሾልኮ ተውዘግዝጎ ሲዶል

"ጎል!" ይባላል፥ እንዲያ ነው ጎል!...

ከዚያማ ጎል አባ ቁርጡ

ያንን ሁዳድ ሙሉ ጀግና፥ ከጉሳገለው ከምጡ....

ምኑ ቅጡ! ምኑ ቅጡ!

ውጥንቅጡ፥ ብሽቅጥቅጡ

የጠርሙስ ስባሪ ጉርጡ

የቡጢው ናዳ የፍልጡ

የተቺ አግቦ ብጥብጡ

የፈላስማው መብለጥለጡ

የታዛቢው ማሽቃበጡ

የእንካ ስላንቲያው ሽሙጡ

የእንካ እንጠጣው ጭልጥልጡ

ያፍና የጥፊ ድጡ

የሆድ ቁስል ፍርጥርጡ

ምኑ ቅጡ፥ ምኑ ቅጡ! ....

የተነፋ ሩር ተጉኖ፥ በእንጨት መካከል ባለፈ

ስንቱ ጉድ ከተለፈፈ

'ያራዳ ጐበዝ' በከንቱ፥ እስከዚህ ከተማረረ

'ጀግና' እንዲህ ከተዋገረ

በነገር ከተዋቀረ

እከደከ! ማለት እንጂ፥ አንደዜም ጎል አንዴም እረግ!

እበሸ ለእበሸ ሲጠራረግ

መቸስ ሌላ ምን ሲደረግ

ፊኛ በእንጨት ውል በገባ

'ጐበዝ' አጉል እየባባ

ነገሩ እንዲህ ከጠነባ

አፍና ደም ከተቃባ....

ጭንቅላት እንደኳስ ሞልቶ፥ በኳስ ተሳክሮ ቢታወር

እርስ በርሱ ቢሰባበር

እረግ! እያልን የጎል መከር

ዝም ብለን ከማየት በቀር

አያስችለን የሱ ነገር፥

የተነፋ ሩር ማባረር።....

ያንዱ ዋይታ ላንዱ ደስታ፥ እሰየው ጎል! እረገኝ ጎል!

ያንዱ ገነት ላንዱ ሲያል።

ለኳስ 'አርበኛ'- ፲፱፻፷

# አዴ አዳዩ

አዴ አዳዩ እመ-ምኔቴ
የትውልድ መስታየቴ
የዘመን ቅርሴ መክሊቴ
የዕድሜ አንቀልባዬ፥ ሞግዚቴ

ቀን ማገረሽ አንቺ እጣዬ
ጃጀሽ አሉኝ አዴ አዳዩ፤....
በሥጋትሽ ተንጠልጥዬ
በአንገትሽ ማተብ ታዝዬ
በዓይንሽ ጢሎሽ ተንጠልጥዬ
በጮጮሽ ተሞካሽቼ፥ በጉርሻሽ ውሽን ተብዬ
በእንጉቻሽ ተከባክቤ፥ በእንኮኮሽ ተደላድዬ፤

ካፍ ከወጣ አፋፍ ነው ሲባል
ለካሳ ነገር ይገለማል፤

አዴ አዳዩ የአባዬ እናት
ለምን ይሆን ያሉሽ አያት
ባፍ ዝምድናሽን ሲያቀርቡት
ስምሽን ሦስት እጥፍ ያራቁት?

ከዚህ ወዲያ ምን ይበሉ
ላይሉት ነገር ብለውኝ፥ ዋ ዕድሌ አለመታደሉ
የአንቀልባ ማውረጃ እርካቤን፥ አዳዬን ጃጅተሻል አሉ።

የዓይንሽ ብሌን ያ ብረቱ
ያ የመለኮት ስለቱ

ካለማወቄ ያገደኝ

ከምድጃ እሳት ያፈለኝ፤

የእጅሽ ድባብ የሙቀቱ
የፍቅርሽ ንቃት ፍጥነቱ
መዳፍ ዳሰሳሽ ድቀቱ
ተግ-ብር ያለ ሥጋቱ፤

ከውድቀት አፋፍ ያቀፈኝ
ከጋሬጣ የጋረደኝ፥

ያ እጅሽ የልጅነት ክንፌ
ጣትሽ የድሆሽ መርገፌ፤
አዳዬ መዳፍሽ ዘርፌ
የትውልድ እም-አአላፌ
የዓለም መሻገሪያ ጠንፌ

ቀን ማገረሽ አንቺ እጣዬ
ጃጅተሻል አሉኝ አዳዬ።

የዘመን አጥር ኣጠረን?
የዕድሜ ግድግዳ ጋረደን?
ሳንጣላ ሳንኳረፍ፥ የትውልድ ማገር ለየን?
ጊዜ ለጊዜ ነው እንጂ፥ ዓይን ለዓይን አላሳይ አለን?...

አዴ-አዳዬ እመ-ምኔቴ
የትውልድ መሰታየቴ
የዘመን ቅርሴ መክሊቴ
የዕድሜ አንቀልባዬ፥ ሞግዚቴ

የሕፃን ዓለም አጥላዬ
መከዳ መካበቻዬ፥

በቃ ላንቺ ወዮ አልልም፥ ይብላኝልኝ፥ ወየው እኔን

ሞተሽ ሳለ ግማሽ ኖረሽ፥ በእስትንፋሰሽ ግርሻ ሳጤን
በበድን ሕይወትሽ ዋገምት፥ በቁምሽ ግማሽ አሰከሬን፥
ሳልገፋው በዕድሜሽ ዕድሜዬን
ጊዜሽ ላይወሰን ዘመኔን
በሰምሽ ሰይሜ ሰሜን፥
አዎን ይብላኝልኝ አኔን

ወረቴ በምድር ለቀረው፥ ያንቺ ሲዛመት በሰማይ
ከእንግዲህ ቋንቋ ለቋንቋ፥ ላንጣጣም ሳንወያይ
ባንቺ ገበያ ላልገበይ፥ ላላገግም ባንቺ ሚሳይ
ዕቁብ ለዕቁብ ላንጣጣ፤ ላልሞካሽ ባንቺ ጠባይ
ዐመል ለዐመል ላንወያይ፥ዕድሌ ዕድልሽን ላያይ
መቀነትሽ ሳይመጥነኝ፥ ላትዘልቂ በኔ አደባባይ፥
ያንቺሰ አካቷል አዳዬ፥ ይብላኝልኝ ለኔው አዋይ።

ይብላኝልኝ አዴ አዳዬ፥ ውለታሽን ላልከፈልኩት
በወዝሽ መጥናቴን እንጂ፥ መጠንጠኔን ላልተማርኩት።

አቀርቅሮ ምድር ዓለም፥ ዓይንሽ አፈር ሲቆረቁር
ሕልምሽ ሲቃ ሲያፍተለትል፥ ሃሳብሽ ጣር ሲቦረቡር፥
ጣትሽ ጉድፍ ሲያጉደፈድፍ፥ ሕሊናሽ ቁልቁል ሲያተኩር
አልፎ አልፎ እንኳን ቀና አትዪ
የኔን ቀሪ ዓለም ዘብ-እረብ፥ እስለምልሜን እንዳታዪ፥...

አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ
የቅድመ ፍጥረት ምክንያቴ፥
የሕይወት አማጭ ሰበቤ
የመኖር ክብካብ ድባቤ፥

ያንቺማ አካቷል እንግዲህ፥ የጊዜአችን ኬላ በሩ
የዘመን ግድብ ድንበሩ

የትውልድ አጥር ማገሩ
አምባ ከአምባ ከፍሎ አግዞን፥ የናት ባዳ ሆኖ አድባሩ፥

ታድመን እንዳልተጣመርን፥ ተሸልቶ እጣሽ ከአጣዬ
ተቆራርጠን ተገንጥለን፥ ባይተዋር ሆነን አዳዬ፤

በዕድሜ ናዳ ተገድቦ፥ የፍቅርሽ ሙቀት ጠልቆ
የሥጋትሽ ምንጩ ደርቆ
ያይንሽ ጨረር ሰሉ ባርቆ
ብርሃን-ወሰፈንጥሩ ዳሽቆ፥

የሰሜት ጮራሽ ዳለጠ
የዕድሜሽ ውጋጋን ሚለጠ።

አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ
የትውልድ መስታየቴ
የዘመን ቅርሴ መከሊቴ
የዕድሜ አንቀልባዬ ሞግዚቴ
ቀን ማገረሽ አንቺ እጣዬ
ጃጀሽ አሉኝ አዴ አዳዬ።

አዎን፥ በትውልድ ኬላ፥ የዕድሜ ሕመምሽ እኔ አያመኝ
ቂም እንዳዘለ አበዳሪ፥ ካጥር ማዶ ነው እሚጠቅሰኝ፥
ላንተም ቀን አለህ እያለኝ፥ ላልረሳው እያስታወሰኝ።
"ጊዜ የጊዜ ነው እንጂ፥ አንቺ እኔ ነሽ፥ እኔ አንቺ ነኝ"

ብልሽ፥ ላንደበት ወግ በቀር፥ እኔም አንቺም አንጠቀም
ሕመሜን ላትታመሚ፤ ሕመምሽን ላልታመም፥

የዘመን አጥር ክፍሎናል፥ አውቀነዋል፥ አንደለል
ታድያን ጊዜ የጊዜ እንጂ፥ ድሮም የዘለቄታ አደል።....

እና፥ የነገ ጥሪዬን፥ ዛሬ በጥሪሽ አየሁት

አዴ አዳዬ እመ-ምኔቴ፥ ጭንቁን በጭንቅሽ ለየሁት፤

እንጂ፥ ካንቺ አልከፈልም
እኔ ቁሰልሽን አልቆስልም
ጣርሽን አልጣጣርም፥
በጉልበትሽ እንደጠናሁ፥ አንቺ በጉልበቴ አትጠኚም
በወዝሽ እንደለመለምኩ፥ በወዜ አትለመልሚም
ቁቤ ያንቺን መንጠቅ እንጂ፥ ዕዳ መክፈሉን አያውቅም
በጉርሻሽ መጥናቱንም በቀር፥ መጠንጠኑን ከቶ አያይም፥

አዴ አዳዬ ብቻሽን ነሽ
ጣር እሚካፈልም የለሽ።....

ክናድሽን እንደ አለት ላይ ዛፍ፥ ቅርንጫፉን ለጭራሮ
ቦና አራቁቶት ተንጨፍርሮ
ለማገዶ ተሠንጥሮ፥

ለዛው ተሟጦ እንደ ሁዳድ
ተንጋሎ በህጋይ ምጣድ
አረህ ሥራ-ሥሩን ነድሎ፥ አጋልጦት ለቀትር ንዳድ፥

የዘመን ህሩር በስለት
ግንዱን ኣክስሎት በግለት፥
ክንፍሽ ዘሞ እንደዛር ጥላ፥ መዳፍሽ አርሮ እንደኩበት
ጣትሽ እንደአሞራ ኩምቢ ጥፍርሽ እንደጥፍሩ ጉጠት...

ስሜ እንኳ እንዲያ የምትወጂው፥ እንደምሥጢር ግር ሲልሽ
እንቆቅልሽ ሲሆንብሽ
ገጥታዬ ሲያሳስትሽ
ትዝታው ሲያስበረግግሽ
ሃሳብ እንደትንፋሽ ሲያጥርሽ

“ጥም እንደቁም ነገር ሲያንቅሽ"*
ውሃ ስትይ የሰንቅ ውሃ፥ ለግብር፥ለጣረ-ሞት ምስሽ
ለመንፈሴ ፋታ ልስጥ፥ ትዝታሽ እንዳያገረሽ
ከንፈሬን ጉንጭሽ አድርሼ፥ ከጭንቀትሽ በዚህ ልሸሽ

ሳትሞቺ ግማሽ ሙት ፊትሽን፥ በከንፈር ተሰናብቼ
ጣርሽን በዚህ ሸኝቼ
የወግ የይስሙላ አድርሼ፥ እፎይ ብዬ ፋታ አግኝቼ
መንፈሴን አስተባብዬ፥ ዕንባዬን በዚህ ገትቼ፤

ተሰናበትኩሽ አዳዬ፥ የትውልድ መስታየቴ
የዘመን ቅርሴ መክሊቴ፥ የዕድሜ አንቀልባ እመ-ምኔቴ፤

ተሰናበትኩሽ አዳዬ፥ በፍትሃት በከንፈር ጉዞ
በግማሽ ሙት ግማሽ ሙሾ፥ በይስሙላ አሰገንዞ፥
ብር ትር ይል የነበረ፥ የደምሽ ሙቀት ቀዝቅዞ
ሸው እልም ይል የነበረ፥ የገጽሽ ውጋጋን በልዞ
የፈገግታሽ መንጸባርቅ፥ ጥርስሽ ፈልሶ፥ ተመዝምዞ
የትዝታሽ ንቃት ፈዞ
የስሜትሽ ብርሃን ቦዞ፥

ከስል አፈር መሰል ቆዳሽ፥ በዕድሜሽ ገጣባ ተተልሞ
የእልፊት ትዝታ መዝገብሽ፥ በአልሞት ባይ ተስፋ ታግሞ፥
ብሌንሽ ቅስሙ ዶልድሞ
በዕድሜ-ምሽት ተጭለምልሞ
በሕይወት ምጥ ተረምርሞ፥

በደቂቅ ነፍሳት ውትብትብ፥ ከቅድመ ዓለም ተጠንጥነሽ፥
በእልፍ-አእላፍ ምእተ-ዓመታት፥ የትውልዴ ድልድይ ሆነሽ
ሰው በመሆን ኪነ-ሰበብ፥ ከዘመን ዘመን አሻግረሽ፥

በጥንተ-ፍጥረት አንቀልባ፥ በፅንስ የፍሬ ዘር ፀዳል
የአጥንቴ ካብ መሰላሌ፥ በተፈጥሮ ምግባረ ቃል፤

እጣሽ ዞሮ ተዳረሰ፥ ቀንሽ ከቀንሽ ተጣባ
አድፍጦ አስታምሞ አዝግሞ፥ ያው ወደ ምድረ-ከርስ አምባ፥

አዴ አዳዩ እመ-ምኔቴ፥ ትከሻሽ ሞት አረበበ
የትውልድ መስታየቴ፥ በረቂቅ ጥሪ ተሳበ...

ጥላው በአናትሽ አንጃቦ
በእርግብግቢትሽ ተከቦ
በሕሊናሽ ገሮ ጠልቆ፥ በአንደበትሽ አኮብኩቦ፤

በሌጣ ጀርባሽ ተጭኖ፥ ፊትሽን ቁልቁል አስተኩሮ
ፍቃድሽን፥ ምኞትሽን፥ የሕልምሽን ቋት ሥርሥሮ
ከዘር እንደተጣባ ዛር፥ በአስትንፋስሽ ፅላት አድሮ
እንደደራሽ ሙላት ቁልቁል፥ ተንደርድሮ አንደርድሮ፥

ከዕለት ዕለት እየጠራሽ፥ እየሳበሽ ወደ ጥንፉ
የዕድሜሽ ልጓም በጁ ወድቆ፥ ተካቶ ሕልውናሽ በእርፉ
ከጥንተ ዓለም መንታ ጉያው፥ ሊያዘርሽ ከፅንፍ እፅንፉ
ሊያከናንብሽ በከንፉ፥...

አንቺም በቦዘ ብሌንሽ፥ አርቀሽ እያስተዋልሺኝ
በግማሽ አስከሬን ጣትሽ፥ በልማድ ብቻ እያሰስሺኝ
አዴ አዳዩ አላይህ አልሺኝ!
በበድን እየዳሰስሺኝ
በደነዘዘ ደመ-ነፍስ፥ ቃትተሻ እያድበለበስሺኝ፥
በርቱእ ሕልው ልቦና፥ አጥርተሽ አላውቅህ አልሺኝ።....
አዴ አዳዩ አላይህ አልሺኝ።

አይሉት ነገር አይባል

ካፍ ከወጣ አፋፍ ነውና፥ ነገር ይሳሳል ይሰፍፋል
ደርሶ ካፍ-አፍ ይገለማል
ይቀላል አጉል ይነፍሳል፥
ያልተናገሩትም እንደሁ፥ ያው ነገር በሆድ ይቆርጣል፥

ይሻላል ማሰላሰሉ
ሳንጣላ መኳረፉ፥ አብሰልስሎ መብሰልሰሉ፣....

ዋ የጊዜ ኬላ በሩ
የትውልድ አጥር ማገሩ፥ ድንበር አለማሻገሩ፤

ዋ ዕድሌ አለመታደሉ
የአንቀልባ ማውረጃ እርካቤን፥ አዳዬን ጃጅተሻል አሉ፤

አዴ አዳዩ እመ-ምኔቴን
የትውልድ መስታየቴን

የሕይወት አማጭ ለበቤን
የመኖር መርገፍ ድባቤን
ዘመን ከዘመን አጠረን
የዕድሜ ግድግዳ ጋረደን
የዕትብታችን ግድብ ለየን።»....

አዴ አዳዩ ብቻሽን ነሽ
ሞት እሚካፈልም የለሽ።

ለአዴና ለጎሮምቲ ጉቴ ዳኛ - (፲፱፻፷- በሎ)

# የት አባቱ ሞትም ይሙት!

እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ስሞት ሞትም አብሮኝ ይሙት
በሳቅ በደስታ ግደሉት
በሃሴት በዕልልታ ውገሩት
ከአጥንቴ በታች ቅበሩት፤
እባካችሁ ዘመዶቼ፥ ለሞት የልብ ልብ አትስጡት
ናቁት አጥላሉት አውግዙት
በሙሾ ግነን አትበሉት
በሞቴ፥ እንዳታስደስቱት።
እንደ ዶርዜ ወንድሞቼ
በሳቅ ታጅቤ ኮርቼ
ሞቴን በዘፈን ሞልቼ
በዳንኪራ ሰበቃና፥ በዘፈን ሆይታ አካትቼ
በሠርጌ ብቀበር ሞቼ
አፀድቅ ነበር ባትረሱ
በእንባ ውሌን ባታፈርሱ።

እባካችሁ ዘመዶቼ፥ በሳቅ ጉዞ ፍታት ፍቱኝ
በሙሾ ዋይታ አታጅሉኝ፤
እናቴም ፈትሽ አይክሰል

በእልልታ ብርሃን ይንበልበል፤

በእረፍቴ አንዳታፌዥብኝ፥

በሥርጌ እንዳታለቅሽብኝ።

ገጽሽ በጭንቅ አይወረስ

ልብሽ በኃዘን አይላበስ

በሆድሽ ሞት አይፀነስ

ፅንባ ባይንሽ አይቋጠር

የሞት ቅስሙ እንዲስበር።

አዎን፥ አደራ፥ አደራችሁ፥ የሙት ውሴን ተቀበሉኝ

ደስታዬን ተካፈሉኝ

ለንስሃ ሞት አደለም፥ ስፍሥሐ እረፍት አብቁኝ፤

በዶርዜ እስክሳታ አሰቀብሩኝ

በአልልታው ጉዞ አሳጅቡኝ

በጦሩ ችቦ አሳጥሩኝ፥

ጭብጨባችሁ በስልቱ ይውረድ

ዛፍ ቅጠሉም አብሮ እሰኪረግድ፥

ሀገር ምድሩ ያቅራራ

ሀሴት ነው ይበል፥ ጀቢራ

ሥርጌ ነው፥ ይምታ ዳንኪራ።

እንዲህ ስሜት ሲፍለቀለቅ፥ ሲፈነድቅ ሲግል ሃሞት

ቱማታው ሲዋጥ በላቦት

ሆይታ በሆይታ ሲራኮት

ማሳለፊያ መግቢያ ሲያጣ*፥ ፍርሃት ገበናው ሲራቆት

መቃረቢያ ፍንጭ ሲያጣ፥ በእልልታ ሲወገር ብሶት...

ብቻ ነው* ሞት ራሱ አሚሞት።

እባካችሁ ዘመዶቼ ሰሞት፥ ሞትም አብሮኝ ይሙት!

በአልልታችሁ ግደሉት

በዳንኪራችሁ ውገሩት

ከአጥንቴ በታች ቅበሩት።

፲፱፻፷፫ - ዶርዜ ሠፈር

# ሰቆቃው ጴጥሮስ

## ከጴጥሮስ - ያቺን ሰዓት ቴአትር

አየ፥ ምነው እመ ብርሃን? ኢትዮጵያን ጨከንሽባት?
ምነው ቀኝሽን ረሳሻት?
እሰከመቼ ድረሰ እንዲህ፥ መቀነትሽን ታጠብቂባት?
ልቦናሽን ታዞሪባት?
ፈተናዋን፥ ሰቀቀንዋን ጣሯን ይበቃል ሳትያት?
አላንቺ እኮ ማንም የላት...
አውሮጳ እንደሁ ትናጋዋን፥ በፋሽሰታዊ ነቀርሳ
ታርሳ፥ ተምሳ በስብሳ
ሂትለራዊ እባጭ ጫንቃዋን፥ እንደኮረብታ ተጭኗት፥
ቀና ብላ እውነት እንዳታይ፥ አንገቷን ቁልቁል ጠምዝዟት
ነፍሷን ድጦ ያሰበረከካት
ሥልጡን ብኩን መፃጉዕ ናት...
እና፥ ፈርቼ እንዳልባክን፥ ሲርቀኝ የኃይልሽ ውጋጋን
አንቺ ካጠገቤ አትራቂ፥ በርታ በይኝ እመ ብርሃን
ቃል ኪዳኔን እንዳልረሳት፥ እንዳልዘነጋት ኢትዮጵያን።
አዎን፤ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ

እሸሸግበት ጥግ አጣሁ

እምፀናበት ልብ አጣሁ፥

እማማ ኢትዮጵያን መንፈሴ፥ ተፈትቶ እንዳይከዳት ሠጋሁ...

አዋጅ፥ የምሥራች ብዬ፥ የትብት ምግቤን ገድፌ

ከናቴ ማኅፀን አልፌ

በኢትዮጵያ ማኅፀን አርፌ፥

ከአፈርዋ አጥንቴን ቀፍፌ

ደሜን ከደሟ አጠንፍፌ

ከወዟ ወዜን ቀፍፌ

በሕፃን እግሬ ድኼባት በሕልም አከናፌ ከንፌ

እረኝነቴን በሰብሏ፥ በምድሯ ላብ አሳልፌ

ከጫጩትና ከጥጃ፥ ከግልገል ጋር ተቃቅፌ፤

በጋው የእረኛ አደባባይ፥ ክረምት እንደወንዙ ፍሳሽ

በገጠር የደመና ዳሰ፥ በገደል ሸለቆ አዳራሽ

ከቆቅና ከሚዳቋ፥ ከዥግራ ጠረን ለተሻሽ፥

በወንዝ አፋፍ ሐረግ ዝላይ፥ መወርወር መንጠልጠል ጢሎሽ

ከፍልፈል ጋር ሩጫ ሰገጥም፥ ከቀበሮ ድብብቆሽ

ከናዳ ጫፍ ሣር አጨዳ፥ ለግት ላሜ ትንሽ ግጠሽ

ለጥጃዬ የሌት ግርዶሽ

ለጥማድ በሬዎች ራት፥ ለማታቸው ትንሽ ድርቆሽ፥

ለግልገሌ ካውሬ ከለል
እማሳው ሥር ጐጆ መትከል
ለፀሐይ የሾላ ጠለል፥ ለዝናብ የገሳ ጠለል፥
ውሎ የንብ ቀፎ ማሰሰ፥ ያበባ እምቡጥ ሲፈነዳ
የግጦሽ ሣር ሲለመልም፥ ሲሰማሩ ሰደድ ሜዳ
አዝመራው ጣል ከንበል ሲል፤ ከብቱ ለሆራ ሲነዳ
ፈረስ ግልቢያ ሰሽመጥጥ ከወፎች ዜማ ስቀዳ
ልቤ በንፋስ ተንሳፎ፤ በዋሽንት ዋይታ ሲከዳ...
ያቺን ነው ኢትዮጵያ የምላት
እመ ብርሃን እረሳሻት?
ያችን የልጅነት ምሥራች? የሕፃንነት ብሥራት
የሣቅ የፍንደቃ ዘመን የምኞት የተሰፋ ብፅአት
ያቺን የልጅነት እናት?
አዛኚቱ እንዴት ብለሽ ጥርሶችሽን ትነክሽባት?

ሰሜን በሰምሽ ሰይሜ ባገልግሎትሽ ሰዋትት
ከዜማ ቤት እቅኔ ቤት ከድጓ ቤት እመጻሕፍት፥
ካንቺ ተቆራኝታ ዕድሌ፤ ካንቺ ተቆራኝታ ነፍሴ
ከቀፈፋ ደጆ ለላም፥ ከቤተ ልሔም ቅዳሴ፣
አኮ፤ ቀፎ ዳባ ለብሶ

ቅኔ ዘርፎ ግሥ ገሦ

መቅደሰ አጥኖ፤ ማኅሌት ቆሞ

በልብሰ ተክህኖ አጊጦ፥ በብር አክሊል ተሸልሞ

እመ ብርሃን ያንቺ ጽላት፥ ነፍሴ ላይ በሳት ታትሞ

የመናኒው ያባ ተድላ፥ ረድ ሆኜ አብሮኝ ታድሞ፥

ሕይወቴ እምነትሽን ጸንሶ

ሥጋ ፈቃዴ ተድሶ

ለሕንፃሽ መዲና ቆሞ፥ ለክብርሽ ድባብ ምሰሶ፤

ስሜን በስምሽ ሰይሜ፥ ሆነሽኝ የእምነቴ ፋኖስ

ለዋዜማሽ ግሸን ማርያም፥ ለክብርሽ ደብረ ሊባኖስ

ስሮጥ፥ በወንበሩ አኖርሺኝ፥ በአንበሳው በቅዱስ ማርቆስ፤

ታዲያን ዛሬ ኢትዮጵያ ስትወድቅ፥ ከምትሰጪኝ ለፍርሃት ጦስ

ምነው በረኝነት ዕድሜ፥ ዓይኔን በጓጐጣት የሎስ

የጋኔል ጥንብ አንሳ ከንፎ፥ ወርዶ በጭለማ በርኖስ።

ባክሽ እመ ብርሃን ይብቃሽ፥ ባክሽ ምሰለ ፍቁር ወልዳ

ጽናት ስጪኝ እንድካፈል፥ የእናቴን የኢትዮጵያን ፍዳ፤

ከነከሳት መርዝ እንድቀምስ፥ ከነደደችበት እቶን

የሷን ሞት እኔ እንድሞታት፥ ገላዋ ገላዬ እንዲሆን።...

አዎን፤ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ

እምፀናበት ልብ አጣሁ።....

ሕፃን ሆኜ የእርግብ ጫጩት፥ አንዳንዴ ራብ ሲያዳክማት
ችጋር ከጐጆዋ ገፍቶ፥ እዛፍ ግርጌ ሲጥላት
እናቷ በርራ ደርሳላት
በአክናፏ ሙቀት ታቅፋት
እፍ እያለች ግንባሯ ላይ፥ ሕይወት ስትተነፍስባት
ወዲያው ነፍስ ትዘራለች
ሽር-ብር-ትር እያለች።
ባክሽ አንቺም አትራቂብኝ
አመ ብርሃን እናቴ፥ ትንፋሽሽን እፍ በዪብኝ
ፅናትሽን እፍ በዪብኝ፥
ወይም ይቺን የሞት ጽዋ፥ ጥላዋ ነፍሴን ካፈናት
እንዳልጠጣት አሳልፊያት
መራራ ክንፏን ገንጥለሽ፤ ቀጠሮ፤ ቃልዋን ግደፊያት፤...
አለዚያም ጽናትሽን ስጪኝ፥ ልጠጣው ኪዳነ-ውሌን
የኔ ፈቃድ እምነትሽ ነው፥ ያንቺ ፈቃድ ብቻ ይሁን።
እንደጳውሎስ እንድጸና፥ በፍርሃት እንዳልታሰር
በውስጤ ከሚታገለኝ፥ በሥጋ አውሬ እንዳልታወር
ለየዕለቱ ሞት አንዳልሰንፍ
የኪዳኔ ቃል እንዳይነጥፍ
ቃልሽ በሕሊናዬ ዲብ፥ ኃይልሽ በሕዋሴ ይረፍ።

ፍርሃት ቢያረብብኝም፤ አንቺ ካለሽኝ አልሠጋም
ኩርትም ብዬ እችልበት፥ እሸሸግበት አይጠፋም
የግማደ መስቀሌን ጉጥ፥ እታገስበት አላጣም፥
አለዚያማ ብቻዬን ነኝ፥ ኢትዮጵያም አላንቺ የላት
አንቺ አፅኝኝ እንድጸናላት።
አስርጨብኝ የእምነት ቀንጃ፥ ለሥጋቴ አጣማጅ አቻ
ለጭንቀቴ-መቀነቻ።....
አዎን፥ ብቻዬን ነኝ ፈራሁ
እሸሸግበት ጥግ አጣሁ -
እምፀናበት ልብ አጣሁ...

፲፱፻፷፩ - ቀበና

# እንቅልፍ ነው እሚያሰወስድህ

"ዝም አልኳቸው ዝም ይበሌኝ

ትቻቸዋለሁ ይተዉኝ

አልነካቸውም አይንኩኝ"

ብለህ፥* ተገልለህ ርቀህ

እውነት ይተውኛል ብለህ

እንዴት ተሰፋ ታደርጋለህ?...

ትሰፋ አርዝሰ ምን ልትሆን፥ ወይስ ተሰፋው ምን ሲሆንህ?

እንቅልፍ እንጂ እሚያሰወሰድህ።

"አልጠራቸውም አይጥሩኝ

አይንኩኝ ስሜን አያንሱኝ'

ብለህ እንዴት ትመኛለህ፥ እንደማይተዉህ ስታውቀው

የተወጋ በቅቶት ቢኛ፤ የወጋ መች እንቅልፍ አለው

የጅምሩን ካልጨረሰው?

የተበደለ ቢችልም

ቢሸሸግም ቢደብቅም

የበደለ ዝም አይልም።

እንዴት አስችሎት ዝም ይበል? ለፍልፎ ከማሰለፍለፉ

አደል እንዴ የሱ ቤዛ፥ የበደሉ ጥቅም የግፉ

ዝምማ ካለ ጉድ ፈላ

ነገር በጤና ሲብላሳ

እያደር ሲጣራ ኋላ

ግፉ ይፋ ይሆናሳ...

ሰላምማ ከለገሡህ

ሕመምህ እየታወሰህ

ትዝታ እየቀሰቀሰህ

የሕሊናህ ሚዛን ረግቶ ጉዱ ሁሉ ኩልል ሲል

ያደፈረሰው ሲያጠልል

እግዜር ያሳያችሁ ብለህ፥ ፍረዱኝ ዳኙኝ እንዳትል

ከነአካቴው ሳይጨርሳላህ

ምን ቢሆን ሰላም አይሰጥህ።

እሱስ ቢሆን ያለትክሉ፤ ያላጥንቱ የሰላም ውርሰ

ከቶ የማያውቀውን ቅርስ

ይሰጠኝ ብትል የት ይሆናል

ያልተዘራ መች ይዘቅላል?

የጓሮ ጐመን ሲያጢላ

አጥፊ ትሉን እንዲያፈሳ

እንዲያው በነገረ ቀደም፥ እንደሱስ ለሙን ቢለፍፍ

ስላምን የሰጠህ መስሎህ፤፥ በጉጉት ሲታሰፈስፍ

ተለሳልሰህ እንደቃተትክ፥ ተስፋ አርገህ እንዳትል እርፍ።

እና ዘበት ነው ጥረትህ

በከንቱ ተሰፋ ማድረግህ

ላያዋጣ መመኘትህ

የሰላም ቅዥት ማየትህ

ምን ልትሆን? ምን ሊሆንህ?...

ይቅርብህ። በኔ ይሁንብህ

እንቅልፍ ነው እሚያሰወስድህ።

ለኤድዋርዶ ሞንድላን - (፲፱፻፶፱ - ዳሬ ሰላምነ

# እሳት ወይ አበባ

እና፥ እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት ዓይኑን የታወረ

እግረ ሕሊናው የከረረ፥

ባሕረ-ሃሳቡን ያልታደለ

የውበት ዓይኑ የሰለለ

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ አበባ እኮ አደለም አለ።

ያልታደለ።

---

ሌት ከዋክብቱ እንደፀደይ

አጥለቅልቆን በቀይ አደይ፥

ሰማዩ ሥጋጃ አጥልቆ

ተሽለምልሞ አንፀባርቆ

ፈክቶ፥ አሽብርቆ ደምቆ

በአዝመራ፥ በአጥቢያ ዐፀድ ሰፍኖ

በዓደይ አዝርእት ተከሽኖ

በእንቁጣጣሽ ሰብል ታጥኖ

ኢዮሃ አበባዬ ሆኖ፥

ጨረቃዋ ከቆባዋ ከሽልምልሚት እምቡጧ

ጧ ብላ ከሰንኮፈንዋ፥ ተንዠእግጎ የእንኩይ ቡጧ፥

ድንግል ጽጌ-ረዳ ፈልቃ

ፍልቅልቂት ድምብል ቦቃ....

ተንሠራፍታ የአበባ ጮርቃ፥

ታድያን ብሌኑ የጠጠረ

ባሕረ-ሃሳቡ የከረረ

የውበት ዓይኑን የታወረ

ልበ-ሕሊናው የሰለስ

አይ፥ አበባ አደስም አለ

አይ፥ እሳት አደለም አለ

ያልታደሰ። ...

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት አደል ብሎ ካደ

እቶን በዓይኑ እየነደደ።

ከዋከብቱ እንደችቦ

በነበልባል ወርቀ ዘቦ

ከፅንፍ ፅንፍ አውለብልቦ

ደመራው እየተመመ

እየፋመ እየጋመ፥

ደመና እንደ ንዳድ ሲነድ

መንጸባርቅ ሰደድ ሲወርድ

በራሪ ኮከብ ተኩሶ

በአድማሳት እሳት ለኩሶ...

ይኸ እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት ዓይኑ የሰሰለ

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት እኮ አደለም አለ፥

ያልታደለ፤....

---

ይቅር ብቻ አንናገርም፥

እኔና አንቺ አንወያይም፥

ለውይይት አልታደልንም

እንዲያው ዝም እንጂ፥ ዝም ...ዝም።

አበባ አንሆን ወይም እሳት

ተጠምደን በምኞት ቅጣት

ሰመመን ባጫረው መዓት

ዕድሜአችንን እንዳማጥናት....

እሳት አንሆን ወይ አበባ

በሕቅ-እንቅ ስንባባ

ባከነች ልጅነታችን፥ እየቃተትን ስናነባ፡።....

ፈራን፤ አዎን ፍቅር ፈራን፥

የነፍስን አንደበት ዘጋን፥

የዕድሜ ጠብታችንን ምጥ፣ የጣር ፅንሳችንን ልሣን፥

ልጅነት የለገሠንን

በመለኮት የቀባንን

በእሳቱ ያጠመቀንን

የፍቅር አምላክ በጥበቡ በሥልጣን ያለበሰንን

ፈራን፥ አዎን እውነት ፈራን

የስሜት እሰትንፋስ ነሳን።.

---

ብቻ ለይቶ ላይለየን

በእንፋሎት ላብ እያጠነን፥

ዓይን ለዓይን እየገደበን

ወይ አቅርቦ ላያቀርበን

በይሉኝታ አጥር እያጠረን

በአሉ ቧልታ እየለየን

በይስሙላ እየከፈለን፥

እሳት ሳንሆን ወይ አበባ

ተገድበን አምባ ለአምባ...

እኔና አንቺ አንናገርም

ቢያመንም አንወያይም

እንዲያው እርጭ፥ ጭጭ፥ ዝም።

በቃሽ ትዝታሽን ማሪኝ

የሕልም-ሕመምሽን ታረቂኝ፥....

ዓይንሽ ዓይኔን ሙት እንዳለኝ፣ ሰመመን ተግሣፅ ከሰማ

ሙት እንዳሉት ከሞተማ

ሂድ ቅር ሲሉት ከቀረማ

ይሉኝታ ካደመጠማ

ሲነቀፍ ከታዘዘማ

አሜን፥ ይቅር እንግዲያማ፥

ይቅር የወፎቹም ዜማ፤

ይቅር ጨረቃንም አናይ

ከቶ ላም አለኝ በሰማይ

ብኩን አይጨበጥ ሢሳይ

አይቀርም እንጂ ከቀረ፥ ይቅር ሲሉት ከቀረማ

አይሞትም እንጂ ከሞተ፥ ሙት እንዳሉት ከሞተማ፤...

አማን አልነበረም ያማ።

በይ ሕመምሽን ታረቂኝ

ሰቀቀንሽን ተማጸኚኝ

ሰመመንሽን ይቅር በይኝ

እምትምሪኝ ከሆነማ፥ ማሪኝ ትዝታሽን ማሪኝ፤...

---

ምነው ታድያን ድምፅሽ ራቀ?

ምነው ልሣንሽ ረቀቀ?...

የዓይንሽ ብርሃን ቀለስ አለ፥ የእንባ ወዝ እንደቋጠረ

ቃጥቶ እንደተውተረተረ

የመከራ፥ የጭንቅ የምጥ፥ ስልባቦት እንዳቀረረ

የደም ወዝ እንደነዘረ

እንደተሰቀቀ ቀረ?...

ምነው እንባሽን በጠረኩት

ምነው ወዝሽን በዳሰስኩት

ምነው ያይንሽን ውጋጋን፥ ነበልባሉን በቀረብኩት

መንጸባርቁን በሞቅኩት...

ምንም እንኳን ባልደርስብሽ፥ ባልቀርብሽ፥ በሃሳብ አንቅቼ

በእስትንፋስ ተንጠራርቼ

ብደርስብሽ፥ ብዳስስሽ፥ የነፍሴን ሕዋስ ዘርግቼ

የረቀቀብኝ ፈለግሽን፥ ጠረንሽን በምጥ አሽትቼ

እንደጽላት ፋናሽ ግርጌ፥ ገጹን ግንባሬን ደፍቼ፥

የተሳለምኩብሽ ትቢያ፥ እሳት አትሆን ወይ አበባ

ያለፍቅር እንባሽ ላይረባ

ያለሰመመን ወለባ

ቡጡ ካልተንዠረገገ፥ ካልተፍለቀለቀ ቅሰሙ

የነበልባልሽ የፍሙ

የቆባሽ የሰልምልሙ

የብሌንሽ የመብራቱ

የወሰፈንጥርሽ የእሳቱ

የገጽሽ የእቶን ግማዱ

የፍላፃሽ የንዳዱ.....

አረ ይብቃን መቃጠሉ፥ በዓይን ወላፈን መለብለቡ

ያለፈርጁ ያለባሕሉ፥ እሳት አይጭር ሰው በቀልቡ

ፍም አዝሎ ላይዘልቅ ልቡ፥

አጉል ምን አቀጣጠለን

አሰቀድሞ ሳያድለን?

በሰመመን ሟሟን እንጂ፥ በመውደድ ለምልሙ አላላለን።....

ድባብ እንደራቃት ቆሌ

ባህር እንደገባ አሞሌ

እንዲያው በሕልም አባይ ገነን፣ ለቅዠት መራወጥ ፎሌ

ኣረ ወዲያ ይብቃን ይቅር

ይኸ የዓይን አዋጅ ብር ትር

ወዝ አይወጣው ድብን እርር......

አበባ አንሆን ወይም እሳት

ተቅበዝብዘን በሃሳብ ምትሐት

ለጽድቅ አልበቃን ለኃጢአት

ለነፍስ ወይ ለሥጋ ብፅዓት

ወድቀን በሕልም ዓለም ቅጣት

ፈርስን በሰመመን መዓት...

ታዲያን ምን መናገሪያ አለን? ድዳው ልባችን ዋይ ይበል!

ዕውር ነፍሳችን ይንበልበል

እስትንፋሳችን ይቃጠል

እንጂ.... እኛማ ተረግመን

መቸ መነጋገሪያ አለን?

የእርግማን ቢሆን ነው አዎን፥ እንጂ ከየት መጣ ዐመሉ

ላንዲት ፋታ ሳንጠቀም፥ በደሰታ ጐሕ በፀበሉ

በብርሃኑ በፀዳሉ

በአሉ ቧልታ ለሰም ብቻ፥ ለይሰሙላ መደለሉ?

የተደሰትን ማሰመስሉ

ለማሰመሰል መታለሉ?

በፍቅራችን መዋሸቱ

በነፍሳችን መዶለቱ? በፍቅራችን ግፍ መዋሉ?

እርግማን እንጂ ትርጓሙ

ሌላ ምን ሊባል ነው ሰሙ?

አንቺም የወግ ገባር ሆነሽ፥ እኔም የይሉኝታ ባሪያ

የልብን ወሰፈንጥር ጮራ፥ ደፍነን ለሃሜት መደለያ

የመውደድን ቆባ ኬላ፤ የፍሥሃን መጥለቅለቂያ

የሲቃን የምሥራች በር፤ የእልልታውን መታበያ

የፍቅርን እቶን ሰንኮፈን የጣር የምጡን ገበያ

የነፍሰን የእርግብግቢት ፍንጭ የምጣችንን ማጥለያ፤

የመውደድን ቆባ ገፍፈን

ሽሉን በአመዳይ ለብልበን

ዲካውን በጢሰ አፍነን

አውተፍትፈን፥ አድበሰብሰን፥ አንገዋለን ምሰን ቀብረን

ከቶ ለኛ እንዳይታደግ

እንዳያብብ እንዳያሠርግ

የመውደድን አምላክ ፈለግ

ቀብረን በይስሙላ በወግ

አልተረገምንም ካልንማ፥ ሞት እንጂ ሕይወት ካላየን

ያለፀጥታም ድምፅ የለን...

ባያድለን.... ባያድለን።....

ያውም ይኸ አልበቃ ብሎን፥ ሞትን እንደፍቅር ፀንሰን

የወግ የማዕረግ እጣቢ፥ የጉራ መሰዋዕት ሆነን

መውደድን በለም ገንዘን

በይሰሙላ ጢሰ አፍነን

ላፍ ዳረጐት ፍቅርን ከደን

ውቃቢያቸው አምላካቸው፥ ያይብናል እንላለን!

ይባላል፥ አዎን ይባላል

“ይታደሏል እንጂ መቸስ፥ ዕድልን መች ይታገሏል?" ....

መውደድ ለሞት አደግድጎ

ለዕድር ወግ ለዕቁብ ለሸንጎ

ለተዝካር ለፍትወት ድርጎ

ለአደባባይ ይምሰል ልቅሶ

ለእውነት ውጦ ለሃሰት ቀምሶ

ለይሉኝታ ተለባብሶ፤....

አልተረገምንም ካልንማ፥ ሞት እንጂ ሕይወት ካላየን

ያለፀጥታም ድምፅ የለን

ባያድለን... ባያድለን።....

አንቺም ከሌላ ጋር ብትውይ፥ እኔም ከሌላ ጋር ብውል

ባምሳያ እንጂ ላንቺው ሥዕል

የኔ ልኬ ካንቺ ሳያልፍ

በሌላ አካል አንቺን ለማቅፍ፥

ሌላዬቱን ባንቺ አምሳያ -

የሥጋ ምሴን ልወጣ፥ ያንቺን ሕመም በሷ ሳቢያ፤

በገላዋ አንቺን እያየሁ

በዓይኗ ዓይንሽን እያሰብሁ

በጠረኗ አንቺን እያሰሰኩ

በአካልዋ አንቺን እየዳሰሰኩ
ሰምሽን ከስሟ እያሳከርኩ
በእስትንፋሷ እያነበነብኩ
አንቺን በሷ ውስጥ ካቀፍኩ
በማኅፀኗ አንቺን ከፀነሰኩ፥
በሰው ቅርፅ አንቺን አንጬ
በሰው ጭንቅ አንቺን አምጬ
እሷ ያንቺ ቋት ሆነቺኝ
በሥጋዋ አንቺን ሰጠችኝ፤
እያየሁ አሷን ሳላያት
እያቀፍኩ እሷን ሳላቅፋት
አንቺን አይቼ በሷ አካል...
አንቺን አቅፌ በሷ አምሳል
እያየሽው የግፍ ግፌን
በሰው ኃጢአት መዋሌን
ዕቃ አድርጌ መጠቀሜን
በሰው ሥጋ አንቺን ማቀፌን...
ምነው ደርሶብሽ አይተሽው
የኔን ግፍ በሰው ውለሽው
የፍትወት ግብር ልትከፍይ፥ የፈጸምኩትን ፈጽመሽ

በሰው አካል እኔን አቅፈሽ

በሰው ጭንቀት እኔን ፀንሰሽ፤

መውደድን ለወግ ማገዱ

ፍቅርን ለቧልት መካዱ

ሳንደሰት ደስ እንዳለን

ለይስሙላ አሰመስለን

ውቃቢያቸው አምላካቸው፥ ያይብናል እንላለን!...

አልተረገምንም ካልሽማ፥ ሞት እንጂ ፍቅር ካላየን

ያለፀጥታም ድምፅ የለን።

እሳት ሳንሆን ወይ አበባ

ዘር ነሰቶን ለወግ ገለባ

ፍሬ አጥተን ለወሬ አላባ

ለጉጉት ሽል ስናደባ፥

አበባ አንሆን ወይም እሳት

ተስለምልመን በእውነት ፍርሃት

ሳንኖር በሙት ሕይወት ሥጋት

ወይ ሳንሞት በቁም-ሞት ፍትሐት

ተይዘን በሃሳብ-አታምጣ

በ-አይነግሩት የቁም ሰቅል ዕጣ

ከቶ ሳያሸት ባጨጨ

ላይጠጣ በመነጨ

ሳይፈጠር በተቀጨ፤...

የኛን ከቶ አይወለድ ፅንስ

አፍ አይነካው የጽላት ጥቅስ

የሕመም የሰመመን ውርስ

የኛን ሾላ በድፍን ቅርሰ

እኔና አንቺ አንወያይም፥

በሞት አፍ ብናገግምም

በምጥ ጦር ብንሰበርም

ዝም እንጂ አንነጋገርም

እንናገረው የለንም።

ምኞት ብቻ ነው እሚርበን

ላናገኘው ላያጠግበን፤

ዕጣችን በጣር ታግሞ

በዘለዓለም አረምሞ፥

እሳት አንሆን ወይ አበባ

እንዲያው በልብ የምጥ እንባ

ተከናንበን ስናደባ

ተሸሽገን ሰናነባ...

ዓይኔ አንቺን፥ ያንቺ አኔን ሲሰብ

ለዓይነ-ሥጋሽ የጧፍ ምግብ
ላናገኘው ላንጠግብ
ያንቺ እኔን የኔ አንቺን ሲያርብ....
ልጅነትሽን ሳታካብች፥ ዕድሜሽን ምን ሳትሠሪበት
አባከንሺው ባከንሽበት፥
ልጅነቴን ሳላካብት፥ ዕድሜዬን ምን ሳልሠራበት
አባከንኩት ባክንኩበት፤
እግዜር የሰጠኝን ዕድሜ
ሰንጀባረር አጣጥሜ
አበባዬን ላቤን ወዜን
የልጅነት ቆባ ቁቤን
ምን አረኩት? ምን አረግሺው?
አባከንኩት፥ አባከንሺው፥
ባከንሽበት፥ ባከንኩበት።
ተሰፋና ምኞት ለጸጋሽ ማዕጠንቱን ብቻ ሳውቅበት
ነፍሴን ለነፍስሽ መስዋዕት፥ ግዳይ ሰጥል ባደግሁበት
ሰሞገሰሽ ሃሌ-ሉያ፥ ለአድባርሽ በሰገድኩበት
ሳንፈጠር በሞትንበት
ሳናብብ በረገፍንበት
ሳንጠና ባረጀንበት

አበባ ወይንም እሳት፥ መሆኑን ብቻ አጣንበት።...

---

ታድያን እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት ዓይኑን የታወረ
እግረ ሕሊናው የከረረ
ባሕረ-ሃሳቡን ያልታደለ
የውበት ዓይኑ የሰለለ
ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ አበባ እኮ አደለም አለ።
ያልታደሰ፡፡....
ሌት ከዋክብቱ እንደፀደይ
አጥለቅልቆን በቀይ አደይ
ሰማዩ ሥጋጃ አጥልቆ
ተሸለምልሞ አንጸባርቆ
ፈክቶ፥ አሽብርቆ ደምቆ
በአዝመራ፥ በአጥቢያ ዐፀድ ሰፍኖ
የዓደይ አዝርእት ተከሽኖ
በዕንቁጣጣሽ ሰብል ታጥኖ
ኢዮሃ አበባዬ ሆኖ፥
ጨረቃዋ ከቆባዋ ከሽልምልሚት እምቡጧ
ጧ ብላ ከሰንኮፈንዋ፥ ተንዣርግጎ የእንኮይ ቡጧ፥
ድንግል ጽጌ-ረዳ ፈልቃ

ፍልቅልቂት ድምቡል ቦቃ....

ተንሠራፍታ የአበባ ጮርቃ፥

ታድያን ብሴኑ የጠጠረ

ባሕረ-ሃሳቡ የከረረ

የውበት ዓይኑን የታወረ

ልበ-ሕሊናው የሰለለ

ኣይ፥ አበባ አይደለም አለ፤

አይ፥ እሳት አይደለም አለ፤

ያልታደለ።....

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት አደል ብሎ ካደ

እቶን በዓይኑ እየነደደ።

ከዋክብቱ እንደችቦ

በነበልባል ወርቀ ዘቦ

ከፅንፍ ፅንፍ አውለብልቦ

ደመራው እየተመመ

እየፋመ እየጋመ

ደመና እንደንዳድ ሲነድ

መንጸባርቅ ሰደድ ሲወርድ፥

በራሪ ኮከብ ተኩሶ

በአድማሳት እሳት ለኩሶ...

ይኸ እንደኔና እንዳንቺው፥ የውበት ዓይኑ የሰለለ

ሰማይ ጨለማ ነው እንጂ፥ እሳት እኮ አደሰም ኣለ፤

ያልታደለ፡፡፡....

---

ይቅር ብቻ አንናገርም፥

እኔና እንቺ አንወያይም፤

ለውይይት አልታደልንም

እንዲያው ዝም፥ እንዲያው ዝም.... ዝም።

አበባ አንሆን ወይም እሳት

ተጠምደን በምኞት ቅጣት

ሰመመን ባጫረው መዓት

ዕድሜአችንን እንዳማጥናት፤...

እሳት አንሆን ወይ አበባ

በሕቅ እንቅ ስንባባ

ባከነች ልጅነታችን፥ እየቃተትን ሰናነባ።

ሳንፈጠር በሞትንባት

ሳናብብ በረገፍንባት

ሳንጠና ባረጀንባት

አበባ ወይንም እሳት፥ መሆኑን ብቻ አጣንባት።

ለአሳምነው ገብረ ወልድ - (፲፱፻፷ - አራት ኪሎ)

# አስቀመጡህ አሉ!

እኮ ስምህን ማን ብለው?

አሁንም "“የሉሉ አባት" ነው?...

ወይስ አዲስ ቀየሩልህ? ሰየሙህ ዳግም አጥምቀው?

እንደ አንኮል ማንጠልጠያ፥ በጥሰው ሌላ ቀጥለው?

“አስቀመጡሀ" ብለው አሉኝ፥ በል እስቲ ይኸ አማርኛ ነው?

አንተና እኔ የምናውቀው?

ወይስ ዘመኑ ወሰደው?...

እኔማ አላመንኳቸውም፤ በዚህ በቋንቋ ጋጠ-ወጥ

ላማጥላላት ለሟሸሟጠጥ

“የሉሉ አባት-የሉሉ እናት” ፥ ብላን ሰንቆለማመጥ

ፍቅራችንን ለማንጓጠጥ

ትዳራችን እንዲናወጥ

ልጃችን ቅሰሙ እንዲቆረጥ

የተደረገ ዘዴ ነው፥ ቀንተው የሠሩት መበለጥ

እንጂ ተቀመጥክስ ቢሉኝ፡-ምንህ ምኗ ላይ ሊቀመጥ?

ደሞሰ ሰምህን ማን ሊሉት

አሁንም “የሉሉ አባት" ነው፥ ወይስ ቆርጠው ሊቀጥሉት?

"አስቀመጡህ ብለው አሉኝ”

አጉል ነግረውኝ ላይጠቅሙኝ

ሊያሳዝኑኝ፥ ሊያስተክዙኝ...

እኔማ አላምንም አልኳቸው፥ ለአፌ እንኳን እንዳልሳሳት

ለምን ደስ ይበለው ጠላት፥

መዘባበቻ እያረገ፥ ለምን ይሳቅ በኔ ጥቃት

አንተም ሃሰት ነው በላቸው፥ እባክህን የሉሉ አባት።

አስቀመጡህ ብለው ቢሌኝ፥ ጥላ ድባቤ ተደፋ

አለኝታዬ አዋዩ ጠፋ

ቀንም የሃሜቱ ሹክሹክታ፥ ሌት ብቸኝነቱ ከፋ

ቀየአችንም ቀዘቀዘ፥ ጐጆአችንም ነፋስ መታው

ሉሉም ጥርጣሬ በዛው

የኔንም ተስፋ ዕድሜ ገባው፥

ንብረታችን ወሬ ንዶት

ትዳራችን ቆፈን ውጦት

ስሜቴም ወዙ ተጣጣ

መካበቻዬ ዋስ ቢያጣ፤

መመኪያዬ ተከተተ

ዕጣ ክፍሌ ተሸለተ

ገበናዬ ተራቆተ፤

እባክህን የሉሉ አባት፥ እኔን ባትምር ስሜን ማረኝ

መታወቂያ መጠሪያዬን ስሜን ብቻ ይቅር በለኝ

ባይሆን የሙት ሚስት ይባሉኝ፥ የቅምጥ ሚስት አታሰኘኝ፤...

ጥሞናህ እንኳ ቢሸሽኝ

ልቦናህ ባያስታውሰኝ

በስም እኮ የሉሉ እናት ነኝ።

እና ባክህ ተሰመነኝ

ስሜን እንኳ እታሳድፈኝ፥

የሙት ሚስት ነው እሚሻለኝ

የቅምጥ ሚስት አታሰኘኝ።

አዎን በኔ ይሁንብህ

እኔና ሌሉ ነን ስምህ

ከኛ ወዲያ ማን ሊያውቅልህ?

ብትሞትስ እንደኛው ያህል፥ ካንተ ሞት ማ ሊጋራልህ?

እንደኛው ሆድ ማ ሊባባ?

እንደኛው እንባ የማ እንባ?

እንደኛው አንጀት ማ ቆርጦት?

እንደኛው እጦት የማ እጦት?

እና በኔ ይሁንብህ

የኔም የሉሉም ነው ስምህ።

የቅምጥ ልጅ፣ የቅምጥ ሚስት፣ መባል ሽታው እያስጠጋም

የእውነት ሞት ግን ከቶ አይኾፃም
ቅስም ሰብሮ አይቀረናም
የስም ሞት ነው ክብርን እሚያም።
ያም ሆኖ እኔ አልተቀበልኩም
ነገራቸውን አእልዋጥኩም
ምንም በግትር አንደበት፥ እስቀመጡህ ብሰው ቢሉም
እስካሁን በጆሮዬ እንጂ፣ በልቦናዬ አልሰማሁም።
ምንም ቢሆን የሉሉ አባት* ውሰት እንዳመቸው ዶማ
ግርዶሽ እንዳወዛው ሲናር፥ እንደ ወዶ ገባ ኮርማ
ተነስ ሲባል ብድግ የሚል፥ ተኛ ሲባል የሚተኛ
በዳረጐት እንደፋፋ፥ የፍርፋሪ ሱሰኛ
ጉልበቱን ለጉርሻ ግብር፥ እንደሸጠ ቀሰብተኛ
አደለም ብዬ ክጃለሁ። ነገሩ ባይዋጥልኝ፥
እመፒብኝ ብለኸኛል፥ እወቅልኝ ባታውቅብኝ
ባይሆን የሞትን ክንድ እንጂ፥ ውርደት ማቀፍ አይሆንልኝ
ዋሸቺ እንደሁ የሉሉ አባት+ ዋሾ ብለህ መስክርብኝ።
መስክርብኝ የሉሉ አባት፥ ባንተ አም አልሰሳሰስ
ምን አባቱ እርሜን ሳውጣ፥ እምነት ቢሞት አይታደስ
አሳማ ነው እንጂ ጨዋ፥ ወደ ትፋቱ አይመለሰ
ያስቀመጡህ ቢያስቀምጡህ፥ ልቤ ነው እንጂ እውነት አትፈርስ።

የተሰማውስ ቢሰማ

በነጋሪት ቢያስተጋቡት፥ ባፍ ሹክሽክታ ቢገለማ

ስም እንጂ ፍቅር አይገማ።

፲፱፻፷፩ - አምቦ

# አባይ

አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ
የቅድመ-ጠቢባን አዋይ
አባይ የጥቁር ዘር ብሥራት
የኢትዮጵያ ደም የኩሽ እናት
የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ
ከጣና በር እስከ ካርናክ
በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ
ለራህ ለፀሐዩ ግማድ፥ ሰጣህ ሰከዋከብት አምላክ
ከጥንተ-ፍጡራን ጮራ፥ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ።

አባይ የምድረ-ኩሽ መኩሪያ
በቅድሙታሪክሽ ጥርጊያ
ከደም-ቢያ እስከ ኑ-ቢያ
ከሜምፊስ እስከሜሮኤ
በሥልጣኔሽሽ ትንሣኤ
ከዴልታሽ እስከ ዴር-ሥልጠን
ከኡመ-ራህ እለከ ኡመ-ዱርማን፤
አባይ የአቴስ የጡቶች ግት
ለዓለም የሥልጣኔ አምብርት፤

ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ

የካም የሥልጣኔ ፍንጭ፤

አንቺ የምድረ ዓለም ሲሳይ

በረሃውን ጥለሽ ግዳይ

ሰሃራን እንዳከርማ ተልም

ሰንጥቀሽው በወዝሽ ደም፥

በጥበብሽ ሥርውፍና

አንቅተሽ ባንቀልባሽ አዝለሽ፥ የቅድመ ታሪክን ዝና

የራምሴስን አበ-ሲሞቦል፥ የመነስን ልዕልኖ

በአልፉ የአልሙጋን ሐውልት፥ የቢያ-ሃንኬን ፍልስፍና

በኮማምቦ የሶባቃን፥ በናፖታም የኤዛና

ፊላኤ የአቴስን ምኩራብ፥ በልቅጻር የአሞንን ዜና፤

አባይ ታላቅ ቅድመ-ተስፋ

የኪነት ጉባኤ አልፋ፥

ረቂቅ አባይ ያንቺ መገን

ምጥቀትሽ አይተንተን፥

የእጅ ማስነሻሽ በረከት

ግብርሽ ከአድማሳት ሲከትት

መንጣለያሽ ከዕለት ዕለት

መሻገሪያሽ ካመት-ዓመት

በመስዋዕት ሲወድቅልሽ

በዝማሜ ሲፈስልሽ

በመመለክ በመመስገን

ጽላትሽ ከዘመን ዘመን

በአዝርእት አበቅቴሽ ሲታጠን

አቤት አባይ ላንቺ መገን፤

አባይ ረቂቅ የጠቢብ ዘንግ

የከዋክብትን ሠልፍ ደርግ

የጨረቃን ጉዞ ፈለግ

አስቀምረሽ በጠቢብ ዘንድ

በፍሳሽሽ ውጣ ውረድ

በሙላትሽ ሚዛን ረገድ

የሰማይን ጥርጊያ መንገድ፥

የጊዜ መለኪያ ስዓት፤ ዚኒት ባንቺ ተቀምራ

ከቴቤስ እስከዳንዳራ

ብሥራትሽን እንደደመራ

ሥልጣኔሽ እንዳበራ፥

የመጽሐፈ-ሙታን ዜና

አድርጐሽ ቅድመ-ገናና

ዛሬ ወራቱ ራቀና

ምድረ-ዓለም ያንቺን አድናቆት
ፈለጉን መሻት ተስኖት
እንዲህ ባንቺ መንከራተት
ታሪክ ወሮታሽ ጠፍቶበት
ትላንት በባዕድ ጩኸት
ዛሬም ባላዋቂ ሁከት
ቋንቋ ለቋንቋ ቢራራቅ
የቅድሚያሽ ንድፍ ላይፋቅ
ኣዚህ ደማም እዚያ ተማም
መባልሽ ብቻ ባይበቃም
የቅርስሽ ጭብጥ ይዞታ
ሆሄታሽ እስካልተፈታ
አባይ ፋናሽ የሕልም ርቅ
ፈለግሽም ቢሆን ደቂቅ
እንዴት እንዴት ነበር ብለን
ካልደረስንበት ፈልፍለን፥
የጥንቷ አባይ እንዴት ትሆን
አባይ-አቢይ አባይ-ግዮን
ከምንጩ የጥበብ ሳሎን
ግሪክ ፋርስና ባቢሎን

ጭረው በቀዱበት ሰሞን፤

አባይ የአማልክት አንቀልባ

የቤተ-ጥበባት አምባ

ከኩሽ የቅድመ-አበው ብሁል

ከተራራሽ አናት ቁልቁል

የሰው ዘር የታሪክ-ፊደል፥ ገና ከፅንሱ ሲረቀቅ

ሲሰይም የእትብቱን ቆባ፥ ምጥቀቱን ለማንጸባረቅ

ዘለዓለሙን ለማሳወቅ

እሰከሜዲተራኒያ፥ ጢሰ እሳትሽ ሲፍለቀለቅ፥

ዓባይ አቢይ፥ ዓባይ ግዮን

ለአማልክቶች አምላክ ለአሞን

የኪነት ምንጩ እምትሆን፤

ለኦሩስ ርቱእ አክናፋት

ለነዳዮናይሶስ አባት

ከእምብርትሽ የፀሐይ ኣምላክ፥ ተቀሰቶ በሰማያት

ያረበበብሽ እንደ እሳት፤

ጥቁር አባይ የጥቁር ምንጭ

የካም የሥልጣኔ ፍንጭ

የቅድመ ታሪክሽ ጥርጊያ

ከደም-ቢያ እሰከ ኑ-ቢያ፥

የኢትዮጲስ ደም የኩሽ እናት

አባይ የጥቁር ዘር ብሥራት

የዓለም ሥልጣኔ ምስማክ

ከጣና በር እስከ ካርናክ

በጡትሽ እቅፍ እንዲላክ

ሰራህ ለፀሐዩ ግማድ፥ ሰጣህ ለከዋክብት አምላክ

ከጥንተ-ፍጡራን ጮራ፥ የመነጨሽ ከኩሽ አብራክ፤

ሰሃራን እንደምሁር ተልም

ያለመለምሽ በወዝሽ ደም

የቅድመ-ጠቢባን አዋይ

አባይ የምድር ዓለም ሲሳይ።

ለየኔታ አሥረስ የኔሰው - (፲፱፻፷፬-ቴቤሰ፣ ሙታን-ከተማ)

# መሄዴ ነው

ባር ባር አለ ሆዴ፥ ልቤ መሬት ለቆ
ሊያከንፈኝ እንዳይሆን፥ አለግብሩ መጥቆ
አለአስተዳደጉ፥ አለባህሉ ወድቆ።

ሸው እልም ሸው እልም፥ ልቤ ወፌ-ይላላ
በመስተፋቅር ቀስት፥ በሮሮ ምህላ
እንደደመና አክናፍ፥ እንደጮራው ጥላ
ሸው እልም ሸው እልም፥ ሸው እልም ይላላ።

ነሸጠው፥ ሸፈጠ፥ ሄደ ሸመጠጠ
በመስተፋቅር ጦር፥ በሮሮ አመለጠ።

፲፱፻፷ - ቤልግሬድ

# ዶጋሊ

ምፅዋ አፋፍ ላይ ምጥ - ፅዋ
ዶጋሊ-ግለት ህሩርዋ
ከእለት ፍርኩታ ከሜፍዋ
ቆሟል ቃፊር ጠባቂዋ.

ቀ!
ምነው ብቻህን አሉላ
በንዳድ እምትቆላህ

"ቱርክ-ፓሻው" ኩሩ አበሻ
ብቻህን በእሳት ፍል ዋሻ

ግንባርክን እንዳኮሰተርክ ኣቅጣጫህን ሳታላቅቅ
በዶጋሊ ጣር ብርቅርቅ
ዕፁብ ድንቅ ኣሉላ ዕፁብ ድንቅ
በዚያ በምጥዋህ ንዳድ በዚያ በአዱሊስ እሳት ጭንቅ
በእቶን ጥሩር፥ በምድር ፍም ትጥቅ
ቃፊርክን ሳታፈራርቅ
ምነው አሉላ ብቻህን፤ ብቻህን እምትጠብቅ....

፲፱፻፹፫ ጉርጉስም

# ቦረን (የሙርቲ-ጸሎት-ጥሪ)

፤ ሃይ ሃይ!

ጸጥታ ይሁን...

አንተ የሠራህ ሁሉን

አምላክ ጋዳን ባርክ፤

ጋዳን ባርክ አምላክ

ጋዳ-ሉባን ባርክ፥

ሃሳብን አጥና

ፈረስን አቅና

እምቦሳን አጥባ

ጊደሩን አርባ

ኮርማውን አስባ

ምድሪቱን አጽድቅ

ጠላትን አድቅቅ

ዝሆን-ጐሽ አድቅቅ

ጦርን አቅናልን

ግዳይ ጣልልን

ምርኮን አግባልን

ማርዳውን አጥልል

ጸጋን ለኛ አክል

ሥርዓቱን አውል

በዐሉን ዐድል

በዐሉን ዐድል....

ቀጥል!

፤ ሃይ ሃይ!

ጸጥታ ይሁን...

ለማዳ ጋልማ - አባ ጋዳ - (፲፱፻፷፱ - ዲሬ)

# ውሸታም

እሷ የደም እሳት የላት!

እኮ ትዝታ'ኮ ለካ፥ ክቶውኑ ቅድሰት ናት

ምንም ሕመም አይሰማት

እሷን፥ የእግዜር ፍቅር እንጂ፥ የሰው እሳቱም አይሞቃት!

ብቁ ናት ለካ ፍጹም ናት።

እነሱራፌል ኪሩቤል በእሳት ሠረገላ ወርደው

በመለኮት ብርሃን አቅፈው

በአክናፋት አኮቴት ቀዝፈው

በኅብር አዝለው አንከባክበው

ሰባቱን ሰማያት መጥቀው

ሽቅብ ይዘው፥ ሽቅብ ይዘው....

አዎ ትዝታ'ኮ ለካ

በሥጋዌ ልቡሰ ሕመም፥ ሳትወሰን ሳትለካ

በምድር ስሜት ሳትነካ

በሰው መውደድ ሳትረካ

ቅዱስ መንፈስ ያላበሳት

ብቁ ናት፥ ለካስ ፍጹም ናት

የሰው እሳት እማይሞቃት!

ከመላእክት ጋር አብራ፥ ክንፍ አውጥታ ተፈትልካ

ምንም ምንም ሳትነካ

በቃች! ትዝታ'ኮ ለካ

ሰው አደለችም ቅዱሰ ናት

የሰው ንዳድ እማይሞቃት።

ብቁ ነች አዎ፥ ፍጹም ነች፥

ምን ያረጋል.... ሰው አደለች።

እሷ የደም እሳት የላት

እውነት የእውነት... ውሸታም ናት።

፲፱፻፷፪ - ሰድስት ኪሎ

# ከፋ

ትኩስ፥ የቡናው ሣሳይ ከተማ

ያባ ጂፋር፥ ያባ ቡና፥ ያባ ጂማ

ከፋ፤ የምንጩ አልጋ ከተራሮች ማማ

ከቀይ መስኖ ማኅፀን፥ የቀይ አፈር ግርማ፤

ከፋ፤ ምድረ ዘለዓለም-አዝመራ
ጥቁር ቡና፥ ውሀ-ጠይም ዘር ሲያደራ

ከፋ፤ ኮፊ' ሞክሼው፥ በአቦሉ ጀባ ሲጠራ

ረዳው በነጌኔ ተራ

የከፋ ወዝ፥ የቡና መገኑ

ጉሙ፥ ዝናብ አቀፍ ደኑ

ጭጋግ ከንፉ፥ ደመና ወሰኑ፤

ያደን ምድር፥ አውሬ ከንፋስ ሲያጋፋ
ባባ ጂፋር፥ በጀግና አገር፥ ከፋ፤
የቀጭኔው ምጡቅ ግርማ

የእሳት ዓይኑ የነዳልጋ አንበሳው ጋማ

በሌሊት ጥሪ ሲያሰማ

ከፋ፥ ያባ ጂፋር፥ ያባ ቡና፥ ያባ ጂማ

በንጋት አቦል ሲያጠማ
"ትኩስ፥ የቡናው ሣሳይ ከተማ።

፲፱፻፶፱ - ጂማ

# "እሳት ዐመድ ወለደ"

"አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል!

ወለድኩ ይበል ይልቅ፥ በቃ፥

በምላሱ እሚያመረቃ!

ወኔው ባአረቄ እሚነቃ

ልቡን ባቧልት እሚደቃ

በሤራ ባነገር አሽሙር

'በታክት በአንትሪግ' አዙር

ሳሮጥ ሳሽከረክር ሳዞር

በብልጠት ባንደበት ንቃት፤ በመስሎ አስመስሎ መኖር

ሴቷን በነገር መብለጥለጥ፥ ጋለሞታን በምላስ ጦር

ሁሏን ረትቼ አሸንፌ፥ በምጸት ወግ፥ በጌጥ፥ በ'አሞር'፥

ሲነጋ አንደአመድ አፋሽ ገል

ሲመሽ እንደሽንቁር በርሜል

የአግቦ ጢስ በማንቃረሩ

ወሬ በማንሸራሸሩ

ተሞልቶ በመተርተሩ፥

ነፋስ ጠብቶ አየር ታልቦ

የነገር ረሃብ ተርቦ

ጉድ በማናፈስ ተስቦ
ከዚህ ቀድቶ እዚያ ዘንቦ
ውሀ እንደማይቋጥር ገንቦ....

ላባቴ ተወልጄለት፥ ቅምጥል የልቡ ኩራት
ግሥላ የወኔው እሳት
ይመካ እንጂ ይንቀባረር
ይሞካሽ እንጂ ይገደር
የዘር ወጉ እንዳይደፈር
ደርሼለት እሱን መሰል
በተከለው እሚከተል
አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል።

መስል ወራሽ ተካሁ ይበል፥ የዘር ቅርሱን የሚያስፋፋ
ድል የሚመታ ሰተቴ፥ በነገር በአሽሙር ልፈፋ
በአግቦ እንደቅኔ ዘረፋ
በሽሙጥ ባፍ ዘለፋ፥
ይበል እንጂ 'እኔም ወንድ ወለድኩ
ባፍ እሚበልጠኝ አደረስኩ
በነገር እሚጥል ፈጠርኩ፥
ያባት ልጅ ያዘው ቅምጥል
የደሙ ትክል የወኔው ሽል፥

ፈጠርኩ ይበል ቀበዝባዛ፥ እንደአዙሪት እሚፈትል

በምላስ ቀስት አነጣጥሮ፥ ቂም በልቦና እሚተክል

ደም በደም እሚያስተጣጥብ፥ ወገን ከወገን እሚያክል

እንደሥራ-ሥር ደብተራ፥ ላንቃው መርዝ እሚያቀላቅል

ውጋቱ ዘር እሚያጣጥል

እንደጦስ እሚደበልል

እንደዛር ውላጅ አሽሮ

ያጥንት ስባሪ አቅሮ

አንደበቱ እንደወሰፈንጥር፥ ሾሎ ባስተናግር ቅጠል

አፈ-ጊንጥ ያብሾ ጡት ልጅ፤ ጥላ ወጊ ቀትረ-ፍልፈል

አለሳልሶ እንደወላፈን፥ አሽልቦ ሲንበለበል

በከንፈር ፈግታ ከንፎ፥ ባፉ ጥላ-ወግቶ እሚገል፥

ደም-መራዥ ልጅ፥ ያፋፍ ላይ ድጥ፥ መሰከ መሳይ ያሽሙር ደለል

የወሬ ማንፈሻ ጋሻ፥ ደርሼለት እሱን መሰል

በተከሰው እሚከተል....

አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል!"

'ለተማሩ' - ለማይምሩ አፈ-ሊቃውንት - (፲፱፻፰፩ - አዲሳባ)

# ሕረር

ሐረር፥ የግንብ-አጥር ማኅደር

ያባአደሬ ያባድር በር።

ድባብ ሦራ

ቀደምት የከተሞች አባወራ።

አምባ ዙሪያ-ክብ መንደር

ከሸዋ በር ፋልአና በር

ሐረር ጀጎል የሁሉ ዕድር

በአትክልት ሆነ በጫት እግር

የጥጋብ የሲሳይ ምድር፥

ከዱክ በር እስከቡዳ በር፥ በአምስት ደጅ የምታጋፍር

ተትረፍርፋ ስትመግብ፥ ቀናን ክአታክልቷ ቅጥር

ሌቷን በጨረቃ ችቦ፥ ጥላ ለአያጅቦ ግብር።

ሐረር፥ ሸንጐሽ ሁሉን አቀፍ

በበተስኪያን በመስጊድ ሠልፍ

በጂጂጋ ኮረብቶች ዘርፍ

በአጥሮችሽ ቅስቶች መርገፍ

በነራምቦው ብዕር ንድፍ

በሸኅዩ ወሸባ እቅፍ

የተንቈጠቈጥሽ መንደር
ሐረር፥ የግንብ አጥር ማኅደር
ያባአደሬ ያባድር በር።
ድባብ ሦራ
ቀደምት የከተሞች አባወራ።

ለከበበው አሻግሬ - (፲፱፻፰፫ - ሐረር)

# እውነት አሁን አንቺ እሷ ነሽ!

እሷ ነኝ በዬኝ ግድ የለም!...

ሁሉ ላፍ አልተፈጠረም

ቢሉም አፍ ኣይለው የለም።

ልወቀውና ላውጣ እርሜን፥

የለንት ዘመን ረሃቤን

ልጋረጠው በዓይንሽ ዓይኔን።

ልጅነቴን የዳኸኩበት፥ የስንት ዘመን ፈለጌ

በናፍቆት ቋት ተሰግስጌ

በጣር በምጥ አደግድጌ

በእግረ ሕሊና ጠርጌ

በትዝታ በዳሰሳ፥ በፈለግሽ የናዳ ዳር

ስዋትት ሰማስን በጣር

ዛሬ ያገኘሁሽ ባሣር

በስንት ዘመን የዕድሜ ምጥ

እውነት ኣንቺ እሷ ነሽ እርግጥገ!

መምሰልማ ትመስለያለሽ

ማከልማ ታክያለሽ

የደም ግባቷን ተላብሰሻሽ

መጠሪያዋን ተሰይመሻሽ....

ያቺን የኔን...ያቺን የኔን

የኔን የመጀመሪያዬን

የጥንቴን የልጅነቴን

የሰንት ዘመን ሕመሜን

የሕልም ዓለም ሰመመኔን

የት አረግሻት? የት ደበቅሻት?

ዋጥሻትገ....

አጥንቷን በእጥንትሽ ለብሰሽ

ወዚን በላቦትሽ ታጥነሽ

በልጅነቷ ልጅ ሆነሽ

ገጺን በግንባርሽ ነድፈሽ

አበቧን አደብዝዘሽሽ

መልኳን በመልክሽ አክስለሽ

ቡቃያዋን በፅድሜሽ ውጠሽሽ

በሰም ብቻ እሷን ሆነሽ

ማነሽ? እውነት እንቺ ማነሽ

እኮ ንገሪኝ እሷ ነሽ?

ግድየለም ንገሪኝ ሐቁን

እርግጥ አንቺ እቧሷ ነሽ አሁን!

ንገሪኝና ላውጣ እርሜን

የሰንት ዘመን ረሃቤን

የጋረጠው ዓይንሽ ዓይኔን

እርግጡን ብቻ የሐቁን

የሰማይ የምድር እውነቱን

የቁርጡን የእርሙን የእቅጩን

በይ እሰቲ አንቺ እሷ ነሽ አሁን?!

፲፱፻፶፫ - አዳማ

# በራ፤ የመስቀል ደመራ

የአደይ ችቦ እየፋመ፥ እየጋመ

ኢዮሃ እያሰገመገመ እየተመመ

የመስቀል ደመራ

በራ።

በራ የአዲሰ ዘመን ችቦ

በመስከረም ለብል እብቦ

ከዋክብቱን ፈነጠቀ

ርችቱን አንጸባረቀ

ተኳለ አዲስ ደመቀ

መሰኩን በቀለም አዝርእት፥ በጥበብ አጥለቀለቀ

ሸለቆው ተንቆጠቆጠ* ተራራው አሸበረቀ

ኢዮሃ ኢዮሃ አበባዬ፤ ምድር ሕይወት እፈለቀ።

ነጋ፥ የአዲሰ ዘመን ችቦ

ፈካ፥ ፀደይ አረብቦ

ሌሊቱ እንደጎሕ ቀደደ፥ ጨለማው እንደቀን ጠራ

እንደውቅያኖሰ ዕፀዋት፥ እንደጠፈር ኮከብ ደራ

ምድር ሥጋጃ ለበሰ፥ የጌጥ አልባሳት ተቀባ

ሰማይ በእልልታ እስተጋባ

ኢዮሃ መሰከረም ጠባ።

ነጋ፥ የአዲስ ዘመን ችቦ፥ ምድር ሕይወት አፈስቀች

የምሥራች እዝርእቷን፥ዐ አዲስ ቡቃያ ወለደች

የእደይ አበባን ለገሠች

ለአዲሰ ዘመን አዲስ ብርሃን፥ አዲስ መስከረም ገበየች።

ነጋ የአዲስ ዘመን ችቦ

ፈካ፤ ፀደይ አረብቦ

በራ፥

የመስቀል ደመራ።

መስከረም - ፲፱፻፷፫ - መስቀል አደባባይ

# ጌራ

ጌራ ነበልባል ዘለላ
እንደመንጸባርቅ ጥሳ
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠሳ፤
ጌራ የፈተና መከር
የቁንጅና ራዕይ በር
እድብተሽ እንዳረህ ደለል
በልብ እሳት ለመዋለል
ሰቀቀን እስኪዘነበል
ጣር ለጣር ለመቀላቀል
ድንገት ደርስሽ ለመንጣለል፤
ጌራ የልጅነት ፍቅር
ድብቅ የዕድሜ ልክ ምሥጢር
አይሆንም እንጂ ቢሆንሽ
ነፍሳችን ይኳረፍ እባክሽ።
ጌራ የኪሩቤል እሳት
በኛ በሙታን ሕዋሳት
ተግ ሲል ያይንሽ እልባት
ልብ እያየ ልብን ሲያጧት

ማቀርቀር እንጂ መደፋት
በማን ልብ ቆመው ሊያይዋት!
በግልምጫ ስታመንን
አይታ ስታስደፋ ቀልብን
እንደመለኮት እንቅታ፥ ሳትበደል እምትኮንን።
ማስጣር እንጂ እሷ ሳትጥር
ያየን እንደበላዔ-ሰብእ፥ እንጂ እንደ እመ-ብርሃን ሳትምር
አትተውም ጌራ አትለቅም
መኰነን በቀር አታውቅም
እሙ-ብርሃን ትምሰል እንጂ፥ እንደ እሙ-ብርሃን አትምርም፥
እንኳንና ሰው ብኩኑ፥ መለኮት ወርዶ ቢያበራ
ከቶም አትለቅና ጌራ
እንዲያው እንደዘልማዱ፥ በእንቅልፍ ልብ እንጣራ
ነቅተን በቅዣት እናውራ።
በጥረት ጌራን ከታደግን
ከእርካንዋም ከቶ ከታገድን
ለብቻ የመኮራመት፥ የዕድሜ ጥሻ ነው የለመድን።
እንደጮራ ድንገት ሰርቃ
በጥሻ ዋሻችን ጠልቃ
ወዲያው እንደመብረቅ መጥቃ

በቁም ስታቃዣን አውቃ፥

በቃን እንል ነበር ጣሯ፤ ይበቃን ነበር ብትተወን

ችላ መቻል ብታስችለን

የልብ ውጋት ሳትዋጋ

በሕልም ቤት ሳታናጋ።....

ብቻ ጌራ

ነችና የሕልም እንጀራ

የምትመጣ ሳትጠራ

ሂጅ ሳትባል የምትሄድ፥ የምትመነጠቅ በርራ

እኛለ ይብላኝልን ለኛ። መኮራመቻችን ፈርሶ

ድንገት ከሙት-ዓለም ዋሻ፥ ገበናችን ተገርስሶ

እንገት እንኳ እምንደፋበት፥ መተፋፈሪያ እሰክናጣ

እንደዘመናይ ባላንጣ

በማታምንበት አጋልጣ፤

የዕድሜ ወዛችን ፈሰሰ

ልጅነታችን ቀነሰ

አሰበርግጋ ብትነድፈን

አጋልጣ ብትሠወረን።

ተይ አንል አትሠወሪ

ስሚ አንል በሕልም ጥሪ

ወይ ፈጽመሽ አንል ቅሪ
“ነፍስ ሳይግል ነው እሚነድግ
ሞት ሳይሞቱት ነው እሚለመድ?"
ብላን ብቻ ብላን ትቅር
እንዲያው እንዲሁ እንደ ምሥጢር
እንዲያው እንዲሁ ሳትምረን
እንዲያው እንዲሁ ሳትተወን
እንቅልፋችንን ሳትቸረን
አንቅታ እንድትኩንነን።
ጌራ፥
ያረቀቀሽ የአምሳከ ሥራ፤
ጌራ* የቁም ሕልም እንጀራ፤
ጌራ፥ የዲበ-ሹሉ ጡብ
የሕዋው ፈተና ክቡብ
የመለኮት ቅጣት ዕቁብ፤
ጌራ የሰቀቀን ጽዋ
“ዓይጥ በበሳ ነው ዳዋ
እሚበራይ እሚሰዋ"
ብሳን ብቻ ብላን ትቅር።
“ላይችል አይለጥ" ብላን ስውር።

የነፍሰን ንዳድ ላትሞቃት
የልብን ዋይታ ላትሰማት
የብሌንን ምጥ ላታያት
ምን ሳይተርፈን ምን ላይተርፋት
ብንወድም ወደድን አንልም?
ብንነድም ነደድን አንልም? ...
ምንም ሳንተነፍስ ኩርትም!?
ጌራ የውብ-ዓለም ብቁ
እስከዚህ ነው ኑሮ ጭንቁ
ጌራ ይህ ነው የዕድሜ ብሩቄ?
ምኞት ናዳ-ድጥ ነው ትጥቁ?
የዕድሜ ብኩን ጣር ነው ሰንቁ?
ጌራ የሕልም-ዓለም ደለል
ትዝታሽ ሞልቶ ሲቆለል
ሲቃ ነው እሚኮስኮል።
ጌራ የእቶን-ፍም ዘለሳ
ከገጽሻ የእሳት ክለላ
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠላ
እንደመንጸባርቅ ጥላ
ተግ አትበይ ባይንሽ እልባት

ልብ እያየ ልብን ቢያጧት
የእዝን ቋት ላይተካላት
ማቀርቀር እንጂ መደፋት።

ጌራ የመከራ መከር 5
የቁንጅና ራዕይ በር ን
ሕልም ኣይቻለሁ ልናገር። '
አንቺ ስትስቂ እኛ ስንበር
ስንቀርብሽ እየሸሸሽን፥ ሸሽተሸ በማታውቂው እገር
ስንርቅሻ ተግ እያልሽብን፥ ረግጠን ከማናውቀው ጠፈር
ኣንቺ ታጅበሽ ስትበሪ፥ የኛ ክንፍ ሲሰባበር
አንቺ አንድያሽን ስትርቂ፥ እኛ ስንወድቅ እኛ ሰንቀር!
ፍቺልን ጌራ ፍቺልን፥ ሰው አይከርምም ሕልም ጕርሶ
በቅዣት ጠረንሽን ዳሰሶ
በሽውታ-ተስፋ ደርሶ
ቀን በቁሙ ካልጸለሰየ፥ ጌራ ያንቺን ኪራራይሶ?
ምነው ያንቺስ ሩካቤ አቅም
ከኛ እንጂ ወደእኛ አይዘልቅም?
ሲላመዱለት እይለምድም?
ሸቅብ ከራቀበት ወርዶ

እንደሰው ለሰው ተጠምዶ

በፍቅር እምሳክከ ተገዶ!

ፍቿልን ፍቿልን ጌራ

ቀልብ እንዲህ ሰጣር ተድራ

ከሕልውናችን ስብራ

ያሰዕጣችን ተስባጥራ

እንደሰሞነኛ ካህን፥ ነግ በእንቅልፉ ጣዕም ወድቆ

ያለሱባዔ በምኞት፥ በተስፋ እግሩ ብቻ ፀድቆ

ያልደረሰበትን ደርሶ፥ ያላወቀበትን እውቆ

በሰመመን መሶብ ብቻ፥ ከነፍሱ ረሃብ ተላቆ

በፍስሐ ተፍለቅልቆ

እንደአራስ ነፍስ ፈንድቆ

ከረፈደ ኋሳ ከርሞ፤0 ነፍሱን ሲቃ ከማስወረር

ከቶ ሳይነቃ እንደሚቀር

ዓይነቱ ነው የኛም መከር?

ፍቿልን ጌራ ፍቿልን፥ ቀን ታልሞ ሌት ታልሞ

ፍዳን ቃትቶ አጣጥሞ

አይተረጉሙት ሕልም ነን፥ የሚደበቅ ተረምርሞ

እንደሰሞነኛው ካህን፥ ከንጋት ቅዥት ጋር ወድሞ?

በተስፋ እንደተዘረጋ

ለመከራው ከሚያነጋ

የማይነቃ የሚረጋ

ንዓይነት ነው ጌራ ፍቺልን? ማግረሺን በሕልም ጐጆ

ጌራ ብርሃን ጌራ ቆንጆ

ለተለፋችን ዕዳ ሆንነው?

'እኛ ለኛ አንኾነው እልነው?'

ሌት በቅዣት ተሰትረን

ቀኑን በስቀቀን ታንቀን

ዕድሜኣችን በምኞት ታጥፌ

ፍቅር እንደዜ ነው እሚገል፥ ኒኛ ስንቴ እንሙት ጌራ?

ውሳችን በውሱ ላይኖር

ተነጣጥለን ሰመባከን፥ ለመንከራተት ለመዞር

ተጣምረን ላንከራረም

ተቄራኝተን ላንታደም

ላይነጋልን ላናጨልም

ላንዳበል ላናገግም

መባከን ከሆነ ፍቺው፥ ብኩን ክብኩን እይሠምርምገ!

ጌራ የስቃይ ስያሜ

ለአንዲት ደቂቃ እንኳን ዕድሜ

'ተስፋ' ብንል ብለሽ 'እርሜ'

የተንከራተተውን ሕልም
የተቅጠለጠለውን ቅስም
ስናታክት ለናደክም፥
ብራቅ ዳዕሩን ተርክኮት፥ እንደማይነድ ያድባር ዋርካ
በቁም ሞተን ሰናወካ
ፈተናሽ ታልፎ ላይበቃ
በቅዣት ላናመረቃ።
ጌራ ብኩን ጌራ ብካይ
ጌራ ከንቱ ጣር አሰልሳይ
ጌራ የሕልም ዓለም ሰቃይ፤
ጌራ ሰቀቀን መከራ
በቅዠዣት ከምንጣራ
አይሆንም እንጂ ቢሆንሽ
ነፍሳችን ይኳረፍ እባክሽ።
በቁም ቅዥት እንወያይ
በምኞት ጣር እንተያይ
ይብቃን ደህና ዋይ፥ ደህና ዋይ።

ጌራ ነበልባል ዘለላ
እንደመንጸባርቅ ጥላ
ሽልም ሽፋልሽ ሲያጠላ።

ጌራ የፈተና መከር
የቁንጅና ራዕይ በር
አድብተሽ እንደአረህ ደለል
በልብ እሳት ሰመዋሰል
ሰቀቀን እንዲዘነበል
ጣር-ሰጣር ለመቀላቀል
ድንገት ደርስሽ ለመንጣሰል፥
በለዘብታ ለማመነን
እንደመለኮት አንቅተሽ* ሳትበደይ ለመኩነን።
ጌራ-ሽልም ጌራ-ስውር
ገጸ-ረቂቅ ልበ-ነብር
እመ-ብርሃን መሰል ጌራ፣ እንደ እመ-ብርሃን እማትምር
ሽሻግ የዕድሜ ልክ ምሥጢር
ጌራ የልጅነት ፍቅር....
አይሆንም እንጂ ቢሆንሽ
ነፍሳችን ይኳረፍ እባክሽ።»

፲፱፻፹ - ፓሪስ

# ማይጨው

የማን አንደበት ነው ማይጨው
ያንቺን ሲኦል የሚነግረው?
በማን የብዕር ቃል-ደም ነው
ታሪክሽ የሚነደፈው?
ማይጨው እግዚኦ ላንቺ ቆሌ
አገር ውሀ-ገባ-አሞሌ
የሆነብሽ የአሳት ምፅዓት
በነጭ አረመኔ መዓት
የመድኃኔ ዓለም ቀን ቅጣት፤
እንዲህ ነበር ብዬ ላልጥር
ያንቺን መቅሰፍት ያንቺን ዕድር
ላይጽፈው የሚችሉ ሰው ብዕር፣፤
ያንቺን የእርባ ዓመት ቂም በቀል
ያንቺን ዕብሪት ያንቺን በደል
አስቀድሞ እንደተባለው
"እግዚአብሔርና ታሪክ" ነው
ፍላፃሽሽን የሚጽፈው
ፍርድሽን የሚቋቋመው፥...

ያገር ጐበዛዝ ያገር ወንድ
በነጭ እረመኔ ሞገድ፥
ሑር ኤርክሔ
ያገር ሕፃን ያገር ወላድ
በእቶን የመርዝ እሳት ንዳድ፥
እንደፍካሬ ኢየሱስ ቃል
በፋሽስት ሲኦል ሲጣል*፥…
ማይጨው እግዚኦ ላንቺ ቆሌ
አገር ውሀ-ገባ-አሞሌ
የሆነብሽ የእሳት ምፅዓት
የነጭ አረመኔ መዓት
በሟች ብዕር ላይቀመር
የመቅሰፍትቫሽ ሲኦል ድንበር
"በአግዚአብሔር-በታሪክ" በቀር
በቁም ሮሮ ላይሠፈር
ላይመጠን ላይነገር።
በማን አንደበት ነው ማይጨው
በማን የብዕር-ቃል-ደም ነው
ሲኦልሽ የሚነደፈው?

፲፱፻፵፰ - ማይጨው

# ድሬ-ዳዋ

ዲሬ-ዳዎ ድሬ-ዳዋ

የምሥራቅ አድባር ጥላዋ

ላገር ጕሣ ድምር ጽዋ

ኅብራጠባይ ማጥለያዋ፤

ድሬ-ዳዋ ውስጠ-ደማቅ

ሽፍንፍን እንደአባድር ጨርቅ፥ ብልጭልጭ እንደሩቅ ምሥራቅ

ያውራ ጐዳናሽ ዛፍ ጥላ* ጋርዶሽ ከንዳድሽ ብራቅ፥

ድሬ-ዳዋ ዲሬ-ዳምዎ፥* የማእጠንትሽ ወዝ ብርጉዱ

ውልውል ሲል በቀትር፥ ከላጋር በር ማልካ ጃብዱ

ከጋንዳ ቆሬ ካዚራ

ከአፋታ-ኢሳ ቃፊራ

ከማጋላ ጋንዳ-ጋራ፤

በረድ ሲል ጥላሳሽ ሲወርድ* ቆሌሽ ቀይሮ ሲወጣ

በሽርጥ በሻሽ በቁምጣ

በመለዮ በባርኔጣ

በየጉድባሽ ጫት ሲሰጣ፤

ጣይ ያደከመው ወፈፌሽ፥ 'አራራሪ' ጥሎት ሲንጣጣ፥

ብሌኑ እንደጎሽ-ግት ደምቆ

በንዳድሽ ግለት ሞቆ

ጉድ ከየአንደበቱ ፈልቆ

ሰንቱ ቋንቋ ተድብለቅልቆ+፥

ከትምባሆሽ ረት ጨምቆ

ጫት ከአብሾሽ ወዝ ተማጥቆ

ድሬ ምድራ-4ቦት ዘፍቆ፤

ድሬ-ዳዋ ቁሉቢ በር

የስንቱ ዘር የእኩል እገር

ዲሬ-ዳዎ ድሬ-ዳዋ

የምሥራቅ አድባር ጥላዋ

ላገር ጐሣ ድምር ጽዋ

ኅብረ-ጠባይ ማጥለያዋ።

፲፱፻፷፫ - ድሬ-ዳዋ

# ተወኝ

ላታሰታምም አትመመኝ

ላትወስደኝ አታንጠልጥለኝ

ይቅር፥ አንጀቴን ቁረጠኝ

ጋሸዬ፥ አልወድሽም በለኝ።

እጅ እጅ አልበል አታባክነኝ

ባክህ፥ ወንድ ነው ቆራጡ፤ እንትፍ-እርግፍ አርዝ) ተወኝ።

አየህ፥ እንዳንተ እባት አለኝ

ሴት በወለድኩ ተዋረድኩ፥ ረከስኩ ቀለልኩ እሚለኝ፥

እኔም እንዳንተ እህት አለኝ

ሥጋሽን ሳይሆን ልብሽን፥ ከፍተሽ ጥለሽ ነው እምትለኝ

እና ተወኝ፥ ባከህ ተወኝ፤

እንዳንተ እኔም አለኝ እናት

የሴት ቁንጮ እምመሰላት

ጎረቤት ፊት እምታፍር፥ እንዲህ ሆነችልሽ ሲሏት!...

እና፥ እልሆንሽም በለኝ

ባክህ እንጀቴን ቁረጠኝ...

ፍቅር እንደሁ የኔ ይበቃል፥ ላንተም ለኔም እኔው ልውደድ

ከዘመድ ግንባር ደብቂቂ፥ እኔ የብቻዬን ልንደድ፥

ብቻ፥ ከወጥመድህ ለየኝ

አልችልህም፥ ንቀህ ማረኝ

ካንተም ከሰሜም ከቤቴም፥ ያጣሁ ብኩን አታድርገኝ፥

ባከህ፥ አንጀቴን ቁረጠኝ

ተወኝ፥ ተወኝ፥ ተወኝ።

፲፱፻፶፯ - ኒውዮርክ

# ድንቅም አደል?

እሰቲ ሰው ሞልቶ ባገሩ....

ተትረፍርፎ በየበሩ....

እያንዳንዱ በየግሉ

እንደዘበናይ ዕድሉ

ተገንጥሎ ለበኩሉ

ለየፊናው ለየቅሉ

ከነፍሰ ወከፍ መደበሩ

አንድ ራሱን መሰወሩ

ለብቻው መነጋገሩ

ከጥላው መመካከሩ

በነፍሰ ወከፍ መደበሩ

ከሕልሙ መመሳከሩ፤...

ብቸኝነት ውጦት ሁሉ

ለፍሬም ባይሆን ለቃሉ

የተሰፋን ችቦ መሳሉ፤

ለውኑም ባይሆን ላመሉ

እንደዘበናይ ዕድሉ

በምኞት ሱስ መዋለሉ፤

“ከዘመድ ከወዳጅ ጠለል"

ከስንቱ 'መዓት' መካከል

ለየብቻው በመገንጠል

በሕልም ዓለም ለመንጠልጠል

ተደባብቆ ሲብሰለሰል

ጉድም አደል? ድንቅም አደልገ...

'ለብቻኞች'- ፲፱፻፶፱ -አዲሳባ

# ኣብረን ዝም እንበል

ከሰው መንጋ እንገንጠል

ለአንድ እፍታ እንኳ እንገለል

በእፎይታ ጥላ እንጠለል

ዝም ብለን አብረን ዝም እንበል።

ምነው አዋሽ ማዶ ቆቃ፥ እሽለቆው ግርጌ ሸሽተን

የቆቃን ለቆቃ ሰምተን

ሲቃውን ሲሰብቀው አይተን

ሰቀቀኑን ተወያይተን

የምሽት ጀምበር ቢውጠን?...

ወሀ እንደዱታ ሲተምም፥ በድን ሽለቆ ሲናገር

በሰማይ ፈረሰ ተጭኖ፥ ከአፅናፍ አፅናፍ ሲንደረደር

ሲያጉተመትም ሲያሰገመግም፥ በዓይነ-ሕሲና ለመመሰከር

ሳንጨነቅ ሳንገደር

ለማንም ምንም ሳናዋይ፥ ሳንናገር ሳንጋገር

ከዓይንሽ ከልብሽ ከልቤ፥ አዋሽ ማዶ አብረን እንብረር።

አዋሽ ማዶ አብረን እንውረድ

አጉል ነው ብለንም ሳንፈርድ

ድንቅም ነው ሳንል ሳንወድ

ዝም ብለን አብረን ብንወርድ...

ከሰው መንጋ ተለይተን

ከጠረኑ ተነጥለን

ከጉምጉምታው ተገንጥለን

ከኳኳታው ብንከለል...

ከላንቃው ከድምፁ ሸሽተን፥ በእፎይታ ጥላ እንጠለል

በቆይታ፥ በፀጥታ፥ ዝም ብለን አብረን... ዝም እንበል።...

መቸስ አይሆንም ካልሽ .... ቅሪ

ግድየለም አትገደሪ

ልቦናሽ በመተረልሽ፥ ባሳደረብሽ እደሪ፤

ተስፋ መቀነት ነው መቸም

የሰው ልብ አይችለው የለም ....

ብቻ ዳግመኛ ሞት ሳንሞት፥ አዲስ ቀን ሳይጨልምብን

ድፍን ደመና ሳይቋጥር ከረምት ውርጅት ሳይወርድብን

ኮከባችንን ሳንጠራ፥ ሳንቆጥርባት ሳትቆጥርብን

ሞራችንን ላናሰነብብ፤ ሳናሳያት ሳታይብን

ጨረቃን መሰከሪ ሳንል፥ ሳናውቅባት ሳታውቅብን

አዋሽ ማዶ ቆቃ በርረን፥ ባክሽ ጀምበር ትጥለቅብን፡....

ወሀ እንደዱታ ሲተምም፥ በድን ሸለቆ ሲናገር

በሰማይ ፈረስ ተጭኖ፥ ከአፅናፍ አፅናፍ ሲንደረደር

ሲያጉተመትም ሲያስገመግም፥ በዓይነ-ሕሊና ለመመስከር

ሳንጨነቅ ሳንገደር

ለማንም ምንም ሳናዋይ፥ ሳንናገር ሳንጋገር

ከዓይንሽ ከልብሽ ከልቤ፥ አዋሽ ማዶ አብረን እንብረር።

ከሰው ኳኳታ እንነጠል

ለአንድ አፍታ እንኳ እንገለል

በእፎይታ ጥላ እንጠለል

ዝም ብለን አብረን ዝም እንበል።

፲፱፻፷፩ - ቆቃ

# አሥመራ

ምነው ሁሉ እንዳንቺ አሥመራ

እንደከተሞች መዲና አቀያየሱ ቢጠራ፤

ያውራ ጐዳናሽ ጠለላ፤ ሁሉን በአክናፉ እየጠራ

አሥር ሰዓት ላይ ሲደራ

ለመንገደኛሽ መዝናኛ፣ ሲያጠላ ሲያብብ ሲያፈራ፤

ምነው ሁሉ እንዳንቺ አሥመራ

አደባባይ ሲያነጥፉ

አድባራትና መስጊዱን፥ ካቴድራሉን በየረድፉ

ገበያውን በየመልኩ፥ እንዳውታር እያሰለፉ

በወግ እየደረደሩ

በሥምረት እያሠመሩ

በውበት እያዳበሩ

እያሳመሩ ቢያደሩ፤

በየክፍሉ በየበሩ፥ በየመልኩ በየተራ

ፋኖሱን እንደደመራ

ቡና ቤቱን እንደሦራ |

ምነው ሁሉ እንዳንቺ አሥመራ

እንደከተሞች መዲና፥ አቀያየሱ ቢጠራ።

፲፱የ፻፵፫ - ኢሥመራ

# ወንድ ብቻውን ነው እሚያለቅስ

ከወዳጅ ከዘመድ ርቆ

አንጀቱን በእንጀቱ ታጥቆ

ተሸሽጎ ተገልሎ፥ ተሸማቆ ተሸምቆ

ከቤተ-ሰው ተደብቆ

መሸቶ፥ የማታ ማታ ነው፥ ሌት ነው የወንድ ልጅ እንባው

ብቻውን ነው የሚፈታው።....

ብቻውን ነው የሚረታው።....

ችሎ፥ ውጦ፥ ተጨብጦ ተማምጦ ተጣጥሮ

በሲቃ ግት ተወጥሮ

እንደደመና ተቋጥሮ

እውስጥ አንጀቱ ተቀብር ...

መሸቶ ረፍዶ፥ ጀምበር ጠልቆ

የጨለማ ድባብ ወድቆ

በእንቅልፍ ጥላ ሲከበብ፥ በዝምታ ሲዋጥ አገር

ፍጡር ሁሉ ተስለምልሞ፥ ብቸኝነት ብቻ ሲቀር....

የኋላ የኋላ፥ ማታ

ምድር አገሩ በእፎይታ

ዓይኑን በእንቅልፍ ሲያስፈታ

ሁሉ በእረፍት ዓለም ርቆ፥ ብቸኝነት ብቻ ሲቀርብ

ያኔ ነው ወንድ ዓይኑ የሚረጥብ

የብቻ፥ እንባ ወዙ እሚነጥብ።

ብቻውን ነው፥ ብቻውን ነው ...

የእንባ ጭለማ ለብሶ ነው

ወንድ ልጅ ወዙ እሚነጥበው።

ዕጣውን ለብቻው ቆርሶ

ብቻውን ሰቀቀን ጉርሶ

ብቻውን ጭለማ ለብሶ

ገበናውን ሣግ ሸፍኖ

ክብሩን በሰቆቃ አፍኖ

ሌሊት፥ የማታ ማታ ነው

ሕቅ እንቁን እሚነጥበው

ኤሎሄውን እሚረግፈው ....

ከዓይኑ ብሌን ጣር ተመጦ

ከአንጀቱ ሲቃ ተቆርጦ

ደም አልሞ ፍም አምጦ

ከአፅመ-ወዙ እቶን ተፈልጦ

እንደጠፈር-ብራት እምብርት

እንደእሳተ ገሞራ ግት

'ርቅ ነው ወንድ ልጅ እንባው

ደም ነው፥ ፍም ነው እሚያነባው፤

ንጥረ ሕዋስ ነው ሰቆቃው

ሪቂቅ ነው ምሥጢር ነው ጣሩ፥ ... ብቻውን ነው የሚፈታው፥

ብቻውን ነው የሚረታው።

ችሎ፥ ውጦ፥ ተጨብጦ፥ ሰቀቀኑን በሆዱ አጥሮ

በአንጀቱ ገበና ቀብሮ

ውሎ ጭጭ እፍን ብሎ፥ እንደደመና ተቋጥሮ

ጣሩን ውጦ ተጣጥሮ

በሲቃ ግት ተሰትሮ...

ከወዳጅ ከዘመድ ርቆ

ከቤተ-ሰው ተደብቆ

አንጀቱን በአንጀቱ ታጥቆ፥

ተሸሽጐ ተከናንቦ፥ ተሸማቆ ተሸምቆ...

የብቻ ብቸኝነቱ፥ የጭለማ ልብሱ እስኪደርስ

በዓይን አዋጅ ሃሞቱ እንዳይረክስ

ቅሰሙ በገበያ እንዳይፈስ

ተገልሎ በእኩለ-ሌት፥ ወንድ ብቻውን ነው እሚያለቅሰ።

ለዘውዴ ሽዋሞልቶት - (፲፱፻፶፫ -- አምቦ -ኮልፌ)

# ትዝታ

ዓይንህን በዓይኔ ፀንሼ፥ የቀስቱን ጮራ እንደቋጠርኩ
ሌሊት በሕልሜ አማምጬህ፥ ሕመምህን እየፈጠርኩ
ቀን ጥላህን እንደሰበሰኩ
የፍቅራችንን ነበልባል፥ በቁም ሰመመን እንዳቀፍኩ
ልብ ውስጥ እንዳዜሙት ሙሾ፥ የሲቃ ስልት እንዳቃጨልኩ
የነፍሴን የእሳት ዘለላ፤ ጐዳናህ ላይ እንዳነጠብኩ
እንደገደል ዳር ቄጠማ፥ የሥጋት እንባ እንደቃተትኩ
ሕይወቴን ላንተ እንዳሸለብኩ
ሕልምህን በጄ እንደዳሰስኩ
ያን የመጀመሪያ ሞቴን፤ በመሸ ቁጥር እንደሞትኩ
አለሁ፥ እንደብኩን መረብ፥ ትዝታህን እንዳጠመድኩ።

፲፱፻፶፱ - ጋርባ - ጉራቻ

# አዘቦን ዳግም አየኋት

ዓይን ማየት ነውና እሚያቅ

የብርሃን ዕድሜ አዚሙ እስኪያልቅ ...

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፥ ዳግም አዘቦን አየኋት

ዙሪያ ቅጽሯን አስተዋልኳት

አጠናኋት፥ አዳመጥኳት ....

ዦሮ ማዳመጥ ነው ክፍሉ

ተቀባይ ሕዋሱ እስካሉ ...

እና አዘቦን ሰማኋት

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፥ ተመልሼ አዳመጥኳት

እና ዛሬስ፥ እንኳን አልኳት ....

ያኔ ድምጿ ከሩቅ ነበር፤ እንደሚቻች ሳል ሲል የሚለው

የልሳን ሲቃ ጥላ ነው

የከፉ ቀን የቅዠት ጣር፤፥ ብኸ እልሙ ነው እሚታየው

ያደባባይዋም ላይ ጭጋግ፥ የጥንብ አንሳ አክናፍ ብቻ ነው።

መሬቷ እንደሞረድ ስለት፥ ጥርሷ ሲፋጭ እንደ ደወል

ሰቆቃ እንጂ እኮ ድምፅ አደል!

ያሞራው ጥላ እንደጉም፥ ከጣራ በላይ ሲቃጨል

ሰው እንደ አይጥ በየጥሻው፥ ሲጥ ሲል እንደ ግንደ በል

ሰቆቃ እንጂ እኮ ድምፅ አደል። ....

ዛሬ ግን ጤና ይታያል

ሕፃናቱም ይቦርቃል

ከብቱም እንደልብ ይግጣል

ስውም ያወጋል ይስቃል

"ዝ ኾነ ኾይኑ" እንኳን ይላል፤

ከየምድጃው ዳር እሳት ከየጣራው ጢስ ይናኛል። ...

ዓይን ማየት ነውና እሚያቅ

የብርሃን ዕድሜ አዚሙ እስኪያልቅ

ዳግም አዘቦን አየኋት

ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ፥ ተመልሼ አስተዋልኳት

እና ዛሬስ እሰይ አልኳት።

፲፱፻፷፫ - መቀሌ

# እንዳይነግርህ አንዳች እውነት!

ደንስ ጉበዝ! ደንስ ጀግና

ክራቫትክን አውልቅና

ሃሳብክን ልቀቀውና

ኮትክን ሸሚዝክን ጣልና

ርገጥ፥ ጨፍር፥ ደንስ ጀግና!

ያን የሙዚቃህን ናዳ፥ የኮንትራባሱን መብረቅ

ልቀቀውና ይድብለቅለቅ

ምድር በሆይታ ይጥለቅለቅ!

ምንም-ምንም እንዳታስብ፥ ሁሉጉሁሱን እንድትረሳ

ደንስ! ካካታው ይነሳ

ጨፍር፥ ወስሉ እስኪበባሳ ...

ሃይ-ሃይ! ዋይ! ሃይ-ሂይ! በልበት

የጃዝ ፋንፋር አንኳኳበት

ራስክን እንዳታስብበት

ሆ! በል እሪ| በል ምታበት

ፎክርበት አቅራራበት

አናፋበት፥ ሸልልበት

የሲቃ ሳቅ እስካካበት

ሆያ-ሆዬ! በል ጩኸበት

ኡኡታህ መንኮራኩርከን፥ እስኪያሰጥመው አጓራበት

ጭንቅሳትክን ግዘፍበት፥ ውቀጥበት፥ ውገርበት፥...

ዝግ ብሎማ ያስበ እንደሁ፥ ይነግርሃል አንዳች እውነት!

፲፱፻፰፫ - አዲሳባ

# የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ

ተስፋ ባጣ ምድረ በዳ

ያንድ እውነት ይሆናል ዕዳ፣

እና ትንፋሼ አልሆነሽም፥ ሆኜብሽ መራር መካሪ

"ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ!"

እውነት ላንቺ መች ተስፋ ናት፥ ጉስቁል ልሳንሽን ነክሳሽ

ክንድሽን ካዘለ ቅርስሽ፥ መጠላለፍ ሲሆን እጣሽ

ከእንግሊዝ የሞት አማልክት፥ መተናነቅ ሲሆን ድርሻሽ

መልመጥመጡ፤ መሽቆጥቆጡ፥ መስሎሽ ድንገት የሚያዋጣሻ

የኔ እውነት ሆነብሽ ዕዳሽ። ....

ወራሪም ፈጣሪን ላያቅ

የጣለውን በስሏል እንጂ፥ ወድቋል ብሎ ግፉ ላያልቅ

መች ትተርፊያለሽ ኢትዮጵያ፥ ሕዋስሽ አብሮኝ ካልሠራ

አንገትሽ ብቻ መቅደላ፥ አፋፍ ወጥታ ብታበራ

የቀረው ሠራ-አከላትሽ፥ በየጥሻው ተዘርሮ

ከአባት በወረስሽው ንፍገት፤ ነብዞ ደንዝዞ ተቀብሮ

ባጉል ወጌሻ ታጅሎ

እጅና እግርሽ ታሽቶ ዝሎ

እኔን ለጥንብ አንሳ ጥሎ፤

ከደቀቀ ከደከመ፥ ክንድሽ አልነሣ ካለ
ሞት እንጂ ለኔስ ምን አለ? ....
ሆኖም ጐስቋላ አልምሰልሽ፥ የሚያዝንልኝ አልፈልግም
ጠላትሽን በክንድሽ እንጂ፥ በእንባሽ ወዝ ባላሸንፍም
የልቤን ፍቅር በስተቀር፥ እማወርስሽም ውል የለኝ
የኮሶ ሻጭ ልጅ ደሃ ነኝ። ...
ደሞም ያላንቺ የለኝና
ድሌም የተስፋ ጒሕ ባይሆን፥ ከሞት ጋር ትግል ነውና
ከዚህ ሌላ ትእዝብት ውረሻ፥ ሳይነጋ እንዳስመሸሽብኝ
ጊዜና ትውልድ ይፍረደን፥ ሳልነቃ እንዳስረፈድሽብኝ።
ያም ሆኖ ለራስሽ እንጂ፥ ለኔ ከቶም አታልቅሺ
አንቺ ነሽ እንባ እምትሺ፤ ...
የእምነትሽ መተሣሰሪያ፤ ውልሽ ለተላቀቀብሽ
ላንቺ ነው እንባ እሚያስፈልግሽ።
አዎን፥ይኸን እወቁልኝ፥ ምስክር ሁኑኝ ሰማዕታት
ለሷ ነው እንባ እሚያስፈልጋት።
ከጠላቶቼ ጭብጥ ውስጥ፥ ትንፋሼን በጄ ስነጥቃት
ሞቴን ከመንጋጋቸው ውስጥ፥ መንጭቄ እኔው ሰሞታት
ላገሬ ብድር ልከፍላት
የነፈገቺኝን ፍቅር፥ በራሴ ሞት ልለግሳት

ዳግም ከሞቴ ባንኜ፤ በመንፈስ ጣር ስሞግታት!...

ያኔ ነው እንባዋ የሚያጥራት።

ስለዚህ ለራስሽ እንጂ፥ ልቅሶሽ ለኔ ምን ሊረባ

ብቸኛ ምሬት ነው ኃይሉ፥ ወኔ መስለቢያው ነው እንባ።

እና ለራስሽ እዘኚ

እንጂ ከቶ ለኔ አትባክኚ። ....

ይልቅስ ተረት ልንገርሽ፥ የተላከ ከእንግሊዝ ዘንድ

እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ፥ እጅ ተይዞ ሊወሰድ፥

ምን እጅ አለው የእሳት ስደድ?

አያውቅም ክንዴ እንደሚያነድ። ...

ዳዊት እንዲያ በበገናው፥ ማልቀስ ማላዘን መያዙ

ይኸ የጐልያድ ውላጅ፥ ቢበዛበት ነው መዘዙ

ምንጩ እንደአሸን እየፈላ፥ አገሩን ምድሩን ማንቀዙ

ቸግሮት ነው፥ መጋፈጡ፥ ከስንቱ መወናጨፉ

በባላንጣው ሳቢያ ምክንያት፥ የራሱን ወገን ማርገፉ። ....

ታድያ እንግዲህ አንቺ ኢትዮጵያ፥ እኛስ ልጆችሽ ምንድነን

አመንኩሽ ማለት የማንችል፥ ፍቅራችን የሚያስነውረን

ዕዳችን የሚያስፎክረን

ግፋችን የሚያስከብረን

ቅንነት የሚያሳፍረን፥ ቂማችን የሚያስደስተን

ኸረ ምንድነን? ምንድነን?
አሜከላ እሚያብብብን
ፍግ እሚለመልምብን፥
ከአረም ጋር ያፈራን ጊንጦች፥ ከእንክርዳድ ያልተለየን ዘር
ግርዱ ከምርቱ ተማጥቆ፥ ከቶ ያልተበራየን መከር
ምንድነን? ምንድነን እኮ?
አረጋዊውን ባንቀልባ፥ ከምንሸከም እንኮኮ
ጐልማሳውን ከወኔ ጣር፥ ካልፈታን ከፍርሃት ምርኮ
እንደወዶ ገባ ወደል፥ መጠለሉን ከሴት ታኮ ....
ካቃተን፥ ምንድነን እኮ? ...
አየሽ አንቺ እማማ ኢትዮጵያ፥ አየሽ አንቺ እናት ዓለም
ቃል የእምነት ዕዳ ነው እንጂ፥ ያባት የናት እኮ አደለም። ....

ያም ይቅርና መርዶ ላርዳሽ፥ ስሚው እኔ እንደሰማሁት
እርም በልተሽ ከምትቀሪ፥ ስሚ፥ ገብርዬንም ጣሉት። ....
እስቲ እንግዲህ በይ ፍረጂኝ፣ ከእንግዲህ እኔ ፍሬ አላይም?
"ዘርቶ መቃም ወልዶ መሳም"
አባባል ለኔ አይባልም?
እስቲ ገብርዬን መሰል ዘር፥ ፍሬው ከቶ አይለመልምም?
እኔስ ዘር ዘራሁ አልልም? ....

ምነው ፍንጭትክን ገብርዬ፥ ያን ፍንጭትክን አጨለሙት

እንደሬት ልግ አከሰሉት

ከጡቶችሽ እቅፍ ነጥቀው፥ ከማኅፀንሽ ፍቅር ቆርጠው

እውነትን ሲንሉ እንዲህ ነው፥ ፈገግታውን አጨልመሙው። ....

እስቲ እባክህን ገብርዬ፥ የዛሬን እንኳ ስቀህ ሙት

በዕድል ጥቀርሻ እንደአጀሉት

እንደወላድ ጣውንት ጡት

አርማ ጉሳ እንደቀለሙት

ፈገግታህን አያጥቁሩት።

እምቢ በላቸው ገብርዬ፥ በአባት ሤራ እንዳስገዘቱት

በመሃላ እንዳሳገዱት

የነፍስህን ጮራ ብርሃን፥ ከገጽህ እንደቀበሩት

ዘለዓለም ላያጨልሙት

ወንድምዬ እምቢ በላቸው፥ የዛሬን እንኳ ስቀህ ሙት። ....

ያለፈ ጥረታችንን፥ ሳስታምመው ትዝ ሲለኝ

ከሞከርነው ነገር ይልቅ፥ ያልሞከርነው ነው እሚቆጨኝ።

እና በኔ ይሁንብህ፥ መጣሁ፥ ስቀህ ተቀበለኝ

እኔም ላዋይህ አድምጠኝ ....

እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ፥ እጅ ተይዞ ሊወሰድ

ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ?

አያውቅም ክንዴ እንደሚያነድ። ....

ለዓለማየሁ ቴዎድሮስ - (፲፱፻፶፮ - ደሴ)



# ስለደራሲው በጥቂቱ

"የማይነጋ ህልም ሳልም
የማይድን በሽታ ሳክም
የማያድግ ችግኝ ሳርም
የሰው ሕይወት ስከረክም
እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም"

ባለቅኔ ሎሬት ብላቴን ጌታ ፀጋዬ ገብረመድኅን (1928-1998) ቦዳ ተብላ በምትታወቅ አምቦ ካተማ አካባቢ በምትገኝ ተራራማ ቦታ ተወለዱ። በአምቦ ማአረገ ሕይወት ቀ.ኃ.ሥ. ትምህርት ቤት ከዚያም ጀነራል ዊንጌትና በአዲስ አበባ የንግድ ትምህርት ቤት በአገር ውስጥ ትምህርታቸውን ከገፉ በኋላ በቺካጎ ብላክስቶን በህግ ትምህርት ተመርቀው በ1952 እንደ ወጡ በለንደን ከተማ የቴአትር ትምህርት በሮያል ኮርት ቴአትርና በፓሪስ ኮሜዲ ፍራንሴዝ ተከታትለዋል። ከ1954 እስከ 1964 የብሔራዊ ቴአትር በአርቲስቲክ ዳይሬክተርነት አገለግለዋል። ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ዲፓርትመንትን አቋቁመዋል።

ሆኖም በ1960ዎቹ ደርግ አብዛኛውን የቴአትር ሥራዎቻቸውን ሲያግድ እሳቸውንም ለማሰር በቅቷል።

ብላቴን ሎሬት ጸጋዬ በርካታ ግጥሞችን፥ የቴአትር ሥራዎችን የተለያዩ መጣጥፎችንና ዘፈኖችን አበርክታዋል። ጸጋዬ በ1990 ለጉበት በሽታ ሕክምና በመሻት ወደ ማንሃታን በሄዱበት አርፈዋል። በአዲስ አበባ በቅድስት ሥላሴ ቤተክርቲያን ተቀብረዋል።

እንደ፡ አዉሮፓ፡ አቆጣጠር፡ በ 2002 ዓ.ም. የብላቴን ሎሬት ጸጋዬ፡ ገብረ መድህን፡ ግጥም፡ ("Proud to be African") አዲስ፡ በተመሰረተው፡ የአፍሪካ፡ ኣንድነት፡ ማሕበር፡ በሕዝብ፥ መዝሙርነት፡ ተመርጧል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. እሳት ወይ አበባ (**ግጥምና ቅኔ**)
2. የዳኒሲዩስ ዳኘነት (**ተውኔት**)
3. በልግ(**ተውኔት**)
4. የደም አዝመራ(**ተውኔት**)
5. እኔም እኮ ሰው ነኝ(**ተውኔት**)
6. የከርሞ ሰው (**ተውኔት**)
7. የእሾህ አክሊል(**ተውኔት**)
8. ክራር ሲከር(**ተውኔት**)
9. አስቀያሚ ልጃገረድ(**ተውኔት**)
10. እኝ ብዬ መጣሁ(**ተውኔት**)
11. ቴዎድሮስ(**ተውኔት**)
12. ምኒልክ(**ተውኔት**)
13. ጴጥሮስ ያቺን ሰአት(**ተውኔት**)
14. ዘርዓይ ደረስ(**ተውኔት**)
15. ጆሮ ገድፍ(**ተውኔት**)
16. ሀሁ በስድስት ወር(**ተውኔት**)
17. እናት ዓለም ጠኑ(**ተውኔት**)
18. መልእክተ ወዛደር(**ተውኔት**)
19. አቡጊዳ ቀይሶ(**ተውኔት**)
20. ጋሞ(**ተውኔት**)
21. ሀሁ ወይም ፐፑ(**ተውኔት**)
22. ቴራቲረኞች የምፀት ኮሜዲ፥ አልታየም (**ተውኔት**)

23. ዐፅም በየገጹ (**ተውኔት**)
24. ሰቆቃወ ጴጥሮስ(**ተውኔት**)
25. ትንሣኤ ሰንደቅ ዓላማ(**ተውኔት**)
26. የመቅደላ ስንብት(**ተውኔት**)
27. ጥላሁን ግዛው(**ተውኔት**)
28. ዐፅምና ፈለጉ(**ተውኔት**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY